# ጊዜው

ልዩ ዕትም



# “ነጣቂ ተኩላ”!

## የዘመኑ ነቢያትና ሐዋርያት

# ከአዘጋጆች ብዕር

ጌታችንና አምላካችን ክርስቶስ የመልዕክቱ ፍሰት ሳይቋረጥ ከተናገረባቸው ስብከቶች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው በተለምዶ “የተራራው ስብከት” የሚባለው ነው። በዚህ ስብከቱ እጅግ በርካታ ጉዳዮችን የዳሰሰው ጌታ፤ “ብሩካን” በማለት በማቴዎስ ምዕራፍ 5 ንግግሩን ጀምሮ ምዕራፍ 7 ላይ ሲደርስ አንድ ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። እንዲህም አለ፤ “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?” (ማቴ 7፡15-16)።

በአገራችን የደቡብ ክፍል የሚነገር አንድ ተረት አለ፤ ጥንቸል፣ ቀበሮና ተኩላ በስምምነት ተላምደው ይኖሩ ነበር። ቀበሮውና ተኩላው ከሚመገቡት ሥጋ ጀምሮ የባህርይም ተመሳስሎ ስለነበራቸው ይግባቡ ነበር። ጥንቸሉ በአመጋገቡ ከእነርሱ የሚለይ ቢሆንም ፈጣን መልዕክተኛ በመሆኑ በአገልግሎቱ ተስማምተው ለመኖር ቀጠሉ።

ሆኖም ቀበሮውና ተኩላው ሲያስቡት ከጥንቸሉ ጋር በዚህ መልኩ መኖራቸው አልተስማማቸውም። እናም ሲነጋገሩ ይህንን ጥንቸል ብንበላው፤ አንዳችን እግሩን፣ ሌላችን ደግሞ ሌላውን ይዘን ብንትተው በቀላሉ ልንገነጣጥለውን እንችላለን፤ መጠኑ ትንሽ በመሆኑ ለምሳ የሚበቃን ባይሆንም ለቁርስ ምንም አይልም ተባባሉ።

ከተላከበት ሲመለስ ሁኔታው ያላማረው ጥንቸል፤ ተኩላው ጥርሱን ሲያፋጭ በድንገት ተመልክቶ “ምን ሆናችኋል፤ ሰላም አይደለም?” ብሎ ጠየቃቸው። ችግር እንደሌለ ቢነግሩትም ከባህርያቸው ማንነታቸውን አሳምሮ የሚያውቀው ብልጡ ጥንቸል ቀስ ብሎ ሾልኮ አመለጠ።

በጉዳዩ የተናደዱት ተኩላና ቀበሮ ጥንቸሉን አባብሎ የመያዝ ወጥመድ በቀጣይ ዘረጉ። ተኩላው ሕመምተኛ በመምሰል ይተኛል፤ ቀበሮው ጥንቸሉ ወዳለበት ይሄድና የተኩላውን በጽኑ መታተም ይነግረዋል፤ ጥንቸሉም ስለ ቀድሞው ወዳጅነታቸው በሚል ተኩላውን ለመጠየቅ ሲመጣ አፈፍ ያደርገውና ከቀበሮ ጋር ይካፈለዋል።

ድራማው ተቀናበረ፤ ጥንቸል በሚመጣበት መንገድ ቀበሮው ጠብቆ የተኩላን መታመም ነገረው። ጥንቸልም ተኩላን ለመጠየቅ ወደቤቱ ሄደ። ሆኖም ዓይኖቹን ጨፍኖ (ሽፋሽፍቱ ግን ይርገበገብ ነበር)፣ አፉን ዘግቶ የተኛውን ተኩላ ጥንቸሉ ሲያይ የሆነ ወጥመድ የተዘጋጀለት መሰለውና በጣም ተጠራጠረ። ጥቂት አሰበና “ተኩላ እኮ ሲሞት ዓይኑ በቶሎ ሲከደን አፉን ግን ይከፍታል” አለ። ይህንን የሰማው ተኩላም ዓይኑን ግጥም አድርጎ በመጨፈን አፉን ሲከፍት ጥንቸሉ ሳይታይ ሮጦ አመለጠ።

ጌታም እንዲህ አለ፤ “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ”። ከተኩላ እንዴት እንጠበቃለን ብለን ከጠየቅን በታሪኩ እንደተገለጸው ጥንቸል ብልህ በመሆንና አርቆ በማሰብ፣ በጸሎትና በቃል ጥናት ነው።

በዚህ የጊዜው መጽሔት ልዩ ዕትም በዘመናችን በተለይም በአገራችን የበግ ለምድ ለብሰው ምዕመኑን እያምታቱ ስላሉት “ተኩላዎች” ሰፊ ትንታኔ ተሰጥቷል። የቀረቡት ጽሁፎች ዓላማና ይዘት የሰዎችን ስም እየጠሩ ስህተታቸውን ለማጋለጥ አይደለም። ይልቁንም ጽሁፎቹ ትኩረት ያደረጉት ስለ **ተኩላ ባሕርያት**፣ ጌታችን **“ተጠንቀቁ”** ሲልና **“ተኩላ”** ብሎ ሲጠራቸው **ምን ማለቱ እንደሆነ፤ እውነተኛ ነቢይን በምን እንደምንፈትን፤ የዱሮና የአሁኑን ነቢያትና ሐዋርያት ንጽጽራዊ ትንታኔ** እንዲሁም **ስለ ተዓምራትና ስለ ልሳን ትርጉምና አጠቃቀም** ነው።

በዘመናችን በየሚዲያው እንደምንመለከተው እነዚህ የሃሰት ነቢያትና ሐዋርያት ክርስቶስ እንዳለው “የበግ ለምድ” መልበስ የሚያስፈልጋቸው አይመስሉም። ሃማይኖቱን እንተወውና ሰብዓዊነት በጎደለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት የሚከተላቸውን ምዕመን እንዴት እንደሚያሰቃዩ መስማት ለአእምሮ የሚከብድ ነው። ከሁሉ በላይ ግን ይህንን የሚያደርጉት በእግዚአብሔር ስም በመሆኑ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አንገት የሚያስደፋም ነው። ይህ፤ እጅግ የከበረውና ለምህረቱና ርኅራኄው ወሰን የሌለውን አምላክ ስም እጅግ የሚያጠለሽ ብቻ ሳይሆን በከፉ እንዲነሳ የሚያደርግ እኩይ ተግባር ነው።

ጌታችን ስለተኩላዎች ሲናገር “ተጠንቀቁ” ቢለንም ዋናው ዓላማ ግን ዕድሜልካችንን የተኩላዎችን ድርጊት ስንከታተልና የሡሩትን መጥፎ ተግባራት ስንኮንን እንድንኖር አይደለም። ይልቁንም ዋና ትኩረታችን “መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል” (ዮሐንስ 10፡11) በማለት የተናገረውን የመልካሙን እረኛ የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ባህርያት ጠንቅቆ ማወቁ ላይ ነው። የዚህ ልዩ ዕትም ዋና ዓላማም ይኸው ነው።

መልካም ንባብ።

አዘጋጆቹ

# ማውጫ

"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ" 4

የእውነተኛ ነቢይ መለኪያ መሥፈርቶች 9

ነቢያት፤ ዱሮና ዘንድሮ 13

ከነቢይም ሁሉ የሚበልጥ 21

"ነጣቂ ተኵላዎች" - የዘመኑ ነቢያትና ሐዋርያት 24

ተዓምራት፤ በፊሊጶስና በጠንቋዩ ሲሞን 28

ሐዋርያነት፤ ዱሮና ዘንድሮ 32

በልሳን መናገር: ትርጉምና አጠቃቀሙ 39

የሽፋን ፎቶ፤ ከRefkije Royal መጽሐፍ ሽፋን የተወሰደ፤ ለማሳያነት የተጠቀምናቸው ሌሎቹ የውስጥ ፎቶዎችም ከኢንተርኔት የተወሰዱ ናቸው

"ስለዚህ **ጊዜው** መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም" ማርቆስ 13፡33

**ጊዜው** መጽሔት የመጨረሻው ዘመን መድረሱን ለማስገንዘብና ለማስጠንቀቅ መልዕክት የምታቀርብ እንደመሆኗ የመጽሔቷ ስም ዓርማው ውስጥ ተካትቷል፡፡ ከሥሩ የሚታየው ጥሩምባ ከመልዕክቱ በፊት ንቃት እንዲኖር የሚሰማ የማንቂያ ድምጽ ማመላከቻ ነው፡፡

**አዘጋጆች፤**
ዳዊት መሐሪ
ድርባ ፈቃዱ
ዘውዱ ሰብለወርቅ
ጥበበሥላሴ መንግሥቱ
**አምደኞች፤**
ፓ/ር አገኘሁ ወንድም
ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ
**ሽያጭና ስርጭት**
ልዝቤ ፈንታሁን
ወገን ፈጠነ
ምንትዋብ ሰብለወርቅ
**Logo Design and Layout:**
Danny Monnie

**አድራሻ፤**
**ኢሜይል፤** editor@giziew.org
**ስልክ: 911-918194/911-335790/911-373097**
**መ.ሳ.ቁ. 438**፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Facebook: fb.me/giziew7
**ከአገር ውጪ ለመደወልና ለመጻፍ: +1 314 499-8477**
Viber: **+1 785 730-4800**
Whatsapp: **+1 314 499-8477**
Telegram: t.me/giziew7 ወይም **+1 314 499-8477**
Website: http://www.giziew.org/

በተለይ እስካልተጠቀሰ በዚህ መጽሔት ውስጥ የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት እኤአ በ1962 ከታተመውና ከአዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ነው።

**የጊዜው መጽሔት ዓላማ፤**
**መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት፤ መድኃኒዓለምን ማዕከል ያደረገ የወንጌል መልዕክት ማቅረብ።**

# “ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ”

ጌታችንና መድኃኒታችን በምድር የነበረውን አገልግሎት ወደመፈጸሙ በተቃረበበት ወቅት የእርሱን የፍቅር ጥሪ ስትቃወም ለነበረችው ኢየሩሳሌም “ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትሰበስብ ልጆችሽን” ለመሰብሰብ ብሞክርም ስላልወደዳችሁ “ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል” በማለት አለቀሰላት፤ በመቀጠልም “በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም” በማለት ከመቅደሱ ወጥቶ ሄደ (ማቴ. 23፡37-39)።

ሁኔታው ያስጨነቃቸው፣ የቤተመቅደሱ ጉዳይ ያሳሰባቸው፣ የዓለም ፍጻሜ እንዴት ይሆን የሚል ጥያቄ የጫረባቸው ደቀመዛሙርት ወደ ጌታችን በመቅረብ “ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት” (ማቴ. 24፡3)። ጌታችን ጥያቄያቸውን ሲመልስ በመጀመሪያ የተናገረው “ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ” የሚል ነበር (ማቴ. 24፡4)። ቀጥሎም ይህንን የመሳት (የመታለል) ጉዳይ በማቴዎስ ምዕራፍ 24 ላይ አራት ጊዜ በመደጋገም ማስጠንቀቂያውን አጸናው (ቁጥር፤ 5፣11፣13 እና 24)።

ለምን ይሆን ጌታችን ስለ መታለል እንዲህ በአጽንዖት የተናገረው? ለምንስ ይሆን የመታለል ጉዳይ ከሃሰተኛ ነቢያትና ከሃሰተኛ ተዓምራት ጋር በማያያዝ የተናገረው?

አንድን ሰው ለማሳሳት ቀላሉ መንገድ ውሸትን መንገር አይደለም። ይልቁንም ውሸትን ከእውነት ጋር በመቀላቀል፤ የእውነትን አሠራርና መንገድ በሃሰት በመደባለቅ፤ በብዙ ውሸት ውስጥ አንዲት ጠብታ እውነት ጣል በማድረግ ሰዎችን በቀላሉ ማታለል ይቻላል። ይህ ደግሞ የሠይጣን ዓይነተኛ መሣሪያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።



እናታችን ሔዋን በኤድን ገነት ከባሏ አዳም ተለይታ ባለችበት ወቅት ሠይጣን በእባብ ተመስሎ ወደ እርሷ በመቅረብ የነገራት ውሸት ብቻ አልነበረም። ትንንሽ የእውነት ጠብታዎችም ነበሩበት። የማታለያ ወጥመዱንም ሲዘረጋ ለስለስ ብሎ በስልት “በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን?” አላት። ሔዋንም አምላክ እንደዚያ እንዳላዘዘ ማብራሪያ ከሰጠች በኋላ መብላት የሌለባቸው ፍሬ እንዳለና ከዚያ ከበሉ እንደሚሞቱ ስትናገር እባቡ “ሞትን አትሞቱም” በማለት አወዛገባት።

በመቀጠልም በማር የተለወሰ መርዙን ሰጣት፤ ከእውነት ጋር የተቀላቀለውን ውሸት ቀስ ብሎ በማቅረብ ፍሬውን “በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው” አትብሉ ያላችሁ በማለት የበለጠ አወሳሰበባት። ይህንን ከእውነት ጋር የተቀየጠውን ውሸት እንደ እውነት አድርጋ ሔዋን በመውሰድ ፍሬውን በመብላት የእግዚአብሔር አምላኳን ሕግ ተላለፈች (ዘፍ. 3፡1-6)።

ዓይኗም ተከፈተ፤ መልካምና ክፉውን አወቀች፤ ነገርግን ፍሬውን ሳትበላ እግዚአብሔርን ብቻ በመታዘዝ ዓይኗ ይከፈት ነበር፤ ክፉውንም ለማወቅ የግድ አለመታዘዝ አልነበረባትም፤ ለእውነት በመታዘዝ የክፉውን ማንነት በቀላሉ መረዳት ትችል ነበር። ሆኖም እውነትን በተላበሰ ውሸት ተታልላ ሕይወቷ ለውድቀት ተዳረገ። “የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች” ይላል መጽሐፍ ቅዱስ(1ጢሞ. 2፡14)።

ይህ ውሸትን ከእውነት ጋር እየቀላቀሉ የማቅረብ ስልት ሠይጣን ለዘመናት ቀጥሎበት እስራኤላውያንም በዚሁ ወጥመድ በተደጋጋሚ ሲወድቁ እናነባለን።

አክዓብ የእስራኤል ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ጣዖት አምላኪ የነበረችው ሚስቱ ኢልዛቤል ምድረ እስራኤልን በጣዖት አምልኮ ሞላችው (1ነገ. 18)። አገሩ ሁሉ በርኩሰት መሞላቱን የተመለከተው ነቢዩ ኤልያስ ለንጉሡ አንድ ግድድሮሽ አቀረበለት። የቀረበውንም ተግዳሮት በመቀበል አክዓብ አራት መቶ በላይ የሚሆኑትን የብኤል ነቢያትን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ አስጠራቸው።

“እናንተም የአምላካችሁን ስም ጥሩ፥ እኔም የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ፤ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ፥ እርሱ አምላክ ይሁን” በማለት ኤልያስ ለጣዖት አምላኪ ነቢያቱና ለሕዝቡ ጥሪ አደረገ። ለመስዋዕትም የተዘጋጁት ወይፈኖች ታርደው ቀረቡ። ቅድሚያው ለብኤል ነቢያት ተሰጥቶ አማልክቶቻቸውን በእሣት እንዲመልሱ ዕድሉ ተሰጣቸው።

“ስለዚህ የተሰጣቸውን ወይፈን ወስደው አዘጋጁት። ከዚያም ከጧት እስከ እኩለ ቀን የብኤልን ስም ጠሩ፤ “ብኤል ሆይ ስማን” እያሉ ጮኹ፤ ድምፅ ግን የለም፤ የሚመልስ አልነበረም፤ በሠሩት መሠዊያ ዙሪያም እየዘለሉ ያሸበሸቡ ነበር። ... እየጮኹ እንደ ልማዳቸው ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ሰውነታቸውን በሰይፍና በጩቤ ያቈስሉ ነበር። እኩለ ቀን ዐለፈ፤ እነርሱም የሠርክ መሥዋዕት እስኪቀርብ ድረስ የሚዘላብድ ትንቢት ይናገሩ ነበር፤ አሁንም ድምፅ የለም፤ የመለሰና ከቁም ነገር የቈጠረውም አልነበረም።

“ከዚያም ኤልያስ ሕዝቡን በሙሉ፣ “ወደ እኔ ቅረቡ” አላቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ። ... በመሠዊያውም ዙሪያ ዐሥራ አምስት ሊትር ውሃ የሚይዝ ጕድጓድ ቈፈረ፤ ዕንጨቱን ረበረበ” የተዘጋጀውን የወይፈን ሥጋ ካቀረበ በኋላ “በዕንጨቱ ላይ አኖረው። ከዚያም፣ “ውሃ በአራት ጋን ሞልታችሁ፣ በመሥዋዕቱና በዕንጨቱ ላይ አፍስሱ” አላቸው። ደግሞም፣ “እንደ ገና ጨምሩበት” አላቸው፤ እነርሱም ጨመሩበት። “ሦስተኛም ጨምሩበት” ሲል አዘዛቸው፤ እነርሱም ለሦስተኛ ጊዜ ጨመሩበት። ውሃውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፤ ጕድጓዱንም ሞላው”።

ከዚያም ኤልያስ የአምላኩን የእግዚአብሔርን ስም ጠራ፤ “የአብርሃም፣ የይስሐቅና የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የእስራኤል አምላክ መሆንህ፣ እኔም የአንተ አገልጋይ መሆኔና ይህን ሁሉ በትእዛዝህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይታወቅ። ይህ ሕዝብ፣ አንተ አምላክ እግዚአብሔር እውነተኛ መሆንህንና ልባቸውን የመለስኸው አንተ መሆንህን ያውቁ ዘንድ እባክህ ስማኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ መልስልኝ” በማለት ወደ አምላኩ ልመናውን አቀረበ።

“ከዚያም የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ መሥዋዕቱን፣ ዕንጨቱን፣ ድንጋዩንና ዐፈሩን ፈጽማ በላች፤ በጕድጓዱ



ውስጥ ያለውንም ውሃ ላሰች። ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ፣ በግንባራቸው ተደፍተው፣ “አምላክ እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ ነው! እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው!” አሉ። እውነተኛው አምላክ በእሣት መለሰ (1ነገሥት 18)።

እሣት ከሰማይ ማውረድ የእውነተኛው አምላክ መገለጫ ሆነ። የአምላክን አሠራር በመኮረጅ ሰዎችን በስህተት መንገድ መምራት ልዩ ክህሎት ያለው ሠይጣን ባለንበት ዘመን ይህንን እሣት የማውረድ፣ ተዓምር የመሥራት፣ ድንቅ የማድረግ ክስተት ብዙዎችን ለማታለል የመጠቀሚያ መሣሪያ እያደረገው ይገኛል። በኤልያስ ዘመን እሣት ከሰማይ ማውረድ የትክክለኛነት ማረጋገጫ ሆኖ ስለታየ በተለይ በመጨረሻው ዘመን ያኑ መድገም ሰዎችን ለማሳት ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ እናገኘዋለን።

ባለራዕዩ ዮሐንስ በኋለኛው ዘመን የሚሆነውን ሲናገር ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ “ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉ” በማለት የተነበየውን ለየት ባለ መልኩ ያቀርበዋል። በራዕይ 13 ላይ በአውሬ የተመሰለውና ከባህር (በትንቢታዊ ፍቺው ከብዙ ሕዝብ መካከል ራዕይ 17፡15) የሚወጣው አውሬ፤ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ መልክ በመያዝ ዓለምን እንደሚቆጣጠር ይናገራል (ራዕይ 13፡3፣8)። በተለይ ደግሞ ዘንዶው ወይም የቀደመው እባብ የተባለው ሰይጣን (ራዕይ 12፡9) ለዚህ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ የበላይነት ላለው ኃይል ሥልጣን ስለሰጠው አውሬውን ማን ሊዋጋው ይችላል? እያሉ በምድር ያሉ እንደሚሰግዱለት ይናገራል (ራዕይ 13፡4፣8)።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለራዕዩ ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ እንደተመለከተና ይህ ኃይል ደግሞ ለቀደመው ከባህር ለወጣው ኃይል በምድር የሚኖሩ እንዲሰግዱለት እንደሚያደርግ ይናገራል (ራዕይ 13፡12)። ይህንን ስግደትም

ለማስፈጸም እሣትንም እንኳን ሳይቀር ከሰማይ እንደሚያወርድ፤ ታላላቅ ምልክቶችን፣ ድንቆችንና ተዓምራቶችን እንደሚያደርግ፤ በዚህም ድርጊቱ በምድር የሚኖሩትን እንደሚያስት ይተነብያል (ራዕይ 13፡14)።

በዚህ ሳያቆም ዘንዶው (የቀደመው እባብ ወይም ሠይጣን)፣ ከባህር የወጣው አውሬ (ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሥልጣንን አጣምሮ የያዘው ኃይል) እና ከምድር የወጣው አውሬ (ሃሰተኛው ነቢይም ይባላል) አስመሳይ የሥላሴ ዓይነት ጥምረት በመፍጠር ምድርን ሁሉ በድንቅና ተዓምራት እንደሚያታልሉ ይናገራል። “ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጉንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤ ምልክትን የሚያደርጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና” ይላል (ራዕይ 16፡13-14)።

ጌታችን ክርስቶስ በመጨረሻው ዘመን “ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ” ያለው ያለምክንያት አልነበረም። የሚነሱት ነቢያት ጥቂቶች፤ የሚያስቱትም ሕዝብ ጥቂት ነው አላለም። ይልቁንም የሃሰተኛ ነቢያቱ ቁጥር ብዙ እንደሆነና እርሱን በመከተል የሚስቱትም ሰዎች ብዙዎች መሆናቸውን ነው ጌታችን የተናገረው። ባለንበት የመጨረሻ ዘመን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

ባለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት በአገራችን ብቻ እየሆነ ያለውን ብንመለከት በየቦታው፣ በየማኅበራዊ ሚዲያው፣ “ነቢይ”፣ “ሐዋርያ”፣“የእግዚአብሔር ሰው”፣ “ኧፖስትል”፣ “ፐሮፌት”፣ “ማን ኦቭ ጎድ”፣ … እየተባሉ የሚጠሩ ወንዶችም ሴቶችም ከቁጥር በላይ በርክተዋል። የእነዚህ አብዛኛዎቹ አካሄድ ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በርካታ ሕዝብ በመሰብሰብ፤ ሰዉ መስማት የሚፈልገውን ነገር በመንገር፤ በአብዛኛው የፈውስና መሰል ፕሮግራሞችን ማካሄድ ነው።



አንዳንዶቹ ተጠንተው ሌሎቹ ደግሞ በግምት የሚደረጉት “ትንቢቶች” እና “ፈውሶች” ብዙዎችን ወደ መታለል እየወሰዱ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ከመታለል ባሻገር እነዚህን የሃሰት ትንቢቶች እንደ እውነት በመቀበል ከሥራቸው የተፈናቀሉ፣ ከትዳራቸው የተለያዩ፣ ኑሯቸው የተመሰቃቀለ፣ ገንዘባቸውን የተበሉ እንዲያውም ሕይወታቸውንም ያጡ እንዳሉ የጉዳቱ ሰለባዎች ይናገራሉ።

በአፍሪካ አህጉር ባጠቃላይ ያለው ሁኔታ ይህንኑ የሚሳይ ሆኖ እናየዋለን። ጥቂት የማይባሉ በአገራችን ላይ በነቢይና በሐዋሪያነት የሚጠሩ ዘመናዮች ልምምዳቸውን የቀሰሙት በሌሎች የአፍሪካ አገራት (እንደ ናይጄሪያ ካሉ) ከሚገኙ “አባቶቻቸው” እንደሆነ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፤ ራሳቸው ሰዎቹም ሲናገሩ ይደመጣሉ። በርካታ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ የሚንጣት አፍሪካም ሆነች አገራችን፤ ዜጎቿ ላለባቸው ለዚህ አንገት የሚያስደፉ ችግር መፍትሔው በክርስቶስ ስም የብልጽግና ወንጌል የሚሰብኩላቸው “ሐዋሪያት”ና “ነቢያት” ሆነዋል።

መበልጸግ በራሱ ምንም ችግር ያለበት ጉዳይ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ በርካታ ሰዎች ባለጸጎች እንደነበሩ እናነባለን። ኢዮብ አንዱ ነው፤ “ሀብቱም ሰባት ሺህ በጎች፥ ሦስት ሺህም ግመሎች፥ አምስት መቶም ጥማድ በሬ፥ አምስት መቶም እንስት አህዮች ነበረ፥ እጅግ ብዙም ባሪያዎች ነበሩት፤ ያም ሰው በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቅ ነበረ” (ኢዮብ 1፡2)። ይህንን ሃብት በዚህ ዘመን ባለው ዋጋ ብናሰላው ኢዮብ በቀላሉ ባለብዙ ሚሊዮነር ነበር። ነገርግን ይኸው ኢዮብ ሃብቱ ሁሉ ወድሞ ሙልጩን በቀረበት ጊዜ “እነሆ፥ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ፤ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ” በማለት ነበር በአምላኩ ላይ የነበረውን ፍጹም መተማመን የተናገረው (ኢዮብ 13፡15)። በዘመናችን ሲሆን የምናየው ግን እንደዚያ አይደለም።

“ችግር ከቤትህ ተወግዷ፣ በመሥሪያ ቤትህ የተነሳብህ የጠላት አሠራር ፈርሷል፣ በጎረቤትህ አካባቢ ያለው የምቀኝነት ምሽግ ድባቅ ተመትቷል፣ ወደ ከፍታ ነው የምትጓዘው፣ ለታላቅነት ተጠርተሃል፣ ከሁሉ በላይ ከፍ ስትል ይታየኛል፣ ቅባቱ ባንተ ላይ ፈስሷል፣ ከዚህ በኋላ ሃብትና ብልጽግና ካንተ አይለይም፣ ወዘተ” የመሳሰሉ የሰዎችን ስነልቡና በቀላሉ የሚሰርቁና ከዕለታዊ የኑሮ ተግዳሮት ጋር የተያያዙ “ትንቢቶችንና መገለጦችን” ከመድረክ ይሰማሉ። የጉዳቱ ሰለባዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ሐሰተኛ ነቢያቱ “የሚያገለግሉት” በመረጃ ነው፤ ይህም ምዕመኑን በእንግዳ ማረፊያ (ገስት ሃውስ) በሺዎች የሚቆጠር ብር ከፍሎ እንዲቀመጥ በማድረግ፣



ወይም በሌላ ስልት አስቀድሞ ችግሩን እንዲናገር በማድረግና ቀጥተኛ መረጃ ከራሱ በመሰብሰብ ነው።

ይህንንም በረቀቀ ስልት ወደ “ነብዩ” በማስተላለፍ፤ “ነብዩም” “ጌታ ነው የተናገረኝ” በማለት በሕዝብ ፊት መልሶ በመናገርና ተሰብሳቢውን በማስደመም በሚደረግ ዓይን ያወጣ የማጭበርበር “አገልግሎት” ነው። ይህንን ግልጽ ውንብድና እንደ እውነተኛ መልዕክት በመቀበል እያወቀ የሚታለለውና ሳያውቅ በስህተት መንገድ ላይ ያለው ሕዝብ ለዕለታዊ የኑሮና የጤና ችግሩ ማርገቢያ የሚሆን ተስፋ አዘል “ትንቢት” መስማት በመፈለግ በየቦታው በብዛት ተሰብስቦ ይታያል። ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉም ነገሩ ለአንዳንዶች እንደ ሱስ እንደሆነባቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ። ይህ አስገራሚና አስደንጋጭ ሁኔታ ጌታ ኢየሱስ “ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ” የሚለውን የትንቢት ቃል በጥንቃቄ እንድንመለከተው የሚያደርግ ነው።

ከእነዚሁ ስሜትን ከሚኮረኩሩ የብልጽግና ወንጌል ትምህርቶች ጋር በተያያዘ የፈውስ አገልግሎቶችም ይካሄዳሉ። የሰውን ስብዕና እጅግ በሚነካ፤ የእህቶችን ማንነት እጅግ በሚያዋርድ መልኩ ሰዎች እየተገፈተሩ ይጣላሉ፤ በደረታቸው መሬት ላይ እንዲነጠፉ ይደረጋል፤ በአየር ካራቴ ይመታሉ፤ በቡጢ ይነረታሉ፤ አዛውንት አባቶችና እናቶችም ሳይቀሩ የዚሁ ሰለባ ሲሆኑ ማየት የዕለት ተዕለት ክስተት ሆኗል።

በፈውስ ስም ደግሞ “የተጸለየበት” ነው እየተባለ የሚቸበቸበው “ዘይት” ለሃሰተኛ ነቢያቱ ቀላል የገቢ ምንጭ ሆኖላቸዋል። የምግብ ዘይት ዋጋ እጅግ በናረበትና ጥራቱን የጠበቀ ዘይት ለማግኘት አስቸጋሪ በሆነበት አገር፤ “እፈወሳለሁ” በማለት በትንሽ ብልቃጥ የተሞላች ዘይት እጅግ ውድ በሆነ ዋጋ ለመግዛት የሚሰለፈው ሰው መብዛቱ “ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ” የሚለውን የጌታ ኢየሱስን ቃልና በራዕይ ላይ ከምድር የወጣው ኃይል በድንቅና በተዓምራት እንዲሁም በምልክት ብዙዎችን ያስታል ያለውን ደግመን እንድናሰላስልበት የሚያደርገን ነው።



በኤልያስ ዘመን ጸሎትን ሰምቶ በእሣት የመለሰው ኃያሉ ጌታ እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ መሆኑ ተረጋግጦ ነበር። ይህም የእውነተኛ አምልኮ ማሳያ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል። በኤልያስ ዘመን ሰምቶ በእሣት መመለስ ባለመቻሉ የተዋረደው አሳቹ ሰይጣን፤ ባለንበት የመጨረሻ ዘመን የከሰረውን ታሪኩ ለማስተካከልና እውነተኛ አምላክ እርሱ መሆኑን ለማሳየት እሣትን ከሰማይ እንደሚያወርድ ዮሐንስ በራዕዩ ተመልክቷል (13፡13)። ሃሰትን ከእውነት ጋር በመቀላቀል ሰዎችን በቀላሉ በማታለል የሚታወቀው ሰይጣን፤ በዚህ ዘመን ይህንኑ ስልት ሰዎችን ለማሳሳቻ፣ ለማታለያ ሲጠቀምበት ይታያል። ወደፊት ደግሞ መጠኑን በመጨመር “የእግዚአብሔር እሣት ወረደች” በማስባል ብዙዎችን ያሳስትበታል። ጌታችን ግን ያለው “ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ” ነው።

እጅግ ብዙ ሰዎችን በቀላሉ ወደሚፈለግበት አቅጣጫ ለመንዳት የሚቻለው ለአእምሯቸው ሳይሆን ለስሜታቸው ደስ የሚላቸውን በመንገር ነው። በዘመናችን ያሉቱ የሚጠቀሙት ስልት ከዚህ የተለየ አይደለም። ጠንከር ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ፣ አስተምህሮ (ዶክትሪን)፣ ወዘተ ለምዕመናቸው ማስተማር

የማይፈልጉት የዘመናችን “መምህራን፣ ነቢያት፣ ኧፖስትሎች፣ ፕሮፌቶች፣ …” በዚህ መስመር ላይ ያለ አንዳች ችግር ሲመላለሱ እየታዩ ነው። ራሱን ለዕርድ እንደሚያቀርብ በግ በየቀኑ ወደ ጥፋት በሚወስደው ሰፊ ጎዳና ላይ እየተጓዘ ያለው ሕዝብም ቆም ብሎ “ምን እየሆነ ነው?” ብሎ መጠየቅ ይገባዋል።

ጌታችን በምድር በነበረበት ጊዜ እጅግ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል፤ ሐዋሪያቱም እንዲሁ። ችግሩ ያለው ድንቅና ተዓምራትን ማድረግ ላይ ሳይሆን፤ ድንቅ የተደረገለት ሰው በቀጣይ ሕይወቱ ወዴት ይሄዳል? የሚለው ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል ጥናትና የተረጋጋ ሕይወት? ወይስ ወደ ሌላ ተጨማሪ ተዓምራት ፍለጋ? ከዚህ ጋር ተያይዞ “ነቢይና ሐዋሪያ” ነን የሚሉትን ግለሰቦች ሕይወት መመርመር አስፈላጊ ነው። ምን ዓይነት ፍሬ ነው በሕይወታቸው የሚታየው የሚለውን መጠየቅ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

“ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ” (ማቴ. 7፡21-23)።



እነዚህ ራሳቸውን የሾሙ የሃሰት ነቢያት የሚኖሩት ኑሮ ሊጤን የሚገባው ነው። ተዓምራትና ፈውስን ለመቀበል ከመጣው ሕዝብ በተለያየ ስልት በሚወስዱት ገንዘብ ጥግ የደረሰ ዓለማዊ ሕይወት የሚኖሩት እነዚህ “ነቢያት”፤ በጉባዔ ፊት በግልጽ የተቃወሟቸውን እንደ ግል ጠባቂ በቀጠሯቸው ጡንቸኞች ዝም እንዲሉ ከመናገር እስከ መደብደብና እንደሚያጠፏቸው እስከማስፈራራት እንደሚደርሱ የችግሩ ሰለባዎች ሲናገሩ ይደመጣሉ። ከፍሬ ማወቅ ማለት አንዱ ይህ ነው። ጌታችን ስለሁላችን ተደበደበ፣ ተተፋበት፣ ተገረፈ፣ ተሰቃየ እንጂ ማንንም በክፉ ቃል እንኳን አልተናገረም። እንዴት የእርሱ አገልጋይ ነኝ የሚል ፈጽሞ ተጻጻሪ ነገር እያደረገ “የጌታ መልዕክተኛ ነኝ” ይላል? ስለዚህ ልንነቃ ይገባናል፤ ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት ዋንኛው መንገድ ድንቅ፣ ተዓምራትና መገለጥ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት በማጥናትና ራስን አዋርዶ በአምላክ ፊት በመቅረብ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጌታችን በግልጽ እንዳስቀመጠው በኋለኛው ዘመን “ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት” እንደሚነሱና “ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ” በማለት የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት የተናገረውን በጥንቃቄ ማስተዋሉ ከጥፋት ለመጠበቅ ያስችላል (ማቴ. 24፡24)።

በዚህ ሁሉ ወጀብ ውስጥ በድል አድራጊነት ለመውጣትና ለመዳን የሚችለው “እስከ መጨረሻ የሚጸና” መሆኑን አምላካችን አብሮ መፍትሔውንም አስቀምጧል። ይህንን እስከመጨረሻ መጽናት የምንችልበትን ኃይል የምናገኘው ከጌታ ቃል ብቻ ነው። “እኔን ስሙኝ” ባዩ በበዛበት፤ የሃሰተኛው ቁጥር የጻድቃንን ሊውጥ ባለበት ዘመን በብርሃን መጓዝ የምንችልበትን ዘዴ አለ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለእግራችን መብራት፤ ለመንገዳችን ብርሃን ስናደርገው ብቻ ነው (መዝ. 119፡105)።

ቃሉን በትጋት በማጥናት፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ከስህተት መጠበቅ እንችላለን። “የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፤ የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፥ ልብንም ደስ ያሰኛል፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል። የእግዚአብሔር ፍርሃት ንጹሕ ነው፤ ለዘላለም ይኖራል፤ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው። ከወርቅና ከክቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል፤ ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል። ባሪያህ ደግሞ ይጠብቀዋል፤ በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል” (መዝ. 19፡7-12)።

“እርሱም (ጌታ ኢየሱስ) በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፦ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት”።

“ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ”። ጊዜው

(ጥበበሥላሴ መንግሥቱ)

# የእውነተኛ ነቢይ መለኪያ መሥፈርቶች

ነቢያት በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዘመን ትልቅ ሚና ይጫወቱ ነበር። በዘመናችንስ ነቢያት ያስፈልጋሉ? የትንቢት ስጦታ አስፈላጊነት ምን ያህል ነው? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ነቢያት ብቻ ናቸው ትንቢትን ይናገሩ የነበሩት ወይስ እስከ ምድር ታሪክ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔር ነቢያትን ያስነሳል? እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ነቢይ እንዴት ነው መለየት የምንችለው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መልሶችን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ይዘን ቀርበናል።

## የትንቢት ስጦታ አስፈላጊነት

በአንድ ወቅት የይሁዳ ንጉስ ኢዮሣፍጥ በጭንቀት ላይ ነበር። በጠላት ወታደሮች በመከበቡ ምክንያት የነበረበት ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኖ ሳለ "ኢዮሣፍጥ እግዚአብሔርን ሊፈልግ ፊቱን አቀና በይሁዳም ሁሉ ፆም አወጀ" (2ዜና 20፡3)። ሕዝቡም ከእግዚአብሔር ምህረትንና ድልን ለማግኘት ወደ ቤተ መቅደስ ለጸሎት ይጎርፉ ጀመር።



በጸሎትም ሰዓት ኢዮሣፍጥ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። ከደረሰበትም ችግር እንዲያወጣው ስለፈለገ እንዲህ ብሎ ጠየቀው "አቤቱ የአባታችን አምላክ ሆይ በሰማይ ያለህ አምላክ አንተ አይደለህምን? የአሕዛብንስ መንግሥት ሁሉ የምትገዛ አንተ አይደለህምን? ኃይልና ችሎት በእጅህ ነው ሊቋቋምህ የሚችል የለም" (ቁ. 6)። በመቀጠልም "አምላካችን ሆይ አንተ አትፈርድባቸውምን? ይህን የመጣብንን ታላቅ ወገን እንቃወም ዘንድ አንችልም፤ የምናደርገውን አናውቅም ነገር ግን ዓይኖቻችን ወደ አንተ ናቸው" (ቁ. 12) ብሎ የምር ጸሎት አቀረበ።

በዚያን ጊዜ መላው ይሁዳ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ሳሉ የሕዚኤል የሚባል አንድ ሰው ተነሳና በፍርሃት ይንቀጠቀጥ የነበረውን ሕዝብ አበረታታ እንዲህም አላቸው፡- "ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ የእናንተ አይደለምና አትፍሩ፤ አትደንግጡም … እናንተ በዚህ ሰልፍ የምትዋጉ አይደላችሁም … ተሰለፉ ዝም ብላችሁ ቁሙ፤ የሚሆነውንም የእግዚአብሔርን መድኃኒት እዩ፤ እግዚአብሔርም ከእናንተ ጋር ነውና አትፍሩ፤ አትደንግጡም (ቁ. 15-17)።

በነጋታውም ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ወታደሮቹን ለማበረታታት እንዲህ አለ፤ "… በአምላካችን በእግዚአብሔር ታመኑ ትፀኑማላችሁ በነቢያቱም እመኑ ነገሩም ይሰላላችኋል (ይሳካላችኋል)" (ቁ. 20)።

ንጉሥ በነብዩ በየሕዝኤል ቃል ከመተማመኑ የተነሳ በጦርነቱ ላይ በግንባር ቀደምነት የታወቁትን ጀግና ወታደሮቹን በማድረግ ፈንታ የእግዚአብሔርን ክብርና ቅድስና ከፍ ከፍ የሚያደርጉትን መዘምራን እንዲቀድሙ አዘዘ። እነዚህም መዘምራን እምነት የሞላባቸውን መዝሙሮች በሚያሰሙበት ጊዜ እግዚአብሔር የይሁዳን ጠላቶች እርስ በእርሳቸው እንዲጨፋጨፉና አንዱ የራሱን ወገን እንዲገድል አደረገ። የታሪኩም መጨረሻ እንደሚነግረን "… ያመለጠ ሰው አልነበርም" (ቁ. 24)።

በኢዮሣፍጥ ዘመን ነቢዩ የሕዚኤል የእግዚአብሔር አፍ ነበር። በመፅሐፍ ቅዱስ አባባል "ነቢይ" ማለት ከእግዚአብሔር መልዕክትን ተቀብሎ ለሕዝቡ የሚያስተላልፍ ሰው ማለት ነው። ነቢያት ትንቢት ይናገሩ የነበረው በራሳቸው ሥልጣን ተነሳስተው አልነበረም። "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ" (2ጴጥ. 1፡21)።

በተጨማሪም ስለ ነቢያት በ1ኛ ሳሙኤል 9፡9 ላይ እንዲህ የሚል ጥቅስ እናገኛለን፡- "ዛሬ ነቢይ የሚባለው ቀድሞ 'ባለራዕይ' ይባል ነበርና አስቀድሞ በእስራኤል ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፡- 'ኑ ወደ ባለራዕይ እንሂድ' ይል ነበር"፤ "ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም" (አሞጽ 3፡17)።

በአዲስ ኪዳንም ውስጥ የትንቢት ስጦታ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ በመሆን አስፈላጊውን ቦታ ይዞ እናገኘዋለን (ሮሜ 12፥6፤ 1ቆሮ 12:28፤ ኤፌ. 4፡11)። ምዕመናን በተለይ ይህንን ስጦታ ለማግኘት እንዲጥሩ ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "... መንፈሳዊ ስጦታን ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ" (1ቆሮ. 14፡1) በማለት ይመክራል።

በአዲስ ኪዳን ዘገባ መሠረት የትንቢት ስጦታ የተሰጣቸው ነቢያት፡-

1. ቤተክርስቲያንን በመገንባት ተካፋይነት ነበራቸው (ኤፌ. 2፡20)፤
2. ቤተክርስቲያን ወንጌልን እንድታስፋፋ ያደፋፍሯት ነበር (ሐዋ. 13፡1-2፣ ሐዋ. 16፡6-10)፤
3. ቤተክርስቲያንን ያንፁ ነበር (1ቆሮ. 14፡3-4፣ ኤፌ. 4፡12)፤
4. ቤተክርስቲያንን ከሃሰት ትምህርት ይጠብቋት፣ የምዕመናንንም አንድነት ያጠነክሩ ነበር(ኤፌ.4፡14)፤
5. ምዕመናንን ወደፊት ከሚደርሱባቸው ችግሮች ያስጠነቅቁ ነበር (የሐዋ. ሥራ 11፡27-30፣ ሐዋ. 21፡ 4፣ 10፣ 14)፤
6. በቤተክርስቲያን ውስጥ መሠረታዊ ትምህርቶችን በተመለከተ ክርክር ሲኖር እውነተኛውን ትምህርት ግልፅ በማድረግ ውሳኔ ያስተላልፉ ነበር (ሐዋ. 15፡32)፤

## ሁሉን ፈትኑ፣ መልካሙን ያዙ

የምድር ታሪክ የሚገባደድበት የመጨረሻው ዘመን ሲደርስ፣ ማለትም ጌታ ኢየሱስ ቃል በገባበት መሠረት ዳግም የሚመለስበት ጊዜ ሲቃረብ፣ ብዙ "እኔ ክርስቶስ ነኝ" ባዮች በኢየሱስ ስም እንደሚመጡና ብዙዎችን እንደሚያስቱ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፤ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' እያሉ በስሜ ይመጣሉና፣ ብዙዎችንም ያስታሉ" (ማቴ. 24፡4-5)። እነዚህ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ እንደሚያሳዩም የናዝሬቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ ተናግሯል (ማቴ. 24፡24)።

የእነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት ተአምር፣ ምልክትና ድንቅ ነገሮች የማሳየት ችሎታ እውነተኛ ነቢያት ስለመሆናቸው አያረጋግጥም። "እውነተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ ነቢያትን እንዴት መለየት እንችላለን?" የሚለው ጥያቄ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አንገብጋቢና ወቅታዊ የሆነበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ደግነቱ፣ እጅግ በጣም የሚወደን አምላክ፣ በጠላት ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባ ስለፈለገ "እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ" በማለት ክፉውንና በጎውን፣ እውነቱንና ሐሰትን፣ ከጌታ የሆነውንና ከዲያቢሎስ የሆነውን የምንለይበትን መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል። እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ በውስጣችን እንዲሆን ስንጋብዘው፣ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራን የተስፋ ቃል ሰጥቶናል።




ሐዋርያው ጳውሎስም "ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ" በማለት ይመክረናል። ማለትም፣ በዘመናት ሁሉ ነቢያቶች ይኖራሉ ነገር ግን እነርሱ በርግጥ ከእግዚአብሔር ይሁኑ ወይም አይሁኑ ፈትኑ ማለቱ ነው። በመሆኑም፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ፣ እውነተኛ ነቢያትንና ሐሰተኛ ነቢያትን የምንለይባቸውን መሥፈርቶች ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን፡-

**1. ነቢዩ የሚናገረው ትንቢት ሁልጊዜ ይፈጸማል፡-** "ነገር ግን ስለ ሰላም ትንቢት የተናገረ ነቢይ እግዚአብሔር በእውነት እንደላከው የሚታወቀው የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም ነው" (ኤር. 28፡9)። "አንተም በልብህ፣ 'እግዚአብሔር ያልተናገረውን መልእክት እንዴት ማወቅ እንችላለን?' ብትል፣ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም የተናገረው ካልተፈጸመ ወይም እውነት ሆኖ ካልተገኘ፣ መልእክቱ እግዚአብሔር የተናገረው አይደለም። ያ ነቢይ በድፍረት ተናግሮታልና እርሱን አትፍራው" (ዘዳ. 18፡21-22)። እዚህ ላይ ነቢዩ

ዮናስ “በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች” በማለት የተናገረው ትንቢት አለመፈጸሙን ልብ ይሏል (ዮናስ 3፡4)። ትንቢቱ ያልተፈጸመው ዮናስ ሃሰተኛ ነቢይ ስለነበር ሳይሆን የነነዌ ሰዎች ኃጢአታቸውን ስለተናዘዙ ነው።

**2. እውነተኛ ነቢይ ራሱን ሳይሆን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ያደርጋል፣** ክብሩን ለራሱ ለነቢዩ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ይሰጣል፡- “የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል” (ዮሐ. 16፡13-14)። “ዮሐንስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል … እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል” (ዮሐ. 3፡30)።

**3. እውነተኛ ነቢይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል የበሰጠ ለማስረዳት/ለማስተማር፣ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ጥቅስን ከጥቅስ ጋር እያጣቀሰ ያስተምራል እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን በዘፈቀደ ወይም ራሱ እንደተመቸው አይተረጉምም፡-** “ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ የሚተረጐመው አይደለም፤ ምክንያቱም ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም“ (2ኛ ጴጥ. 1፡20-21)።

**4. እውነተኛ ነቢይ ኃጢአትን አያደባብስም፣ ኃጢአትን በስሙ ጠርቶ ይገስጻል፡-** “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ሕዝቤን የሚያስቱ ነቢያት፣ ሰው ሲያበላቸው፣ ‘ሰላም አለ’ ይላሉ፤ ሳያበላቸው ሲቀር ግን፣ ጦርነት



ሊያውጁበት ይነሣሉ። … እኔ ግን፣ ለያዕቆብ በደሉን፣ ለእስራኤልም ኃጢአቱን እነግር ዘንድ ኃይልን፣ በእግዚአብሔር መንፈስ፣ ፍትሕና ብርታት ተሞልቻለሁ“ (ሚክያስ 3፡5፤8)። “በኃይል ጮኽ፤ ምንም አታስቀር፤ ድምፅህን እንደ መለከት አሰማ፤ ለሕዝቤ ዐመፃቸውን፣ ለያዕቆብም ቤት ኃጢአታቸውን ተናገር“ (ኢሳ. 58፡1)። “መጥምቁ ዮሐንስም ‘መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ’ እያለ ህዝቡን ወደንስሃ ሲያደም ነበር። ሕዝቡም ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ይጠመቁ ነበር“ (ማቴ. 3፡1፤2፤6)።

**5. እውነተኛ ነቢይ የፍርድ ሰዓት እንደደረሰ (እንደተቃረበ)፣ ሰዎች ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃል፡-** “ምድር እንደ ሰካራም ዞረባት፤ ነፋስ እንደሚወዘውዘውም ጐጆ ሆነች፣ የዓመጿ ሸክም ከባድ ስለ ሆነ ትወድቃለች፤ እንደ ገናም አትነሣም። በዚያ ቀን እግዚአብሔር፣ በላይ በሰማያት ያሉትን ኀይሎች፣ በታችም በምድር ያሉትን ነገሥታት ይቀጣቸዋል” (ኢሳ. 24፡20-21)።

**6. እውነተኛ ነቢይ ቤተክርስቲያንን ያንጻል፣ ያበረታታል፣ ያነቃቃል፣ በመንፈሳዊ ሕይወት እንድታድግ ያግዛታል፡-** “ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለማበረታታትና ለማጽናናት ለሰው ይናገራል። በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል“ (1ኛ ቆሮ. 14፡3-4)።

**7. የእውነተኛ ነቢይ መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፈው ቃል ጋር ይስማማል እንጂ አይቃረንም፡-** “ወደ ሕጉና ወደ ምስክር ቃሉ ሂዱ! እነርሱም እንዲህ ያለውን ቃል ባይናገሩ የንጋት ብርሃን አይበራላቸውም” (ኢሳ. 8፡20)። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔርን ሕግና ምስክር የሚያቃልል ነቢይ ከእግዚአብሔር የተላኩ ነኝ ማለት አይችልም። እንዲያው ጥቅሱ የሚለው በእግዚአብሔር ሕግና ምስክር መሠረት የማይናገሩ ከሆነ ብርሃን

በውስጣቸው ስለሌላቸው ነው። በእንግሊዝኛ እንዲህ ይላል “To the law and to the testimony! If they do not speak according to this word, it is because there is no light in them” (NKJV).

**8. እውነተኛ ነቢይ ክርስቶስ በሥጋ እንደተገለጠ ይናገራል፣ ያስተምራል:-** “ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ” (1ኛ ዮሐ. 4፡1-3)። ስለዚህ ነቢያት ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር እንደሚመጣ ማመን፣ እንዲሁም ስለ እርሱ መስበክና ማስተማር አለባቸው።

**9. እውነተኛ ነቢይ ትሁት ነው ራስወዳድ አይደለም፤ ይህም በፍሬው ይታወቃል:-** “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?” (ማቴ. 7፡15-16)። የነቢያት ሕይወት (ፍሬ) ከመጸሐፍ ቅዱስ ጋር መስማማት ይኖርበታል (ማቴ 7፡1 8-21 እና ገላ 5፡19-23)። “የትንቢት ስጦታ አለኝ” የሚል ማንኛውም ሰው እነዚህን መለኪያዎች ካሟላ፣ በርግጥ መንፈስ ቅዱስ ለእርሱ የትንቢት ስጦታን እንደሰጠው ማመን፣ በመልዕክቱም መታመን ይቻላል።



**10. እውነተኛ ነቢይ ለእግዚአብሔር ቃልና ለእግዚአብሔር ሕግ ይታዘዛል:-** “ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፥ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል” (ዘዳ. 18፡18)። “እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው” (ሐዋ. 5፡32)።

**11. እውነተኛ ነቢይ የነቢይነት አገልግሎትን በነጻ ይሰጣል፣ ገንዘብ አይቀበልም:-** “ዳንኤልም ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ ‘ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ፤ ሽልማቶችህንም ለሌላ ሰው ስጥ፤ ይሁን እንጂ ጽሕፈቱን ለንጉሡ አነባለሁ፤ ትርጒሙ ምን እንደሆነም እነግረዋለሁ’” (ዳንኤል 5፡17)። “ወዮላቸው፣ በቃየን መንገድ ሄደዋል፤ ለገንዘብ ሲስገበገቡ በበለዓም ስሕተት ውስጥ ወድቀዋል፤ በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋል” (ይሁዳ 1፡11)።

## ማጠቃለያ

አንድ ማስተዋል የሚገባን ነገር አለ። ከላይ በተዘረዘሩት በእነዚህ መሥፈርቶች በአንዱ ወይም በሁለቱ ብቻ አንድን ሰው ትክክለኛ ወይም ሃሰተኛ ነብይ ነው ማለት አንችልም። ለምሳሌ ዮናስ ከእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ ነበር። የተሰጠውም መልዕክት “በሦስት ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች” የሚል ነበር (ዮናስ 3፡4)። ነገር ግን የነነዌ ሰዎች ንስሐ በመግባታቸውና ኃጢአታቸውን በጾምና ጸሎት በመናዘዛቸው ከሚመጣባቸው ቁጣ ዳኑ። ዮናስ የተናገረው ትንቢት ያልተፈጸመው በዮናስ ሃሰተኛ ነቢይነት ምክንያት ሳይሆን በአምላክ ቸርነትና ምህረት ነው። ስለዚህ ይህ ነቢዩን ሃሰተኛ አያስብለውም።

እንግዲህ ውድ አንባቢያን፡- በዚህች አጠር ባለች ጽሁፍ አማካኝነት የእውነተኛ ነቢይ መለያ መስፈርቶች ምን እንደሆኑ በመጠኑም ቢሆን እንዳስተዋላችሁ ተስፋ አለኝ። መጽሐፍ ቅዱስ “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ” (ኢሳ. 54፡13) ስለሚል፣ እናንተ እራሳችሁ በግላችሁ ቃሉን የበለጠ በመመርመር በዘመናችን እንደ አንበጣ የተስፋፉትን ሐሰተኛ፣ አታላይ እና ዘራፊ ነቢያት እንድትለዩ እንዲሁም ከእነርሱ እንድትጠበቁ በትህትና እና በወንድማዊ ፍቅር እማጸናችኋለሁ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካላችሁ በገጽ 3 ላይ በሚገኘው አድራሻችን ልትልኩልን ትችላላችሁ። ዜጠ

(ዳዊት መሐሪ)

# ነቢያት፤ ደሮና ዘንድሮ

የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ በሰብዓዊ ዘር እና በፈጣሪው መካከል ትልቅ የግንኙነት ችግር በመፈጠሩ የክህነትና የነቢያት አገልግሎቶች እንደ መፍትሔ መተግበር ጀመሩ። የክህነት አገልግሎት ማለት ኃጢአት ይቅር እንዲባል የሰው ልጅ መስዋዕት ይዞ ወደ አምላክ እንዲያቀርብ የተዘረጋ ሲሆን የነቢያት አገልግሎት ደግሞ ከአምላክ የሚመጣውን መልዕክት ወደ ሰብዓዊ ዘር የሚያደርስ መስመር ነበር። እነዚህ ሁለት አገልግሎቶች በሙሴና በአሮን አገልግሎት በግልጽ ተወክለው ይታያሉ። አሮን ኃጢአተኛውን ለይቅርታ ወደ አምላክ የሚያቀርበውን የክህነት አገልግሎት ሲወክል፤ ሙሴ ደግሞ ከአምላክ ወደ ሰው መልዕክት የሚያደርሰውን የነቢያት አገልግሎት ይወክላል። እንግዲህ ነቢይ ብለን የምንጠራው ሰውየውን ሲሆን፤ የሚናገረውን መልዕክት ደግሞ ትንቢት ብለን እንጠራዋለን። የዚህ ጽሑፍ ትኩረት የድሮውንና የዘንድሮውን የነቢያት አገልግሎት ማነፃፀር ይሆናል።

### ነቢይ ማነው?

“ነቢይ” የሚለው ቃል መሰረታዊ መነሻው “ናቡ” ከሚለው የአካዳውያን ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙ “ማስታወቅ”፣ “ማወጅ”፣ “አዋጅ መንገር” ማለት ነው። በዕብራይስጥ ደግሞ “ነቢይ” የሚለው ቃል “ነቢ” ከሚለው የተገኘ ነው። በተጨማሪ በብሉይ ኪዳን ውስጥ “ሮኤህ” እና “ሆዜህ” የተባሉ ሁለት ቃላት የነቢይን አገልግሎት



ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውለዋል።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የነዚህ ሁለት ቃላት ትርጉም በቅደም ተከተል “ተመልካች” እና “ባለራዕይ” የሚል ነው። እነዚህ ሦስቱም የዕብራይስጥ ቃላት ሁሉም በ1ዜና 29፡29 ላይ ተጠቅሰው እናነባለን። በብሉይ ኪዳን “ነቢይ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት “ተመልካች” የሚለው ቃል አገልግሎት ላይ እንደዋለ ይነገራል። እየቆየ ግን ይህ ቃል “ነቢይ” በሚለው ተተካ። ከዚህ ሌላ “ነቢያት” ባብዛኛው “የእግዚአብሔር ሰው” በሚል ይጠሩ የነበረ ሲሆን በቡድን ደግሞ “የነቢያት ልጆች” በመባል ይጠሩ ነበር (1ነገ. 17-2፤ነገ. 10)። ስለዚህ በዕብራይስጥ “ነቢይ” ማለት የተገለጠለትን፣ የታየውን ወይም የተመለከተውን የአምላክ ሃሳብ ለሰው ልጆች የሚያውጅ ወይም የሚያሳውቅ ሰው ማለት ነው።

ወደ ግሪኩ ስንመጣ “ነቢ” (נָבִיא) የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል “ፕሮፌተስ” (προφήτης) በሚል ቃል ተርጉሞታል። የዚህም ቃል ቀጥተኛ ትርጉም “ሌላውን ወክሎ የሚናገር” ማለት ሲሆን “የአምላክ ቃል አቀባይ” ወይም “በአምላክ ፈንታ ሆኖ የሚናገር” ወይም “የአምላክን ሃሳብ ለሰዎች የሚተረጉም” ማለት ነው። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የዚህ የግሪክ ቃል ወደ እንግሊዝኛ ተወስዶ “ፕሮፌሲ” (ትንቢት) ተብሏል። ይህም “የወደፊቱን የሚናገር” የሚል ሃሳብ የያዘውን “ፕሪዲክሽን” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሲሆን የቃሉ ትርጉም ግን በዚህ ብቻ ሳይገደብ “ኢንተርፕሪቴሽን” (ትርጉም፤ ፍቺ) የሚለውንም ያካተተ ነው። ወደ አማርኛ ስንመለሰው “መተርጎም” ማለት ሲሆን ይህም ነቢዩ ከአምላክ የተቀበለውን ቃል (ሃሳብ) ሰዎች በሚገባቸው መልኩ ማስተላለፍ የሚለውን ሃሳብ ያካተተ ነው።

ስለዚህ በሌላ አባባል “ፕሮፌሲ” የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ሙሉ ሃሳቡን ለመረዳት “ፕሪዲክሽን” እና “ኢንተርፕሪቴሽን” የተባሉት ሁለት ቃላት ማገናኘት የግድ ይላል። የእነዚህ ቃላት ትርጉምም ነቢይ ማለት የወደፊቱን የሚተነብይና ተጨማሪ ከአምላክ የተገለጸውን ፈቃድ ተርጉሞ የሚያስተምር፣ የሚያውጅ ወይም የሚያብራራ ማለት ነው።

## የነብያት አገልግሎት ታሪካዊ ዳራ

መጽሐፍ ቅዱስ በሦስት ዓይነት መንገድ እግዚአብሔር ራሱን ለነቢያት እንደሚገልጽ ያስረዳል። እነርሱም 1ኛ በሕልም፣ 2ኛ በራዕይ ሲሆን፣ 3ኛው ደግሞ በቀጥታ በድምጽ ወይም በፊት ለፊት ንግግር መሆኑን በዘኍልቁ ላይ እንረዳለን (ዘኍ. 12:5–8)። ሦስተኛው የግንኙነት መንገድ ከፍተኛው የመገለጥ ደረጃ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚያስረዳን በጥንት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው ለሙሴ ብቻ ነበረ።

ከኢያሱ እስከ ካህኑ ኤሊ ዘመን ድረስ እግዚአብሔር እንደ ሙሴ ዘመን በራዕይ አልተናገረም። በተለይም በመሳፍንት ዘመን የክህነት አገልግሎቱ እየተዳከመ በመምጣቱ፣ ከካህናቱ የብቃት ሞራል ከፍ ያለ የክህነት አገልግሎት ሕዝቡ ማግኘት አልቻለም ነበር። ስለዚህ ይህንን ክፍተት የሚሞላ ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት አስፈለገ። በዚህም ምክንያት ለሕዝቡ እግዚአብሔርን መፍራት የሚስተምርና ወደ ንስሐ የሚጠራ የነቢያት አገልግሎት በካህኑ ሳሙኤል ተጀመረ። በመጀመሪያ በሙሴ አገልግሎት ይታወቅ የነበረው ይህ የነቢይ አገልግሎት ሳሙኤል እንደገና አነቃቃው። ቀደም ሲል ሙሴ “ጌታ እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል” ብሎ ስለተነበየ፣ ይህ የነቢይ አገልግሎት በጣም ሲጠበቅ ቆይቷል (ዘዳ.13:1፣ 18:18፣ 20–22)። ይህ አገልግሎት ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ሕግ እንዲመለሱ የሚጠራና ወደ ትልቅ የሞራል ከፍታ እንዲደርሱ የሚያደርግ አገልግሎት ነው።



ሳሙኤልም የነቢያትን አገልግሎት ለማጠናከርና ለማስፋፋት በተለያዩ ቦታዎች የነቢያት ትምህርት ቤት ከፈተ። እነዚህም በራማህ (1ሳሙ. 19:19–20)፣ በቤቴል (2ነገ. 2:3)፣ በኢያሪኮ (2:5)፣ በጊልጌል (4:38) እና በሌሎች ቦታዎች (6:1) ነበሩ። እጩ ነቢያቱ በዋነኛነት ይማሩ የነበረው አምስቱን የሙሴ መጽሐፍት (ዘፍጥረት፣ ዘጸዓት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኍልቁና ዘዳግም) እና ትርጓሜያቸው (ፍቺያቸው) እንደሚሆን አያጠራጥርም። በተጨማሪም ሙዚቃና ቅኔ ወይም ሥነጽሁፍ ይማሩ ነበር (ዘጸ. 15:20፣ መሳ. 4:4-5)። ካህን ለመሆን የግድ ከሌዊ ዘር መወለድን የሚጠይቅ ሲሆን ነቢይ ለመሆን ወይም ወደ ነቢያት ት/ቤት ለመግባት ግን እስራኤላዊ መሆን ብቻ በቂ ነበር።

## ነቢይነትና አገልግሎቱ

ነቢይ የመሆን ጥሪ ወደ ግለሰቡ የሚመጣው በሁለት መልኩ ነበር። የመጀመሪያው ልክ እንደ ሙሴና ኤልያስ ቦታቸውን የሚተኩትን መርጠውና አሰልጥነው እጃቸውን በመጫን ጥሪውን በማስተላለፍ ነው። ሁለኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ በቀጥታ ጥሪው በግል ደርሷቸው ወደ አገልግሎቱ እንደ ሳሙኤል የሚገቡ ናቸው። የነቢይነት ጥሪ ለወንዶች ብቻ የሚመጣ ሳይሆን በርካታ ሴቶችም በዚህ አገልግሎት ውስጥ የታቀፉ ነበሩ። እንደ ማስረጃም የሙሴ እህት ሚርያምንና ዲቦራን መጥቀስ ይቻላል (ዘጸ. 15:20-21፤ መሳ. 4:4-10፤ 6:1-10)።

ልክ በጽዮን ቅጥር ላይ የተመደቡ ጠባቂዎች አደጋ ሲመጣ መለከታቸውን በመንፋት ሕዝቡን እንደሚያስጠነቅቁ ነቢያትም አደጋን ሲመለከቱ ሕዝቡን ማስጠንቀቅ ይጠበቅባቸው ነበር። ዋና አገልግሎታቸው ሰዎችን ስለ ኃጢአታቸው መዝለፍ፣ መገሰጽ፣ መውቀስ፣ ሊመጣ ስላለው መለኮታዊ ቅጣት ማስጠንቀቅና ወደ ንስሐ መጥራት ነው። ሌላው ደግሞ ሕዝቡን ማጽናናትና ስለ እግዚአብሔር ይቅርታ ማወጅ ተጨማሪው የነቢያት ሥራ ነበር።

“በኃይልህ ጮኽ፥ አትቈጥብ፥ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ፥ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብ ቤትም ኃጢአታቸውን ንገር” (ኢሳ. 58፡1፤ ሕዝ. 22፡2፤ 43፡10፤ ሚክ. 3፡8)። “አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ ይላል አምላካችሁ። ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ፤ የተቀጠረችበት ወራት እንደ ተፈጸመ፥ ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ፥ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደ ተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ” (ኢሳ. 40፡1–2)።

እነዚህ ነቢያት በሚናገሩት ትንቢት እግዚአብሔር በጸጋው ለእስራኤል ልዩ ፍቅርና ዓላማ እንዳለው እየገለጹ፤ የእርሱን ፈቃድ፣ ፍርዱንና፣ ጽድቁን እያወጁ፤ ለእውነት በጥብቅና ከመቆማቸው ባሻገር፤ ከመስዋዕት ሥርዓት ይልቅ የሞራል ልዕልና እንደሚበልጥ ከፍ ባለድምጽ መስክረዋል። በአገልግሎታቸው ስለወደፊት ከመተንበይ ባሻገር በሙሴ መጻሕፍት ላይ ተመርኩዘው ሕዝቡ በየቀን ኑሮው እንዴት ህጉን በሥራ መተርጎም እንዳለበት



በማሰብ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የአምላክን ፈቃድ ማወጅ ነበር። ስለዚህ አገልግሎታቸው የሞራል ትምህርትን ያቀፈና የወደፊቱን የሚተነብይ ነበር ለማለት እንችላለን።

ነቢያት እንደሚገጣጣቸው ሁኔታ የአኗኗር ዘይቤያቸውም የተለያየ ነበር። አንዳንዶቹ ያገቡ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ያላገቡ ነበሩ። ለእግዚአብሔር ቃል ካላቸው ታማኝነት የተነሳ በሕይወታቸው አብዛኞቹ ሀብት ለማፍራት ሳይችሉ ሳያገቡ፣ በድህነትና በስደት ተንገላተዋል። ከኤልያስና ከመጥምቁ ዮሐንስ የአለባበስ መመሳሰል በስተቀር ሌሎቹ ሕዝቡ የሚለብሰውን ለብሰው፤ የሚበላውን በልተው ያገለግሉ ነበር።

### ነብያት በአዲስ ኪዳን

በአዲስ ኪዳን ውስጥም ይህ የነብያት አገልግሎት ከመንፈስ ስጦታዎች ውስጥ ተዘርዝሮ የሚገኝ ሲሆን ከሐዋርያነትን ስጦታ ጋር ተወራራሽነት ያለው የአገልግሎት ዘርፍ ነበር (1ቆሮ. 12፡ 28-30)። በአዲስ ኪዳን አንዳንድ የሐዋርያነት ስጦታ ያላቸው ሰዎች የነቢይነት ስጦታም ነበራቸው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የነቢይነት ስጦታ ያላቸውን ሰዎች አገልግሎት በማጥናት ፍራንክ ቢ ሆልብሩክ (Frank B. Holbrook) የተባሉ የሥነመለኮት ምሁር የነቢያትን አገልግሎት በስድስት የተለያዩ ዘርፎች ያጠቃልሉታል።

### በአዲስ ኪዳን የነበሩ ነቢያት፤

1. ነገሮች ከመሆናቸው በፊት ሊመጡ ያሉ አስቸጋሪ ወቅቶችን አስቀድመው አስጠንቅቀዋል (የሐዋ. ሥራ 11፡27-30፤ 20፡23፤ 21፡10-14)፤
2. በወቅቱ በነበረችው ቤተክርስቲያን አማካኝነት ወደ አህዛብ ወንጌል የማድረስ ጥሪ ተለኩሷል (የሐዋ. 13፡1-2) እንዲያውም የመጀመሪያዎቹ የወንጌል ሰባኪዎች የአገልግሎት ምሪትን ይቀበሉ የነበረው በዚህ ስጦታ አማካኝነት ነበር (የሐዋ. 16፡6-10)። በጳውሎስ ሁለተኛ ሐዋርያዊ ጉዞ ወቅት እንኳ ሲላስ የተባለ ነቢይ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ወንጌልን ለመሥራት ወጥቷል፤
3. በሐዋርያት ዘመን የአስተምህሮ ጭቅጭቅ በተነሳ ጊዜ አባላትን በእውነተኛው ትምህርት ለማጽናትና ለማደፋፈር ተግተዋል (የሐዋ. ሥራ 15፡32)፤
4. የቤተክርስቲያን አባላትን ያደፋፍሩ፣ ያጽናኑ እና ያንጹ ነበር (1 ቆሮ. 14፡3)፤
5. ከሌሎች የመንፈስ ስጦታ ካላቸው ጋር በመሆን የቤተክርስቲያን አባላትን ከስህተት ትምህርት ታድገዋል። የቤተክርስቲያን አንድነት በእውነተኛ እምነት ላይ ለመጠበቅ ተግተዋል (ኤፌሶን 4፡11-15)፤
6. ከሐዋርያት ጋር በመሆን ቤተክርስቲያናትን መሥርተዋል፤ “ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን” ተገልጧል (ኤፌ. 2፡20፤ 3፡5፤ 4፡11)።

እስካሁን ነብይ የሚለውን ቃል ትርጉም፣ የአገልግሎቱ ታሪካዊ ዳራና ዋና ትኩረት ምን እንደሆነ አይተናል፤ በአዲስ ኪዳን ደግሞ እንዴት በወንጌል ስርጭት ዙሪያ ነብያት ከፍተኛ ተሳትፎ እንደነበራቸው ተመልክተናል፤ በመቀጠል ደግሞ በዘመናችን ከሚገኙ ራሳቸውን "ነብይ" ብለው ከሚጠሩ ጋር ያለውን ንጽጽር እንመልከት።

## በድሮና በዘመናችን የሚገኙ "ነቢያት" ልዩነቶች

በዘመናችን ራሳቸውን "ነቢያት" ብለው በሚጠሩና መጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት በማለት በሚጠራቸው መካከል የሚታዩ ሰፊ ልዩነቶች አሉ። በሞራል ልዕልና፣ በመልዕክት አቀባበል፣ በገንዘብ መውደድ (ፍቅረንዋይ)፣ በተጠያቂነት፣ ራስን ከፍ ከፍ በማድረግ፣ በአደረጃጀት እና በሌሎች ጉዳዮች ስንመለከተው ልዩነታቸው በጣም ሰፊ ነው።

### ፍቅረንዋይ

ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ ጀኔራል ንዕማንን ሂድና በዮርዳኖስ ሰባት ጊዜ ታጠብ አለው። እርሱም ታጠበ ከለምጹም ነጻ። መፈወሱን ከተመለከተ በኋላም ብዙ ስጦታ ለነቢዩ አመጣ፤ በዚህን ጊዜ ነቢዩ ስጦታውን እንደማይቀበል ነግሮት ያመጣውን ስጦታ ንዕማን ይዞ ተመለሰ። ሆኖም ግን ግያዝ የተባለው የነቢዩ አገልጋይ ለዚህ ትልቅ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ፈውስ የገንዘብ ክፍያ መቀበል እንዳለባቸው ተሰማው። ይህንን ያስተዋለው ነቢዩ ኤልሳዕ ግን ግያዝን ከለከለው (2ነገ. 5፡15-27)።



የዘንድሮው "ነቢያት" ቢሆኑ ኖሮ ገንዘብ ከመውደዳቸው የተነሳ ዘይት በብልቃጥ እንደሚቸረቸሩት ሁሉ እያንዳንዱን የዮርዳኖስ ውሃ በሃይላድ ላስቲክ እየሞሉ አሽገው ይቸረችሩት ነበር። ግያዝ፣ ኤልሳዕ የተባለ የሥራ አለቃውን "ይሄ ቢዝነስ የማይገባው ነቢይ" ብሎ፤ መንገዱን አሳብሮና አቆራርጦ፣ ንዕማንን በማጭበርበር ምርጥ የሆኑ ልብሶችና ጥሬ ገንዘብ ተቀብሎ እንደመጣ የዘመኑ "ነቢያትም" በሌላቸው የነቢይነት ስጦታ ልክ እንደ ግያዝ ኪስ ያወልቃሉ፣ ይዘርፋሉ።

እነዚህ "ነቢያት" ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር መሆኑን ዘንግተውታል። "በነጻ እንደተቀበላችሁ በነጻ ስጡ" የሚለውን ምክር ረስተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብን ስለወደዱ "የበልዓምን መንገድ መርጠዋል" በማለት ይነግረናል። "ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤ እርሱ የዓመፃን ደመወዝ ወደደ፥ ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ" (2ኛ ጴጥ. 2፡15-16)።

### ተጠያቂነት

ብዙዎች የነቢይነትንና የሐዋርያነትን ማዕረግ የሚመኙትና "ነኝ" ብለው ራሳቸውን አታለው ሌላውንም ወደ ማታለል የሚገቡት ይህ የአገልግሎት ዘርፍ ተጠያቂነት የለውም ብለው ስለሚያምኑ ነው። በርግጥ ነቢይን ደፍሮ "ይህን ለምን ታደርጋለህ" ብሎ ማን ይጠይቃል? በተጨማሪም ራሳቸውን በሰው ዘንድ እንደ አምላክ ለመኮፈስም ስለሚፈልጉ ነው። ሰው መሆናቸውን ረስተው እንደ አምላክ ሆኖ መታየት እንዴት ያለ ታላቅ የገቢ ምንጭ መሆኑን አስበዋል።

ይህንን "ነቢያቱ" የሚያስገቡትን ገቢ የተገነዘበ አንድ ሰው ከፓስተሩ ጋር ስለ አገልግሎት እየተጫወቱ ሳለ፤ ፓስተሩ "ወንድሜ አንተን ስመለከትህ "የትዳር አማካሪነት" ስጦታ ያለህ ይመስለኛል" ቢሉት፤ ሰውየውም "የለም! የለም! ፓስተር እኔን ከወደዱኝ እንዲጸልዩልኝ የምፈልገው የትዳር አማካሪ እንድሆን ሳይሆን "ነቢይ" እንድሆን ነው" በማለት ተናገረ። ሰውዬው ይህንን ያለው በዘመናችን ከትዳር አማካሪነት ይልቅ ራሳቸውን

“ነቢይ” ብለው የሚጠሩ ሰዎች እጅግ የናጠጡ ሀብታም ሆነው ስለተመለከተ ነበር። “የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ” (ማር. 12፡40)።

የነቢይነት አገልግሎት ዘርፉ ግን “ፈትኑ”፣ “መርምሩ” በሚሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዞች የታጀበ ስለሆነ ተጠያቂነት የሌለበት አይደለም። ከተጠያቂነትም የሚያመልጥም የለም። ራስን ከተጠያቂነት በላይ እንደ ጳጳስ ማድረግ ያውም በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መሃል የማይቻል ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም ነው። “ወዮላችሁ! እናንት .... ከገሃነም ፍርድ አታመልጡም” (ማቴ. 23፡33)።

እንደሚታወቀው እነዚህ ራሳቸውን “ነቢያት” ብለው የሚጠሩ ሰዎች ቀድመው የነበሩበት ቤተክርስቲያን የተጠያቂነት አሠራር መኖሩ ስለማይመቻቸው ያንን ጥለው በመውጣት አዲስ ላቋቋሙት ድርጅት ራሳቸውን ሥራ አስኪያጅ በማድረግና በራሳቸው ስም የባንክ አካውንት በመክፈት የግላቸው የሆነ ቤተክርስቲያናትን የመሠረቱ ሲሆን በውስጣቸውም ከፍተኛ የሆነ የአደረጃጀትና የተጠያቂነት ችግር ያለባቸው ናቸው።

## በመገለጥ ሳይሆን በመረጃ ማገልገል

ድሮ ድሮ የመጽሐፍ ቅዱሶቹ ነቢያት “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል” የሚለውን ትንቢትም ሆነ ዕውቀት የሚቀበሉት ከእግዚአብሔር ዘንድ በመጣ ድምፅ፣ ራዕይ ወይም ሕልም ነበር። የዘንድሮዎቹ ግን በተለያየ ድብቅ በሆኑ መንገዶች የሚያገኙትን መረጃዎች “ልዩ መገለጥ” በማስመሰል በማጭበርበር ላይ ናቸው።



አንዳንዶቹ መረጃቸውን የሚያገኙት ከግለሰቡ አጠገብ ተደብቆ ባለ መቅረጸ ድምጽ፣ ሰው መጽሐፍ ቅዱሱ ወይም ቦርሳው ውስጥ ጽፎ እንዲያስቀምጥ የተደረገውን የጸሎት አደራ ዝርዝር በድብቅ በማንበብ፣ ወይም ዝርዝሩን ፎቶ አንስቶ ለ“ነቢዩ” በማቀበል፣ የግለሰቦቹን የፌስቡክ አካውንት በማጥናት ወይም በመሰለልና መረጃዎችን ለዚሁ በተመደበ ግለሰብ አማካኝነት ወደ “ነቢዩ” በመላክ ነው። መረጃዎቹን ከተቀበሉ በኋላ የግለሰቡ ስም፣ ሞባይል ቁጥር፣ የህመም ዓይነት፣ የትዳር ሁኔታ ምን እንደሚመስልና ተመሳሳይ ነገሮች በመድረክ ላይ ይጠራሉ። “በስሜ ሐሰተኛ ትንቢትን ይናገሩላችኋልና፤ እኔም አልላክኋቸውም” (ኤር. 29፡9)። “እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ ሐፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው” (ራዕይ 16፡15)።

“ተስማምተው ... ምን ያሉት አይሸትም” እንደሚባለው የአገራችን አባባል ሐሰተኛ ነቢያት በአገራችን ሥራቸውን እየሰሩ ያለው በቡድንና እርስበርስ በመደጋገፍ ነው። “ነቢይ” ነን ባዮቹ እርስበርሳቸው መረጃ ይለዋወጣሉ፤ የተለያየ የሥራ ድርሻ በተሰጣቸው ሰዎች ይደገፋሉ። እየሆነ ያለው ሁሉም ባለድርሻ የገንዘብ ተከፋይ ስለሆነ ምሥጢሩን ለማውጣት የተቸገረ መሆኑን ነው። በድብቅ ሲለማመዱ የቆዩትን ድራማዊ የአጋንንት ማስወጣትና የተለያዩ መገለጥ የሚመስሉ ድርጊቶችን በየስብሰባዎቻቸው በቲያትር መልክ በማቅረብ የሚደረግ የተደራጀ ማጭበርበርና ሌብነት ነው።

በቅርቡ አንዲት “ራዕይ ታይቶኛል ባይ” በወለንጪቲ ከተማ መቃብር ተቆፍሮ እንዲከፈት በማድረግ ከሞተ ሁለት ሳምንት የሆነውን የሁለት ወር ህጻን ልጅ አስከሬን “ከሞት እንዳስነሳ ራዕይ ታይቶኛል” በማለት መቃብር አስቆፍራ ነበር። በመቀጠልም እየጸለየችና “ተነስ!” እያለች ለበርካታ ሰዓታት ድምጽዋን በጩኸት ብታሰማም፤ አስከሬኑ ምንም አልሰማትም፤ አልነቃም፤ አልተንቀሳቀሰምም። “ነቢይቱም” በፈጸመችው ድርጊት ስታፍር ሁኔታውን ለፖሊስ ሪፖርት ያደረጉ በመኖራቸው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውላ ተገቢውን ቅጣት እንዳገኘች [ቢቢሲ አማርኛ 14 ጥር 2020 ዘግቧል]።



ከዚህ ድርጊት እነዚህ ራሳቸውን “ነቢይ” ብለው የሚጠሩ ሰዎች ሁለት ዓይነት መሆናቸውን እንማራለን። አንዳንዶቹ በርግጥ ራሳቸው ለዚህ አገልግሎት የተጠሩ መስሏቸው የሳቱና የተታለሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሆን ብለው ለማጭበርበር የሚሠሩና ድርጊታቸው የሐሰት መሆኑን የሚያውቁ ነገር ግን ገንዘብ ስለሚያስገኝላቸው ብቻ ሆን ብለው ብዙዎችን በማሳት ሥራቸው የተጠመዱ መሆናቸውን ነው።

አብዛኞዎቹ የዘንድሮ ነቢያት ራሳቸውን ከፍ ከፍ ማድረግ ይታይባቸዋል። እውነተኛ ነቢይ ከፍ የሚያደርገው ራሱን ሳይሆን እግዚአብሔርንና ቃሉን ብቻ ነው። በዘመናችን የምናያቸው “ነቢያት” ግን ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ ትላልቅ ፎቶዎቻቸውን በየመንገዱና በየአደባባዩ ይሰቅላሉ። በየቴሌቪዥኖቻቸው “ስለ ነቢዩ ምን ታስባለህ?” እያሉ ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። ነገርግን እንደ ዮሐንስ መጥምቁ ያለ እውነተኛ ነቢይ የሚለው “እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል” ነው (ዮሐ. 3፡30)።

ሌላው እነዚህ ራሳቸውን “ነቢይ” ብለው የሚጠሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልዕክት የሌላቸው መሆኑ ነው፤ አብዛኛው የመልዕክታቸው ትኩረት ስለ ድንቅና ስለ ተዓምር በመናገር ስሜትን መቀስቀስ፣ ማስደነቅ፣ ማስለቀስ ብቻ ነው። ምዕመኖቻቸው መረጋጋት ያልቻሉ በትምህርት ነፋስ ወዲህና ወዲያ የሚፍገመገም የውሃ ላይ ኩበት፣ ተንከራታች ሆነዋል። የነቢይነት ስጦታ የሚሰጠው ግን ምዕመናንን ለማነፅና ለማጽናት ነበር። “እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም” (ኤፌ. 4፡14)።

በርካታ የሚባሉት ቅድስና የጎደላቸው፣ ተሳዳቢዎች፣ ከሴቶች ጋር የሚሴስኑ፣ ዝሙትን በአካባቢያቸውና በዙሪያቸው ያነገሡ አጭበርባሪዎችና ፈሪኃ እግዚአብሔር የጎደላቸው ነፍሰ ገዳይ መሆናቸው በስፋት ይወራል፤ የጉዳቱ ሰለባዎችም ይህንኑ ይመሰክራሉ። እነዚህ ሆን ብለው በእግዚአብሔር ስም አቅደውና ተዘጋጅተው ለማጭበርበር የመጡ ናቸው። “ዳሩ ግን፦ ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ” (ራዕይ 2፡20)።

በኢየሱስ አገልግሎት የተፈወሱ ሰዎች ከተፈወሱ በኋላ ኢየሱስ “ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ” በማለት መፈወሳቸውን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ከካህኑ እንዲያገኙ ይነግራቸው ነበር። የዘንድሮ ሐሰተኛ ነቢያት ግን “ተፈውሳችኋል” ያሏቸውን ሰዎች መድኃኒታቸውን መውሰድ እንዲያቆሙ በማድረግ ሕመም እየተሰማቸው

እንኳን መድኃኒት አትውሰዱ የሚሉ ናቸው። ራሳቸውን ወደ ሐኪም ሄደው መፈወሳቸውን እንዲያረጋግጡ ምክር እንኳ አይሰጧቸውም። የታመሙት ሰዎችም ሐኪም ጋር ሳይሄዱ፣ "ተፈውሰሃል" የሚለውን "የነቢዩን" ቃል በመስማት ብቻ መድኃኒታቸውን መውሰድ እርግፍ አድርገው ትተው ለሞት የተዳረጉት ጥቂት አይደሉም።

አንድ ለቤተሰቤ ቅርብ የሆነ ሰው በጠና ይታመምና በባለቤቱ እየተረዳ "ነቢይ" ብሎ ራሱን የሚጠራ ሰው ስብሰባ ቦታ ይወሰዳል። በአምልኮ መሃል ይህ የታመመ ሰው በ"ነብዩ" ተጠርቶ በሰዎች መሃል እንዲቆም ተደረገ። ነቢዩ "ሞት አይሆንም!" "የሞት ቀንበር ተሰበረ!" ብሎ አስጨበጨበ፤ ተዘመረ፤ ታማሚውም ተጠየቀ፤ "አዎን፤ ሃኪም ሁለቱም ኩላሊቶችህ አይሠሩም ብሎኛል" አለ። "አዲስ ኩላሊት ይታየኛል"፣ "የሞት ቀጠሮ ተሻረ" "ዛሬ ቀኑ ነው ክብሩን ልታይ፣ ተፈውሰሃል፣ ነጋቲ ቡላ!" ብሎ አሰናበተው። ቤተሰቡም አምላክን አመሰገነ። ሆኖም ግን ሰውዬው ከበሽታው አልዳነም ነበረና ይህ የሃሰት ትንቢት በተነገረ በሁለተኛው ወር ሕይወቱ አለፈች።



የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን ይህንን "የሞት ቀጠሮ ተሻረ" የሚለውን ፊልም "ነቢዩ" እስከ ዛሬ ድረስ ከዩቲዩቡ ላይ አፍሮ እንኳን አለማንሳቱ ነው። ምክንያቱም በተጨማሪ ገና ሌሎችን ያጭበረብርበታል፤ ከዩቲዩቡ የሚያገኘው ክፍያ እንዲቀንስበትም አይፈልግም። ይህ ምን ዓይነት የሞራል ዝቅጠት ነው!? የቀድሞ ነቢያት ጋር ይታይ የነበረው የሞራል ልዕልና የት ሄደ!? "የሰው ልጅ ሆይ፥ ትንቢት በሚናገሩ በእስራኤል ነቢያት ላይ ትንቢት ተናገር፥ ከገዛ ልባቸውም ትንቢት የሚናገሩትን፦ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ በላቸው፤ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ምንም ሳያዩ የገዛ መንፈሳቸውን ለሚከተሉ ለሰነፎች ነቢያት ወዮላቸው!" እግዚአብሔር ሳይልካቸው፦እግዚአብሔር ይላል የሚሉ ሰዎች ከንቱ ነገርንና ውሸተኛ ምዋርትን አይተዋል፤ ቃሉም ይጠና ዘንድ ተስፋ አስደርገዋል። እኔም ሳልናገር፦እግዚአብሔር እንዲህ ብሎአል ስትሉ፥ ከንቱ ራእይን ያያችሁ ውሸተኛንም ምዋርት የተናገራችሁ አይደላችሁምን? ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ከንቱ ነገርን ስለ ተናገራችሁ ውሸተኛ ራእይንም ስላያችሁ፥ ስለዚህ፥ እነሆ፥ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር" (ሕዝ. 13፡2-8)።

ከሶስት ወይም ከአራት ዓመት በፊት ነው፤ ሌላው ደግሞ በቴሌቭዥኑ "ትንቢት" ይናገራል፤ በኢትዮጵያ ስላለው ወቅታዊ የፖለቲካ ችግር ነበር "የሚተነብየው"። እንዲህ አለ "በኦሮምያ ያለው የጸጥታ ችግር በቅርቡ ጸጥ ይላል"፤ እንዳነጋገሩ በሁለት በሶስት ሳምንት ውስጥ ችግሩ የሚፈታ ይመስል ነበር። ነገሩ ግን "ነቢዩ" እንደተናገረው ሳይሆን ቀርቶ የጸጥታው ችግር በየቀኑ እየጨመረ፣ እየጨመረ! ሄዶ መንግሥት ተለወጠ። አገሪቱ እንኳን ያኔ አሁን ድረስ የጸጥታ ማጣት ቁፈን አለቀቃትም። "ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው" (ዘዳ. 18፡22)።

## የማጠቃለያ ሦስት ማሳሰቢያዎች

ራሱን እያታለለ ለሚገኝ ሐሰተኛ ነብይ፡- “አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላል” (ገላ. 6፡3) እንደሚለው ቃሉ፤ መጀመሪያ ተረጋግተህ የእግዚአብሔርን ድምፅ እና ከገዛ ልብህ ወይም ከስሜትህ የሚመነጨውን ድምፅ መለየት ብትለማመድ ይበጃል። ነገር ግን ነብይ ሳትሆን ነብይ እንደሆንህ ከተሰማህ እጅግ ስተሃል፣ እጅግ ተታለሃል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስህን ጠንቅቀህ አጥና። እንደ “አኪማአስ” መልክትም ሳትቀበል፣ እንድትሄድም ሳትላክ አትሩጥ። “ትሮጥ ዘንድ ለምን ትወድዳለህ?” (2 ሳሙ. 18፡19-33) “ወዮላችሁ!” የሚለው ማስጠንቀቂያ ወደ ነፍስህ ደርሶ ከሆነ ንስሐ ግባ!

ሆን ብለው ለሚያጭበረብሩ “ነብያት” ደግሞ፡- የተናገራችሁት ትንቢት ስላልተፈጸመ ጴጥሮስ እና ይሁዳ በየተራ “ውኃ የሌለባቸው ምንጮች” (2 ጴጥ.2፡17) እና “በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው ደመናዎች” ናችሁ በማለት ገልጸዋቿችኋል። በሌላ አነጋገር ባዶ ተስፋ ሰጪዎች ናችሁ ማለታቸው ነው። “እነዚህ ሰዎች በፍቅር ግብዣችሁ ላይ ያለ አንዳች ኃፍረት ከናንተ ጋር ቀርበው የሚበሉ ነውረኞች ናቸው” ይለናል (ይሁዳ 12)። ያዘጋጃችሁት የነጻ መውጣት ዝግጅት ማጭበርበር ነው፤ “ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው፡- አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል” (2 ጴጥ. 2፡19)፤ ስለዚህ ንስሐ ግቡ! ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ!

**በመጨረሻም ለምዕመን፡-** እነዚህን ሐሰተኛ ነቢያት “አትፍራው” (አትፍራቸው) በማለት አምላክ እንዳንፈራቸው ያደፋፍረናል። “ከሐሰተኞች ነብያት ተጠንቀቁ” በማለትም ያሳስበናል (ማቴ. 7፡15)። መረጃ ከፌስቡክ እየለቃቀመ በሚተነብይ ሐሰተኛ በቀላሉ ከተታለልን፤ እሳትን ከሰማይ የሚያወርደው ሐሰተኛው ነብይ ሲመጣ እንዴት ልንሆን ነው? “ከእግረኞች ጋር ሮጠህ እነርሱ ካደከሙህ፣ ከፈረሰኞች ጋር እንዴት ልትወዳደር ትችላለህ?” (ኤር. 12፡5)። አምላክ በዘመናችን ሰይጣን በዘረጋው ወጥመድ ውስጥ ወድቀን እንዳንጠፋ ሁላችንንም ይጠብቅ! “ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ”(1 ቆሮ. 10፡12)።

(ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ)

## ዋቢ መጻሕፍት


Achtemeier, Paul J. Publishers Harper & Row and Society of Biblical Literature, *Harper's Bible Dictionary*, Includes Index., 1st ed. (San Francisco: Harper & Row, 1985), 826.

Arndt, William. Frederick W. Danker and Walter Bauer, *A Greek-English Lexicon of the New Testament and Other Early Christian Literature*, "Based on Walter Bauer's Griechisch-Deutsches Wrterbuch Zu Den Schriften Des Neuen Testaments Und Der Frhchristlichen [Sic] Literatur, Sixth Edition, Ed. Kurt Aland and Barbara Aland, With Viktor Reichmann and on Previous English Editions by W.F. Arndt, F.W. Gingrich, and F.W. Danker.", 3rd ed. (Chicago: University of Chicago Press, 2000), 122.

Bromiley, Geoffrey W. *The International Standard Bible Encyclopedia, Revised* (Wm. B. Eerdmans, 1988; 2002), 1:192-195, 3:986-1004.

Brown, Colin.*The New International Dictionaryof New Testament Theology*. Edited by Colin Brown.Grand Rapids: Zondervan, 1976. 1:126-137.

Chantry, Walter J. *Signs of the Apostles: Obseveations on Pentecostalism Old and New*. Pennsylvania: The Banner of Truth Trust. 1973, 1976.

Elwell, Walter A. and Walter A. Elwell. *Evangelical Dictionary of Biblical Theology*. electronic ed. Baker reference library; Logos Library System. Grand Rapids: Baker Book House, 1997, c1996.

Enns, Paul P. *The Moody Handbook of Theology*. Chicago, Ill.: Moody Press, 1997, c1989.

Holbrook, F. B. (n.d.). *The Biblical Basis for a Modern Prophet*. Retrieved from https://adventistbiblicalresearch.org/materials/adventist-heritage-bible-prophecy/biblical basis-modern-prophet

Horn, Siegfried H. *Seventh-day Adventist Bible Dictionary*. Revised edition. Commentary Reference Series. Washington, D.C.: Review and Herald Publishing Association, 1979.

Ryrie, Charles Caldwell. *Basic Theology: A Popular Systemic Guide to Understanding Biblical Truth*. Chicago, Ill.: Moody Press, 1999.

Unger, M. F., Harrison, R. K., Vos, H. F., Barber, C. J., & Unger, M. F. (1988). *The new Unger's Bible dictionary*. Revision of: Unger's Bible dictionary. 3rd ed. c1966. (Rev. and updated ed.). Chicago: Moody Press.

Wood, D. R. W. *New Bible Dictionary*. InterVarsity Press, 1996, c1982, c1962

# ከነቢይም ሁሉ የሚበልጥ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ሰዎች ለመዳን የልብ ዝግጅት ማድረግ ነበረባቸው። የሰው ተፈጥሯዊ ራስወዳድነት በሰማያዊ ፍቅር፤ ትዕቢት ደግሞ በትህትና መተካት ነበረበት። ሰውን ከአምላክ የለየው የልብ መደንደን ስለነበረ በድንጋያማው የሰው ስሜትና አስተሳሰብ ውስጥ የፈጣሪ ርኅሩኅ ሃሳብ የሚገባበት መንገድ መዘጋጀት ነበረበት።

ያንን ቀና መንገድ በራሱ መቀየስ የሚችል ሰው ግን የለም። "እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤ አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም" (ሮሜ 3፡10-11)። በዚህ ምክንያት ጌታ ራሱ ይህን ከባድ ኃላፊነት እንዴት እንደሚወጣው በነቢዩ ሚልክያስ በኩል ሲናገር እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤ በፊቴ መንገድ እንዲያዘጋጅ መልእክተኛዬን እልካለሁ" (ሚል. 3፡1)።

ያ ትንቢት ተነግሮ አራት መቶ ዓመታት ከተቆጠሩ በኋላ ከአምላክ ጋር ጥብቅ ግኑኝነት የነበረው ዘካርያስ የተባለ ትሁት ካህን እንደ አሪት ደንብ ዕጣን ለማጠን ወደ ቤተመቅደስ ገባ። ወደ ዕጣኑ መሰውያም ሲደርስ ያልጠበቀው እንግዳ አገኘው፤ መልአክ ገብርኤልን አይቶ ፍርሃት ዋጠው። "መልአኩ ግን እንዲህ አለው፤ 'ዘካርያስ ሆይ፤ አትፍራ፤ ጸሎትህ ተሰምቶአል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ። በእርሱ ተድላና ደስታ ታገኛለህ፤ ብዙዎችም እርሱ በመወለዱ ደስ ይላቸዋል፤ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና። የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ በእናቱም ማሕፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል። ከእስራኤልም ሰዎች ብዙዎቹን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳቸዋል፤ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው፣ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ፣ ለጌታ የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት በኤልያስ መንፈስና ኀይል በጌታ ፊት ይሄዳል'" (ሉቃ. 1፡13-17)።



ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ የተናገረው ነገር የሚልክያስና የኢሳያስ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው (ኢሳ. 40፡3)። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት "ለጌታ የተገባ ሕዝብ ለማዘጋጀት" የተመረጠው ሰው ዮሐንስ ነበር። ይህ ዮሐንስ ተራ ሰው አልነበረም። ገና በእናቱ "ማህፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል" ተብሎለታል (ሉቃ. 1፡15)። ይህ ማለት ዮሐንስ ራሱን ገና ሳያውቅ ተልዕኮውን ለማሟላት የሚያስችለው መለኮታዊ ኃይል መርቶ ያሳድገዋል ማለት ነው።

"በኤልያስ መንፈስና ኃይል በጌታ ፊት ይሄዳል" የተባለው ዮሐንስ በእርግጥም ተራ ሰው አልነበረም። ቅዱስ ገብርኤል ስለ ማንነቱ ሲናገር "በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናል" ብሏል። የታላቅነቱ ምሥጢር ደግሞ ከመፀነሱ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ ነው። ይህን ሰው ተጠቅሞ ነው እግዚአብሔር "የማይታዘዙትን ወደ ፃድቃን ጥበብ" ለመመለስ የተሰናዳው።

በምድር ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች ገድላቸው ብዙ ነው። በከንቱ ደም ያፈሰሱ ወይም የሚያስጎመጅ ሀብት ያፈሩ ሰዎች ይከበራሉ። በጥበባቸው ዓለምን ያስደነቁ ተመራማሪዎች በተለያዩ ሽልማቶች ይዋባሉ፤ በሕይወት የሌሉቱም ይዘከራሉ። በጌታ ፊት ታላቅ የሆኑትስ?

ዮሐንስ የወይን ጠጅና ሌሎች አስካሪ መጠጦችን ቀምሶ አያውቅም። ስለሆነም አእምሮውና መንፈሱ የተሳሉ ነበሩ። ምግቡም ቢሆን ምላስን አታልለው ጤና በሚያውኩ የጥብስ ቅባቶችና ሰው ሰራሽ ስኳር የተበላሸ አልነበረም። መብሉ ለሆድ የሚቀል፤ በኦሪት የተፈቀደው "አንበጣና የበረሃ ማር ነበር" (ማቴ. 3፡4)። የተጎናፀፈው ደግሞ የነገሥታትን ሐምራዊ ካባ ሳይሆን የግመል ጠጕር ነበር፤ የወገቡም ቀበቶ ጠፈር ነበር።

ዮሐንስ በአበላሉና በአለባበሱ ጠንቃቃ የነበረው ግብዝ በሆነ ትህትና የሰዎችን ቀልብ ሊስብ ፈልጎ አይደለም። ለጥቂት ጊዜ በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ራሱን ገዝቶ የተጠራበትን ታላቅ ዓላማ ለመፈፀም ፅኑ ጉጉት ስለነበረው ነው። ኑሮው ሆድን በማጥገብ፣ በመጠጥና በመዝናናት ላይ ያተኮረ ሳይሆን፤ መንገድ ጠራጊ በመሆን ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ ለማዘጋጀት በቅዱስ ጽሞና ላይ የቆመ ነበር። ይህ ደግሞ አደንዛዥ ከሆኑ ምድራዊ ፍላጎቶች ተላቅቆ ራስን በቃሉ ወደ መመርመርና በማያቋርጥ ጸሎት ኃይል ወደ አምላክ መቅረብን ግድ ይላል። ዮሐንስ ለሥጋው ሳይሆን ለነፍሱ ያደረ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ስለነበር አኗኗሩ በመለኮታዊ ሥልጣን ሥር ነበር። መብል፣ መጠጥና አለባበሱ ለጌታ የመጀመሪያ ምጽዓት የሚያዘጋጁ ነበሩ።

እስቲ ይህንን ለነፍሱ ያደረ ለእግዚአብሔር የኖረ ታላቅ የእምነት ሰው በዚህ ዘመን ታላላቅ ከሚባሉ ነቢያትና ሃዋርያት ጋር እናነጻጽረው? በዘመናችን የጌታ ዳግም ምጽዓት መቃረቡን የሚያሳዩና ለዚያ ደግሞ መንገዱን እንድንጠርግ የሚጠቁሙ ብዙ ምልክቶች እያየን ነው። ፍጻሜ ዓለም የሚሆንበት የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ደግሞ ከመጀመሪያው ምጽዓት የበለጠ ዝግጅት እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። ታዲያ እንደ ዮሐንስ ምድራዊ ምቾትና የገንዘብን ፍቅር የካዱ ነቢያትና ሐዋርያት ዛሬ የማናየው ለምንድነው? መንፈስ ቅዱስ በዘመናት አሠራሩን ቀይሮ ይሆን?

መለኮታዊ ሕይወት ልዩ ኃይል አለው። ዮሐንስ አጥብቆ የሚስብ ሕይወት ነበረው። ቃሉ እንደሚለው "ከኢየሩሳሌም፣ ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጎርፉ፣ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር" (ማቴ. 3:5-6)።



በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሚሠራው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ነው፤ ያ መንፈስ ሲገለጥ ደግሞ "ዓለምን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል" (ዮሐ. 16:8)።

ርኩሰት እንደ ጽድቅ በሚቆጠርበት በዚህ የተገላቢጦሽ ዘመን፤ ኃጢአተኞች ከልብ እየተናዘዙ ቢጠመቁ ምንኛ ምድሪቱ ሰላም ታገኝ ነበር! ግን ሰዎች ወደ ንስሐ እንዳይጎርፉ የከለከለው ምንድነው? መንፈስ ቅዱስን ተሞልተናል በሚሉና፤ ሌሎችን በቀላሉ እንሞላለን የሚሉ ሰባኪያን በገነኑበት አገር ላይ ኃጢአት መለኪያ እስኪያጣ የተትረፈረፈው ለምንድነው?

ስለ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመሰክር እንዲህ አለ፤ "እኮ! ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን ለማየት ይሆን? አዎን፣ እላችኋለሁ፤ ለማየት የወጣችሁት ከነቢይም የሚበልጠውን ነው። … እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም" (ሉቃ. 7:26)።

ይህ "ከሴት ከተወለዱት መካከል" ሁሉ ታላቅ የነበረው ዮሐንስ አንድም በሽተኛ አልፈወሰም፤ አንዳችም የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል አልጻፈም። በእግዚአብሔር ፊት ግን ታላቅ ሰው ነበር። "ከሴት ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም" ማለት ቀይ ባህርን በጌታ ኃይል ከከፈለው ሙሴ፤ ዮሐንስ ይበልጣል ማለት ነው፤ በብሉይ ዘመን ብዙ ድንቅና ታምራት ከሠራው ኤልሳዕም ይበልጣል ማለት ነው።

ይህ ከነቢያት ሁሉ የሚልቀው ዮሐንስ ልዩ ያደረገው ሕይወቱ ነው። ዮሐንስ ንብረት፣ ሚስትና ቤተሰብ አልነበረውም። ገንዘብ በመሰብሰብ ላይ ባተኮረ ምድራዊ ሙያ አንድም ቀን ተጠምዶ አያውቅም። ከመፀነሱ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ጉዳዩና ሕይወቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ ነበር።

ዛሬ በውድ አልባሳት አጊጠው፤ በዘመናዊ መኪናዎችና የሚንሸራሸሩ "ነቢያት"ና "ሐዋርያት"ን ከዮሐንስ ጋር ስናነፃፅር ምን ይታያል? በመድረክ ከሚሠሯቸው "ድንቆች" በላይ የሚደንቀው አጭበርባሪ ባሕርያቸው ውስጥ የጎላው ሰይጣናዊ ተዓምር ነው። መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት እንድንላቀቅ ሲተጋ፤ ታምራት ሠሪዎቹ ደግሞ ለኃጢአት ሽፋን ፍለጋ ድንቅ ትርኢት ለማቅረብ ይሯሯጣሉ። ሰዎች ዓይናቸውን ከአንገብጋቢው የቅድስና አስፈላጊነት ላይ አንስተው በአቋራጭ ለሚገኝ ጊዜያዊ ጥቅም እንዲተራመሱ ጥድፊያ ይፈጥራሉ። ከኃጢአት

ባርነት እንዳንላቀቅ የሚፈልገው ሰይጣን ተዓምራዊ መስተፋቅሩን ያለ ገደብ አፍስሶባቸው ተወዳጅ ዘራፊዎች አድርጓቸዋል።

የዘመኑ ቤተክርስቲያኖች በውሸታም ነቢያትና የተኩላ ልብ ባላቸው እረኞች የተሞሉ ናቸው። አምላክ ሕዝቡን በጤናና በገነት ወርቅ ዛሬውኑ እንደሚክብ የሚያስተምሩ ሁሉ፤ በምድር ሕይወቱ ቤትና ቅያሪ ልብስ ያልነበረውን ትሁቱን ክርስቶስ እንዴት ሊወክሉት ይችላሉ? ለመሆኑ ቃሉ ሥጋዊ ምቾት የቅድስና ውጤት መሆኑን ያስተምራል?

የታመመና በድህነት ቅርቃር ውስጥ የታሰረ ሁሉ ከአምላክ ፈቃድ ውጪ የሚኖር ነው? ዮሐንስ መጥመቁ ድሃ ነበር። ታስሮ የተገደለው ደግሞ እውነትን በድፍረት ለንጉሥ ሄሮድስ በመናገሩ ነው። መጥመቁ ታስሮ ሳለ ነው ጌታ "ከሴት ከተወለዱት መካከል ከዮሐንስ የሚበልጥ የለም" ያለው። ታላቁ ነቢይ ኤልያስም መጠለያና ምግብ አጥቶ ከአንዲት መበለት ቤት ተጠግቶ ይኖር ነበር። ጌታችንንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የሚያስተምርበት የግል ምኩራብ አልነበረውም፤ ቆሞ ያስተማረበት መርከብ እንኳን የራሱ አልነበረም።

የዛሬ "ነቢያት" እንደ ጥንቱ በልዓም ለገንዘብ በመስገብገብ እውነተኛ ጥሪያቸውን ክደው ምድራዊ ቪላዎቻቸውን ለማሳመር ይቅነዘነዛሉ፤ ምስኪኑን ያጭበረብራሉ። በእግር የተንከራተተውን ክርስቶስ ረግጠው በምቹ መኪናዎች ሲሄዱ በሮቻቸውን ለመክፈት በሚፎካከሩ ሰዎች ይከበባሉ። ታዲያ ምኑን የጌታ ተከታዮች ሆኑ? ጎሊናቸውስ እንዴት ዝም አለ? ክርስቶስ እዩኝ ብሎ እየጮኸ በታምራት ቲያትር ተከታዮቹን አጡዟል?

የዛሬ "ነቢያት" ርካሽ የሥጋ ነጋዴዎች ናቸው። በራስ ወዳድ ልቅነት ቅዱስ ቃሉን አጣመው፤ ተከታዮቻቸውን በራሳቸው ጠማማ የእርኩሰት አምሳያ እየቀረፁ ነው። በጎቻቸውን በሙዚቃና በተምታታ መንፈሳዊ ድንጋጤ አደንዝዘው የሰዎችን ክቡር ጊዜና ልብ አባክነዋል። ልብሶቻቸው በቅሚያ ኪሶች የተሞሉ ናቸው። መድረኮቻቸው ደግሞ የቅጥፈትና የዝርፊያ መሰውያዎች ሆነዋል።

ራስን መግዛትና ኃጢአትን የመተው መለኮታዊ ተዓምር ከሁሉ የላቀ ድንቅ ነገር መሆኑ በሰፊው የማይታወቀው እንደ ዮሐንስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የቀየ ግኑኙነት ያላቸው ነቢያትና ሐዋርያት ስለሌሉ ነው። አገራችን በእረኞች ስንፍናና ደፋር ስግብግብነት ምክንያት መንፈሳዊ ኪሣራ ውስጥ ገብታለች። ክርስቶስ ግን ዝም አይልም።



"ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እኔ በእረኞች ላይ ተነሥቻለሁ፤ ስለ መንጋዬ እጠይቃቸዋለሁ፤ ከእንግዲህ እረኞች ራሳቸውን መመገብ እንዳይችሉ፣ መንጋዬን እንዳያሰማሩ አደርጋለሁ። መንጋዬን ከአፋቸው አስጥላለሁ፤ ከእንግዲህም ምግብ አይሆናቸውም"። ...

በፍርዱ ተስፋ የማይነፍገው "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፤ 'እኔ ራሴ በጎቼን እፈልጋቸዋለሁ፤ እጠብቃቸዋለሁም። እረኛ ከመንጋው ጋር ሳለ፣ የተበተኑበትን በጎች እንደሚፈልግ ሁሉ፣ እኔም በጎቼን እፈልጋለሁ። በደመናና በጨለማ ቀን ከተበተኑበት ስፍራ ሁሉ አድናቸዋለሁ። ... በመልካሙ ስፍራ አሰማራቸዋለሁ፤ የእስራኤል ተራሮች ከፍታም የግጦሽ መሬት ይሆናቸዋል። በመልካሙ ግጦሽ መሬት ላይ ይተኛሉ፤ እዚያም በእስራኤል ተራሮች ለምለም መስክ ላይ ይመገባሉ። እኔ ራሴ በጎቼን አሰማራለሁ፤ አስመስጋቸዋለሁም'" (ሕዝ. 34፡11-15)።

መንፈሳዊ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ እረኞች ምክንያት የእግዚአብሔር ዓላማ አይስተጓጎልም። ከነቢይ የሚበልጠውን ዮሐንስን ልኮ፣ ኃጢአተኞችን ወደ ጻድቃን ጥበብ ተመልሰው በሥጋ የሚገለጠውን አዳኝ ለመቀበል የሠራው አምላክ ዛሬም ለበጎቹ ይራራል። ዳግም በክብር ከመገለጡ በፊትም እንደ ዮሐንስ ያሉ፤ በኤልያስ መንፈስና ኃይል የጌታን በጎች ወደ ቀናው መንገድ የሚመልሱ ሰዎችን ይልካል። በነውር ውስጥ ለተመቻቹት ውሸታም እረኞች ግን የህፍረት ቀን ይመጣል። "'ስለዚህ እኔ ለፍርድ ወደ እናንተ እመጣለሁ፤ በመተተኞች፣ በአመንዝራዎች፣ በሐሰት በሚምሉ፣ የሠራተኞችን ደመወዝ በሚከለክሉ፣ መበለቶችንና ድኻ አደጉን በሚጨቍኑ፣ መጻተኞችን ፍትሕ በሚነፍጉ፣ እኔንም በማይፈሩት ላይ እመሰክርባቸው ዘንድ እፈጥናለሁ' ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት" (ሚል. 3፡5)።

(ድርባ ፈቃዱ)

# “ነጣቂ ተኩላዎች” - የዘመኑ ነቢያትና ሐዋርያት

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃሰተኛ ነቢያትንና በእርሱ ስም የሚያጭበረብሩትን ጠንከር ባለ ቃል ብቻ ሳይሆን የጠራቸው በክፉ አውሬም መስሏቸዋል። “የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ” ማቴዎስ 7፡15።

ሃዋርያው ጳውሎስ እንዲሁ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የመሰናበቻ ንግግር ባደረገ ጊዜ ከእርሱ በኋላ ስለሚመጡ ክፉ መምህራንና መሪዎች ሲናገር “ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ” ብሎ ነበር (ሐዋ. 20፡29)።

ከላይ በተጠቀሰው የጌታችን ንግግር ላይ “ነጣቂ” ተብሎ የተጠቀሰው ቃል “ቀማኛ” ከሚለው ጋር አብሮ የሚጠቀስ ነው (ሉቃስ 18፡11)። ሐሰተኛ ነቢያት ከቀማኝነታቸው በተጨማሪ ይህንን ባህርያቸውን ደብቀው እንደሚመጡና ሲታዩ እንደ በግ የዋህና ለሌላው ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ለመስጠት የተዘጋጁ አድርገው እንደሚቀርቡ ጥቅሱ ይናገራል። በዚህ ብቻ ሳያበቃ “ተጠንቀቁ” በማለት ጉዳዩ ጥንቃቄ የሚያሻው እንደሆነ አጽንዖት ሰጥቶታል።

ሃዋርያው ጳውሎስ ደግሞ “ጨካኞች ተኩላዎች” በማለት ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ደቀመዛሙርትን ወይም ተከታዮችን እንደሚሰበስቡ፤ ተከታይ ለማፍራት ደግሞ እውነትን አጣምመው እንደሚናገሩ ይገልጻል። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች ግልጽ ናቸው፤ አንደኛው እነዚህ ሰዎች የሚከተሏቸው እንደሚኖሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማጭበርበር ወይም ነገርን በማጣመም ሰዎችን እንደሚያታልሉ ነው።

## የተኩላ ባህርያት

ተኩላዎች በውሻ ቤተሰብ ውስጥ የሚመደቡ ሲሆን ከዚያ ቤተሰብ ውስጥ ትልቁ እንስሳ ተኩላ ነው። አስተዋይ ወይም ብልህ ከሚባሉት እንስሳት መካከል ተኩላ አንዱ ነው። ወደ ላይ ቀጥ ያሉት ጆሮዎች፣ ስለታም ጥርሶች፣ ወደፊት የሾጠጠው አፍ፣ ሰርጾ ገብ ዓይኖች ይህንን ብልህ የሚባለውን የተኩላ ባህርያትን የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚህ ሌላ የሙቀት መጠኑ እስከ -40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በወረደ ቀዝቃዛ ቦታ መኖር ይችላል።




ተኩላዎች ከሚታወቁባቸው ነገሮች አንዱ በጩኸታቸው ወይም በሚያላዝኑበት ድምጽ ነው። ይህንንም እርስበርስ ለመግባባት የሚጠቀሙበት ነው። ብቸኛ የሆነ ተኩላ ትኩረት ለመሳብ ማላዘን ሊጀምር ይችላል። በማኅበር ውስጥ ያለ ደግሞ እንዲሁ ሊያላዝን ይችላል፤ ነገርግን የእርሱ ድምጽ ማሰማት ዋናው ምክንያት “እዚህ ነው ያለሁት፣ ድንበሬን እንዳትጥሱ” የሚል ማስጠንቀቂያ አዘል ነው።

በአገራችን ከምናውቃቸው ሌላ የተለያዩ ዓይነት ተኩላዎች በዓለማችን ላይ ይገኛሉ። ሁሉንም የሚያመሳስላቸው ባሕርይ የሚያሰሙት ድምጽ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም በርካታ ባህርያት አሉ። ተኩላዎች በደንብ የተደራጀ ማኅበራዊ መዋቅር አላቸው። ይህም በተለይ ለአደን በሚወጡበት ጊዜ ድንበራቸውን በማስጠበቅና እንደልብ በመነጋገር የተሳካ አደን ለማድረግ ያስችላቸዋል።

ተኩላዎች ለአደን በሚወጡበት ጊዜ ሰፋ ያለ ቦታ ያካልላሉ፤ በአብዛኛው የሚጓዙትም በምሽት ጨለማን ተገን በማድረግ ነው። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ቀን ብቻ እስከ 20 ኪሎ ሜትር ይጓዛሉ። የሚፈልጉትን አድነው እስኪያገኙ የማይሄዱበት ቦታ የለም፤ በዚህም በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ የሚታወቁ ሆነዋል።

አመጋገብን በተመለከተ ተኩላዎች ሲያድኑ በቡድን ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በግልም ለአደን ይወጣሉ። ለአደን በሚወጡበት ጊዜ አድነው የያዙትን ማንኛውንም ነገር የመብላት ባህርይ አላቸው። ሥጋ ብቻ በሊታ ሲሆኑ የሚያድኑት ለጨዋታ ወይም ለስፖርት ሳይሆን የመኖር ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ነው። ያደኑትንም አምጥተው ለልጆቻቸው በመስጠት ይመግቧቸዋል። ይህንንም የሚያደርጉት የበሉትን ከሆዳቸው መልሶ በማውጣት ወይም ትኩስ ሥጋ በአፋቸው ይዞ በመምጣት ነው።

ለአደንና ለመብል የሚጠቀሙበት 42ቱም ጥርሳቸው በጣም ጠንካራ በሆነ የመንጋጋ ጡንቻ የተደገፈ ሲሆን ከዚሁ ጋር ከፍተኛ ብቃት ያለውን የማሽተት ችሎታቸውን በመጠቀም ታዳኙ ያለበትን ቦታ ለማወቅና ወደ ጥቃት ለመሄድ በቀላሉ ይችላሉ።

ተኩላዎች አንድ መንጋ ውስጥ ገብተው ከማደናቸው በፊት "የሞት ውይይት" በሚባለው ጉዳይ ውስጥ ይገባሉ። ይህም ተኩላውና ታዳኙ ተፋጥጠው ለተወሰኑ ደቂቃዎች የሚተያዩበት ድምፅ አልባ ንግግር ነው። በዚህ "የሞት ውይይት" ተኩላው ታዳኙን እንስሳ "አሳድጂ ልያዘው ወይስ እንደ ተላላፊ መንገደኛ ቆጥሬ ልተወው" በማለት ውሳኔ ላይ የሚደርስበት ክስተት ነው ተብሎ ይታመናል።

ሌላው የሚገርመው የተኩላዎች ባህርይ ከሚያድኑት እንስሳ መንጋ ውስጥ የሚበሉት በተለይ የታመሙትን፣ ደካማዎችን፣ ልጆችን፣ ወይም ለአደጋ የተጋለጡትን መርጠው መሆኑ ነው። ይህ ግን ጤነኛውን አይነኩትም ማለት ሳይሆን ቀዳሚው ምርጫቸው ግን አይደለም። ልጆቻቸውን ለአደን በሚያዘጋጁበትም ወቅት የሚጠቀሙት አንዱ ስልት ሚዳቋ እንዲያሳድድ ማድረግ ነው። በዚህ ልምምድ ወቅት ዋናው ዓላማ የአደን ክህሎትን ማዳበር ስለሆነ ልጅ ተኩላዎች ሚዳቆዎቹን ማሳደድ እንጂ መግደል አይፈቀድላቸውም።



ተኩላዎች በኅብረት በሚሆኑበት ጊዜ የበላይ ወይም አለቃ የሚባለውን ለይቶ ለማወቅ ብዙም አይከብድም። በኅብረቱ ውስጥ ግጭት ለመቀነስ ከሁሉም የበላይ የሆነው ቀጥ ብሎ ይቆማል፤ ጥርሱን እያሳየ፣ ጸጉሩ እንደቆመ ዓይኖቹን ገልጥጦ በመክፈት ከፍ ብሎ ሲታይ ሌሎቹ ታዛዥ ተኩላዎች ደግሞ ጆሮቻቸውን ወደኋላ በመሸምጠጥ፣ መሬት ላይ ለጥ ብለው፣ ጭራቸውን በእግሮቻቸው መካከል አድርገው፣ አፋቸውን ዘግተው ዓይኖቻቸውን ጨለም ጨለም በማድረግ በሆዳቸው መሬቱን በመንካት ታዛዥነታውን ይገልጻሉ።

### ነጣቂ፣ ጨካኝ ተኩላ

ጌታም እንዲህ አለ፤ "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ" ማቴዎስ 7፡15።

ጌታችንን ይህንን ማስጠንቀቂያ የተናገረው በተራራው ስብከቱ ወቅት ሲሆን ሐሰተኛ ነቢያቱን "ነጣቂ ተኩላ" በሚል ስዕላዊ መግለጫ ነው ያብራራቸው። ከላይ እንደተገለጸው ይህ "ነጣቂ" የሚለው ቃል "ቀማኛ" ከሚለው ቃል ጋር በተመሳሳይ የሚጠቀስም ነው። በሌላ ቦታ ደግሞ ይኸው ቃል "ኃይልን በመጠቀም መንጭቆ መውሰድ"፣ "መንጠቅ" የሚለውንም ሃሳብ የሚጠቀልል ነው። ለዚህም ነው ጌታችን "ተጠንቀቁ" በማለት የተናገረው። ምክንያቱም በንቃት ካልጠበቅን ትልቅ ችግር ውስጥ ልንገባ እንችላለን። ሆኖም "ተጠንቀቁ" ከማለት በተጨማሪ "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" በማለት ዘርዘር ያለ የመፍትሔ ሃሳብንም ሰጥቷል (ማቴዎስ 7፡16-20)።

ከላይ በመግቢያው እንደተጠቀሰው ሃዋርያው ጳውሎስ እነዚህን የተኩላ ባህርይ ያላቸውን ሰዎች "ጨካኞች" ይላቸውና ሲቀጥል "ከእናንተው መካከል እንኳ የራሳቸውን ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እውነትን የሚያጣምሙ ይነሣሉ። ስለዚህ ተጠንቀቁ፤ ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን ምንም ያህል ሳላቋርጥ በእንባ እያንዳንዳችሁን እንደ መከርኋችሁ አስታውሱ" ይላል (ሐዋ. 20፡29-31)። እዚህ ላይ ጌታችን ኢየሱስም ሆነ ሃዋርያው ጳውሎስ የተናገሯቸው ተመሳሳይ ቃላት "ነጣቂ ተኩላ" እና "ተጠንቀቁ" የሚሉት እንደሆኑ ልብ ይሏል።

በጥንት ዘመን እረኞች የሚለብሱት የበግ ለምድ ነበር። ይህም ከበግ ጸጉር የተሠራና የከረምቱን ብርድ፣ የሌሊቱን ቁር ለመከላከል የሚለበስ ነው። እውነተኛው እረኛ ከበጎቹ ጋር ተመሳስሎ፤ ከእነርሱ እንደ አንዱ

ሆኖ፤ የእነርሱን ዓይነት ቆዳ ለብሶ ነው ጥበቃ የሚያደርግላቸው። ከዚህ ሌላ እውነተኛው እረኛ በአገራችን እንደምናውቀው ከበጎቹ ኋላ ሆኖ እየገረፈ ራሱ ወደፈለገው አቅጣጫ መንጋውን የሚመራ ሳይሆን ከፊት ሆኖ አቅጣጫ እያስያዘ፣ እየመራ፣ የሚመጣውን ማንኛውንም አደጋ ከፊት ሆኖ እየተጋፈጠ መንጋው እንዲከተለው የሚያደርግ ነው።



በጎች በተፈጥሯቸው ከመንጋው ተነጥሎ የመሄድ፤ የመንከራተት ባህርይ አላቸው። ይህም ለአደጋ የሚያጋልጣቸውና ለጠላት አሳልፎ የሚሰጣቸው ክስተት ሲሆን ብዙ ጊዜ ይታያል። በጎች ካላቸው የዋህነት አኳያ ጠፍተው ባሉበት ጊዜ እንኳ መጥፋታቸውን ወዲያውኑ አያስተውሉም፤ ተመልሰው ወደ መንጋው እንዴት እንደሚቀላቀሉም አያውቁም። ከዚህ ሌላ ደግሞ መንጋውን መከተል ወይም አንዱ በመራው መከተል የበጎች ባህርይ ነው። ይህም በራሱ ለጠላታቸው ተኩላ ተጋላጭ ሲያደርጋቸው ይታያል።

ጌታችን ሲናገር እንዲህ አለ፤ "መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤ ተቀጣሪው እረኛ ግን በጎቹ የእርሱ ስላልሆኑ፣ ተኵላ ሲመጣ ጥሎአቸው ይሸሻል፤ ተኵላውም በጎቹን ይነጥቃል፤ ይበትናቸዋልም" (ዮሐንስ 10፡11-12)።

ተኩላ በጎችን ለማጥቃት ሲመጣ በተቻለው መጠን ራሱን ከእረኛው ጋር ለመመሳሰል ይሞክራል። ቢገኝም የበግ ቆዳ ለብሶ፤ አስፈሪ ጥርሶቹን ደብቆ "እኔኮ በግ ነኝ" በማለት ለመቀላቀል ቢሞክር የሚደንቅ አይደለም። ነገርግን አንዴ ከመንጋው መኻል ገብቶ ማተራመስ ሲጀምር ሁኔታዎች ፈጽሞ ይቀየራሉ።

በአገራችን ለቁጥር የሚያታክቱት ነቢያትና ሐዋርያት ብዙ የተኩላ ባህርያት ይታዩባቸዋል። ሲጀምሩ በግ ይመስሉና በኋላ ግን የተኩላ ባህርያቸውን ያወጡታል። በአፈጮማነት መጽሐፍ ቅዱሱን ሲጠቅሱ፣ ለምዕመን እየተጉ መሆናቸውን ሲያሳዩ ማንም ተኩላ ባህርያቸውን በፍጥነት ሊያየው አይችልም። በኋላ ግን የሰዎችን አመኔታ ማግኘታቸውን ሲያረጋግጡ እንደ አለቃ ተኩላ ጥርሳቸውን ሲያፏጩ ሌላው በተገዢነት ለጥ ብሎ እንዲሰግድላቸው ቀጥ ብለው ይቆማሉ።



በእነዚህ ነጣቂ ተኩላዎች ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሲናገሩ እንደሚደመጡት ነቢይ/ሐዋርያ ብለው ራሳቸውን የሾሙ ያደረሱባቸው ግፍ ደግሞ ለመናገር የሚያሳዝንና እጅግ የዘቀጠ ነው። አንዳችም የክርስቲያን ባሕርይ ሳያሳዩ እንዴት የረቀቁ ግፎችን እንደፈጸሙ የሚሰማው ዘግናኝ ዘገባ የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ አይደለም የካደው እንኳን የሚደፍረው አይደለም። መልካሙ እረኛ የሆነው ጌታችን አለምክንያት አይደለም "ነጣቂ ተኵላዎች" በማለት የጠራቸው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የተኩላ ባሕርይ፤ እነዚህ ራሳቸውን በተለያየ ቅዱስ ስም የሰየሙ "ነጣቂ ተኩላዎች" ለጥቅማቸው የማይጓዙት ርቀት የለም። ታዳኞቻቸው በሁሉም ቦታ እንደሚኖሩ ስለሚያውቁ ከአገር ውስጥ አልፈው በውጪ አገራት በስደት የሚገኘውን ሕዝባችንንም የጥቃት ሰለባ አድርገውታል። እንዲያውም ከዳያስፖራው የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በብር ከሚያገኙት የላቀ በመሆኑ ቅድሚያ ለእነርሱ እንደሚሰጡ ራሳቸው በአንደበታቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ።

ከዚህ ሌላ ከውጭ የሚመጡትን ከአውሮፕላን ማረፊያ በመኪና ተቀብለው ወደ እንግዳ ማረፊያ በመውሰድ "የቪ.አይ.ፒ. የጸሎትና የፈውስ አገልግሎት" እንደሚሰጡ፤ የአገር ውስጡ ተገልጋይ ግን በየቀኑ በጸሐይና በሌት ቁር እየተሰቃየ፣ በየቤተ እምነቶቹ ጥበቃዎች እየተንገላታ፣ ለቀናት እንደሚጠብቅ በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

"አብረኸኝ እንድታገለግል ጌታ ተናግሮኛል" በማለት በአስመሳይ ትህትና እና "በመንፈሳዊነት" ጥሩ የገቢ ምንጭ ያላቸውን በመቅረብ የእነርሱ አገልጋዮች እንዳደረጓቸው፤ ከዚያም አልፎ ንብረታቸውንና በሺዎችና ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘባቸውን ዘርፈው ሙልጫቸውን እንዳስቀሯቸው የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። እነዚህ ሰለባዎች ጉዳዩ መንፈሣዊ አገልግሎት እንዳልሆነ በሚረዱበት ወቅት ገንዘባቸውና ንብረታቸው እንዲመለስላቸው በሚጠይቁበት ጊዜ የሰማይ ስባሪ በሚያክሉ ወጠምሻዎች ድብደባ እንደደረሰባቸው፤ ለጉዳዩ ዕልባት ለማግኘት የሚሠሩ ሽማግሌዎችም ከባድ ማስፈራሪያ እንደሚሰጣቸውና ሽምግልናውን እንዲያቆሙ እንደሚገደዱ ግፉዓን ይናገራሉ።

ከዚህ ሌላ የተቀደሰ ዘይት ነው፤ የተጸለየበት ውሃ ነው፤ በሚል በብዙ ሺዎች የሚሸጠውና ይህንንም የሚወስዱ ከበሽታቸው ወዲያውኑ እንደሚፈወሱ እየተነገራቸው መድኃኒታቸውን በማቆም ለሞት እንደተዳረጉ የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። ለዚህ ዓይን ያወጣ ወንጀል አንድም ነቢይ ወይም ሃዋርያ ነኝ የሚል ወደ ሕግ ቀርቦ የተጠየቀበት ሁኔታ አለመኖሩ አሁንም በ"ነጣቂ ተኩላነት" ያለተጠያቂነት ያገኙትን እያደኑ እንዲኖሩ ፈቃድ ሰጥቷቸዋል።

### ስለዚህ ምን እናድርግ?

የእነዚህን "ለመንጋው የማይራሩ ነጣቂ ተኩላዎች" ጸረ-መንፈሣዊ የግፍ ድርጊት ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም። ከሁሉ በላይ እጅግ ርኅሩኅና ፍጹም አፍቃሪ በሆነው አምላክ ስም እንዲህ ያለውን ተግባር በመፈጸም የእግዚአብሔርን ቅዱስ ስምና ባሕርይ እንዲጎድፍ በማድረግ ረገድ የጠላት ወኪል መሆናቸው ሕዝባችን ሊገነዘብ ይገባዋል።

ከዚህ ግንዛቤ ሌላ እያንዳንዱ ምዕመን ለእግዚአብሔር ቃል ቀዳሚ ትኩረት በመስጠት ማጥናት ይገባዋል። "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል" ይላል ቃሉ (ሆሴዕ 4፡6)። ስለዚህ ሕዝባችን በቅድሚያ የቃሉ ዕውቀት ያስፈልገዋል።

ወደ እነዚህ "ነጣቂ ተኩላዎች" የምሄደው ለምንድነው ብሎ መጠየቅ ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ነው። በርካታው ሰው የተኩላዎቹ ሰለባ የሚሆነው ሃብት ለማግኘት፣ ከበሽታ ለመፈወስ፣ ከችግር ለመላቀቅ፣ ወዘተ በሚል እንደሆነ እሙን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፈውስ፣ ከችግር ስለመዳን፣ ስለ ብልጽግና እና መሰል ጉዳዮች ምን ይላል ብሎ ማጥናት ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። ሲቀጥል ስለ ሃሰተኛ ነቢያትና ሐዋርያት ቃሉ ምን ያስተምራል ብሎ ጊዜ ወስዶ ማጥናት ሌላው ሥራ መሆን አለበት። "ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል" (ያዕቆብ 1፡5)።



ሌላውና በጣም ወሳኝ የሆነው ነገር "በእርግጥ አምላካችን እንዲህ ማንም ሊቀርበው የማይችል፤ በአማላጅና ነቢያት ነን በሚሉ ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዳችን በቀጥታ ልናገኘው የማንችል ነው?" የሚለው መጠየቅና መመለስ ያለበት ጉዳይ ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ሲናገር "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል" ብሏል (ዮሐንስ 16፡ 23)። አምላካችንን እንደፈቃዱ የለመነውን ሁሉ ሊሰጠን ፈቃደኛ ነው።

በመቀጠልም በዚሁ ዮሐንስ ምዕራፍ 16 ላይ ጌታችን ይህንን አስደናቂ ነገር ተናገረ፤ "በዚያ ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ ይህም በእናንተ ፈንታ አብን እለምናለሁ ማለቴ አይደለም፤ ስለ ወደዳችሁኝና ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ ራሱ ይወዳችኋል" (ቁጥር 16-17)።

ጌታ ኢየሱስ በእነዚህ ቁጥሮች ከላይ በቁጥር 23 የተናገረውን ነው ያብራራው። በሌላ አነጋገር ጌታችን ያለው በእኔም ስም መለመን አያስፈልጋችሁም፤ ለእግዚአብሔር አብ በቀጥታ፣ ራሳችሁ፣ ጥያቄያችሁን ማቅረብ ትችላላችሁ። እኔን የሚወደኝ አብ እናንተንም ይወዳችኋል። በመካከል ምንም አማላጅ፣ ነብይ፣ ሐዋርያ፣ ወዘተ አያስፈልጋችሁም ምክንያቱም "አብ ራሱ ይወዳችኋል" እያለን ነው ያለው።

እግዚአብሔር አምላካችን "እጅግ ርኅሩኅና መሐሪ ነው" (ያዕቆብ 5፡11)። እንዲህ ያለ አምላክ እያለን ለምን ወደሌላ ቦታ፣ ለመንጋው ወደማይራሩ ጨካኝና ነጣቂ ተኩላዎች ለመሄድ እንፈልጋለን?*

"ምሕረትን እንድንቀበልና በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ፣ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብራውያን 4፡16)።

(ጥበበሥላሴ መንግሥቱ)

* በእነዚህና መሰል ርዕሰ ጉዳዮች በቀጣይ የሚወጡ ጽሁፎች ይኖራሉ

# ተዓምራት፤ በፊሊጶስና በጠንቋዩ ሲሞን

በሐዋርያት ምስክርነት ምክንያት የአማኞች ቁጥር በኢየሩሳሌም በፍጥነት ባደገበት ወቅት አስጨናቂ ስደት በቤተክርስቲያን ላይ ደርሶ እንደነበረ ቃሉ ይናገራል። በስደቱ ምክንያት ከኢየሩሳሌም ከሸሹት አንጋፋ ሰዎች አንዱ ፊልጶስ ነበር። ይህ መንፈሳዊ መሪ "ወደ ሰማርያ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው። ብዙ ሕዝብም ፊልጶስ የተናገረውን ሲሰሙና ያደረገውንም ተዓምራዊ ምልክቶች ሲያዩ፣ አንድ ልብ ሆነው ያዳምጡት ነበር። ርኩሳን መናፍስትም እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ወጡ፤ ብዙ ሽባዎችና አንካሶችም ተፈወሱ፤ ከዚህ የተነሣም በከተማዪቱ ታላቅ ደስታ ሆነ" (ሐዋ. 8:5-8)።

ለሰማርያ ሰዎች ክርስቶስ ተሰበከላቸው። ከስብከቱም ጋር ተዓምራዊ ምልክቶች ታዩ። የፊልጶስ ስብከትና ተዓምራት የሕያው አምላክ መንፈስ ሥራዎች ስለነበሩ ሕዝቡ ጉዳዩን በአግራሞት ይከታተል ነበር፤ በከተማዪቱም ታላቅ ደስታ ሆነ። ይህን ታላቅ ደስታ ያመጣው የኃጢአት መድኃኒትና የበሽታ ሁሉ ሐኪም የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ማግኘታቸው ነው።

ቃሉ በመቀጠል እንዲህ ይላል፤ "ነገር ግን ከዚህ ቀደም ሲል በከተማዪቱ ውስጥ እየጠነቈለ የሰማርያን ሰዎች ሁሉ ያስገረመ፣ ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ነበር፤ እርሱም ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ይቈጥር ነበር። ከታናሽ እስከ ታላቅ ያለው ሰው ሁሉ፣ 'ይህ ሰው "ታላቁ ኀይል" በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኀይል ነው' በማለት ከልብ ያዳምጡት ነበር" (ሐዋ. 8:9-10)።

የሲሞን ጥንቆላ እንደ ፊልጶስ ተዓምራት የሰማርያን ሰዎች ሁሉ ያስገረመ ነበር። የመተተኛው ሲሞን ባህርይ ግን ከቅዱስ ፊልጶስ የተለየ ነበር። ፊልጶስ ለዲቁና አገልግሎት የተቀባ፣ ድሆችን ለመርዳት የተዘጋጀ ትሁት ሰው ነበር (ሐዋ. 6፡5)። ሲሞን ግን በጥንቆላው ምክንያት "ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ይቆጥር ነበር"። ከሰማርያም አድናቆትና አምልኮ ተቀበለ።

አንድ ሰው ራሱን እያወቀ "ታላቁ ኃይል" በመባል የሚታወቀው መለኮታዊ ኃይል አንተ ነህ ሲባል እንዴት ሳይፈራ ይቀበላል? የሰማርያ ሰዎች ብዙ ያላስተዋሉት መንፈሳዊ እውነት ቢኖርም፤ ሙሴ በጻፋቸው የኦሪት መጽሐፍት ያምኑ ስለነበር ሲሞንም ይህ አጠራር ትክክል እንዳልሆነ ያውቅ ነበር፤ ነገርግን ለዚህ ነውሩ ከድፍረት ሌላ ምንም ምክንያት አልነበረውም። ኀሊናውን ለጥንቆላ ሸጦ፣ ተሰባሪ ሸክላ መሆኑን ረስቶ፣ አዳፋ ማንነቱን በቅዱስ አምላክ ዙፋን ላይ ለማስቀመጥ የተንጠራራ ሰው ነበር።

ሲሞን ሲናገር ሰዎች ከልብ ያዳምጡት ነበር፤ ሰባኪም ነበር ማለት ነው። ሲሞን በጥንቆላው ብዙ እንደቆየበትና ትኩረት ሰጥተው የሚከተሉት በርካታዎች እንደነበሩ ቃሉ ይመሰክራል (ሐዋ. 8:11)። ስለምን ሰብኮ ይሆን? ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ቆጥሮ የፈጣሪን ምስጋና የሚቀበል አታላይ ስለ አምላክ ታላቅ ርኅራኄና እውነት እንዴት መስበክ ይችላል? በአፈጮሌነት ለሰዎች የሚፈልጉትን በመናገር እንደመሰጣቸው መገመት አያዳግትም። በተለይ የእርሱን ሕይወት ከፊሊጶስ ጋር ስናነጻጽረው ምላሹን እናገኛለን።

የፊልጶስ ስብከት ከሲሞን የላቀ ለመሆኑ ማሳያው ፍሬው ነው፤ ውጤቱ ነው። "ነገር ግን ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው በመቀበላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤ ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር አምኖ ተጠመቀ" (ሐዋ. 8:12-13)።



የእግዚአብሔር መንግሥት ለሁሉም ክፍት መሆኑ፣ በክርስቶስ ስም የኃጢአት ይቅርታና የልጅነት መብት መገኘቱ ከስብከት ሁሉ የላቀ መልዕክት ነው። የአንድ መተተኛ ተዓምራት፣ ድንቆችና ራስን ብቻ ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ከንቱ ትምህርቶች ከወንጌል ኃይል ጋር ፈጽሞ መፎካከር አይችሉም። ስለሆነም ብዙዎች ሲጠመቁ እርሱም ተቀላቅሎ ተጠመቀ።

ሲሞን የተጠመቀው ደንግጦ ነው። የሰከነ ስብዕና አልነበረውም። በሰማርያ ያገኘው ዝና የውሸት ውጤት ነበር፤ ጥንቆላ የአጭበርባሪ ልቡ ሽፋን ነበር። ራሱን እንደ ታላቅ ሰው ቢቆጥርም የሰዎች አምልኮ ሲሸሽው የሕዝቡን

አግራሞት ከርሱ ወደነጠቀው ጉዳይ ዞሮ በመመሳሰል የቀድሞ ክብሩን ለመነናፀፍ ፈለገ። ዋና ሙያው ማስደነቅና ማስገረም ነበር። ይህ ደግሞ ተለዋዋጭና አዳዲስ ስልቶችን ማዳበር ስለሚጠይቅ የአግራሞት ነፋስ ወደነፈሰበት መሮጡ ግድ ሆነበት። ስለዚህም "ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደረገውን ምልክትና ታላቅ ታምራት አይቶም ተገረመ" (ሐዋ. 8:13)።

በሰማርያ ብዙዎች ማመናቸውን ሐዋርያት ሰምተው ጴጥሮስና ዮሐንስን ወደ እነርሱ ላኳቸው። "እነርሱም ሰማርያ በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤ … ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (ሐዋ. 8:15፣17)።

በሐዋርያትና በፊልጶስ ውስጥ የሠራው ኃይል መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ኃይል ደግሞ ለአማኞች ሁሉ በነጻ የሚሰጥ እንጂ እንደ ሲሞን ባሉ ጥቂት ንፉጎች የሚወሰን አይደለም። የእግዚአብሔር ሥራ ድንቅና ብርቅ ነው። ይህ የአምላክ ስጦታ በአንዳንድ "የተለዩ" ግለሰቦች ሕይወት ውስጥ ብቻ እየታየ ብዙሃኑ ከርቀት በመገረምና በመቋመጥ እንዲከታተል የሚጋብዝ አይደለም። በፊልጶስ ላይ የነበረው መንፈስ በሰማርያ አማኞችም ላይ ወረደ። ይህ ደግሞ አጋጣሚ የፈጠረው ክስተት ሳይሆን ጥንት የተተነበየ መለኮታዊ ዕቅድ ነው።

"ከዚህም በኋላ፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ፤ ጐልማሶቻችሁም ራእይ ያያሉ። በእነዚያ ቀናት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ እንኳ፣ መንፈሴን አፈሳለሁ" (ኢዩኤል 2:28-29)። ይህ የአምላክ ጸጋ ውሱንነት የሌለው፣ ለተወሰኑ "ምርጦች" ብቻ የተፈቀደ ሳይሆን ለሁሉም የተሰጠ ስጦታ ነው።



በአንፃሩ ሲሞን የበላይነቱን ለማስቀጠል የሚፈለግ በዘመናችን እንዳሉት የወንጌል ነጋዴዎች እንደነበረ ቃሉ ያስተምራል። "ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ፣ ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላቸው፤ 'እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ለእኔም ስጡኝ'" (ሐዋ. 8:18-19)።

ለመተተኛው ሲሞን መንፈሳዊ ኃይል ግላዊ ጥቅም የሚያግበሰብስበት መሳሪያ ነበር። እምነቱም ከአጋንንት እምነት የተለየ አልነበረም። "አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው፤ አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ፤ በፍርሀትም ይንቀጠቀጣሉ" (ያዕ. 2:19)።

ፊልጶስና ሐዋርያት ውስጥ ሲሠራ ያየው ኃይል የላቀ መሆኑን ስላመነ ነው ሲሞን እጅ የመጫን ሥልጣን የተመኘው። በመሆኑም አዲሱን ኃይል ተቀብሎ በሰማርያ ላይ መሠልጠኑን ሊቀጥልበት ፈለገ። የተሻለ የንግድ አጋጣሚ ተመለከተና ቢሳካለት የሚያገኘውን አስካሪ ክብር በምናቡ አሸትቶ ሕልሙን እውን ለማድረግ ቸኮለ። ስለሆነም ይህ ርኩስ ሰው የሕይወት ሁሉ መገኛና መድኃኒት የሆነውን መንፈስ ቅዱስ አላፊ ጠፊ በሆነው ገንዘብ ለመግዛት አሰበ።

"ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው፤ 'የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት አስበሃልና፣ አንተም ገንዘብህም አብራችሁ ጥፉ! ልብህ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ስላልሆነ፣ አንተ በዚህ አገልግሎት ድርሻ ወይም ዕድል ፈንታ የለህም'" (ሐዋ. 8:20-21)።

አንተም ገንዘብህም አብራችሁ ጥፉ! ራስን መውደድ ዝና ወደማሳደድ አጣድፎ የሚወስድ ሰይጣናዊ ወጥመድ ነው። ሰዎች በመለኮታዊ ድንቆች የመገረም ተፈጥሯዊ ዝንባሌ ስላላቸው ዲያብሎስ የዝና አፍቃሪዎቹን ወደ ቤተክርስቲያን መድረኮች በብዛት ይልካቸዋል። በራስ ፍቅር የጦዙትን የተጠሙትን ዕውቅና አጠጥቶ "ታላቁ ኃይል" በማስባል ለመለኮት ብቻ የሚገባውን ኀይል ያሸክማቸዋል። በተዓምራትና በድንቅ የሰዎችን ትኩረት በመሳብ ብዙ ታማኝ ተከታዮችን ያፈራላቸዋል።

ለመሆኑ ሲሞን ለሐዋርያት መስጠት የፈለገውን ገንዘብ ከየት አመጣው? ሙያው ጥንቆላ ከነበረ ከተከታዮቹ ነው ያገኘው ብሎ መገመት ስህተት አይሆንም። ሐዋርያትን ከርሱ እንደተሻሉ ጠንቋዮች አድርጎ ስለቆጠረም ነው አዲሱን መንፈሳዊ ኃይል በገንዘብ ለመግዛት የፈለገው። ይህ ግን ርኩስ ሃሳብ ነው። የዝና ፍቅር ከገንዘብና ከአጋንንት ታምራዊ ኃይል ጋር ተደምሮ ጥፋት እንደሚያመጣ አምላክ በጴጥሮስ አማካይነት ነገረው።

መንፈሳዊ ኃይል ከአምላክ በነፃ የሚታደል ሥጦታ ነው። ማንም ሰው ይህን ኃይል ተቀብሎ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ውስጥ ድንቅና ታምራት ሲሠራ ማየት ይችላል። ነገር ግን በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚታየውን የድንቅ ዓይነት የሚወስነው ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንጂ የሰው ሥጋ አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ልብ ውስጥ የሚያፈራው ታምራዊ ፍሬ ምንድነው? “የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው።” (ገላ. 5:28)

ከሁሉም በላይ ምድራችን የሚያስፈልጋት ታላቅ ኃይል ሥርነቀል የባሕርይ ለውጥ የሚያመጣ መንፈስ ነው። ታዲያ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት በጠፉበት ዘመን ድንቅ የሚሠሩ ነቢያትና ሐዋርያት መብዛታቸውን እንዴት እናየዋለን?

አብዛኛዎቹ የመፅሐፍ ቅዱስ ታላላቅ አባቶችና ነቢያት በተዓምራዊ ሥራዎች የታወቁ አልነበሩም። ሔኖክና አብርሃም ድንቅ ሠሪዎች አልነበሩም። ለአምላክ ስለታዘዙ ግን ታሪክ ለዘላለም ያመሰግናቸዋል። ኤርምያስና ሕዝቅኤል ከታላላቅ ነቢያት ውስጥ ይመደባሉ። በሕይወት ሳሉ ግን ዝነኛ አልነበሩም፤ ድንቅና ተዓምራት ሠሪዎችም አልነበሩም። እንዲያውም ዘመናቸውን የጨረሱት በድህነት፣ በስደትና ለንስሐ የጠሩት ሕዝብ እምቢ በማለቱ የመጣውን ጦስ ምክራቸውን አልቀበልም ካለው አንገተ ደንዳና ሕዝብ ጋር አብሮ በመቀበል ነበር።

“ሌሎቹ ደግሞ … መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤ ከዚህም ነጻ ለመውጣት አልፈለጉም። አንዳንዶቹ መዘባበቻ ሆኑ፤ ተገረፉ። ሌሎቹ ደግሞ ታስረው ወደ ወህኒ ተጣሉ፤ በድንጋይ ተወገሩ፤ በመጋዝ ለሁለት ተሰነጠቁ፤ በሰይፍ ተወግተው ሞቱ፤ እየተጐሳቈሉ፣ እየተሰደዱና እየተንገላቱ የበግና የፍየል ቈዳ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም ለእነርሱ አልተገባቻቸውምና። በየበረሓውና በየተራራው፣ በየዋሻውና በየጕድጓዱ ተንከራተቱ” (ዕብ. 11: 35-38)።



በአንጻሩ የዛሬዎቹ ነቢያት ራሳቸውን ሳይሆን ተከታዮቻቸውን ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ አሳልፎ መስጠቱን ያውቁበታል። የታመሙና የተቸገሩትን እንደ ጉም ፈጥኖ በሚጠፉ ተስፋ ሸብበው ወደ ሲኦል አፍ ይገፏቸዋል። እንደ መተተኛው ሲሞን “ታላቅ ኃይል” ተብለው ሲጠሩ በይገባኛል መንፈስ “አሜን” የሚሉ ናቸው። ከአማኞች በግፍና በአጋንንታዊ ስልት በተቀነባበረ ተዓምራዊ ተንኮል ባገኙት ገንዘብ የሚገዙት ልብስ ዕድሜያቸውን በመንከራተት እንዳሳለፉት ቅዱሳን “የበግና የፍየል ቆዳ” አይደለም። እንደቀድሞዎቹ ነቢያት በየዋሻውና በየጕድጓዱ እያንከራተተ የሚያኖር ተቃውሞ አጠገባቸውም አይደርስ።

በአገራችን የፈሉት የአሁኖቹ “ሐዋርያት” እና “ነቢያት” “ሲሞናዊ” ግርማ ሞገስ አላቸው። ምቾት በተትረፈረፈበት ፈገግታ ያጌጡ ምስሎቻቸው በትልልቅ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች በየከተማው ጎልቶ ይታያል።

እንደ ሲሞን በየመድረኩ ይደመጣሉ፤ ድርጊቶቻቸው አስደናቂና ተዓምራዊ ስለመሆናቸው የሚመሰክሩ ብዙዎች ናቸው። ሆኖም ከመተተኛው ሲሞን የማይለዩ፣ የማይጠረቁ፣ ገብጋባ የወንጌል ነጋዴዎች ለመሆናቸው በርካታ ማሳያዎች አሉ።

አይሁዳዊው ፊልጶስ ወደ ሰማርያ መሄዱ ድንቅ ነው፤ ምክንያቱም "አይሁድ ከሳምራውያን ጋር ስለማይተባበሩ ነው" (ዮሐ. 4:8)። የሰማርያ ሰዎች ወደ ወንጌል የተሳቡት ፊልጶስ ዘረኝነት በልቡ አለመኖሩን በተግባር ስላሳየ ነው። መንፈስ ቅዱስ በልቡ ያፈራው የፍቅርና የርኅራኄ ፍሬ ከሲሞን ሰይጣናዊ ታምራት እጅግ የላቀ ድንቅ ነበር። ስለሆነም የሰማርያ ሰዎችን ዓይን ጋርዶ የነበረው ሲሞናዊ ጥንቆላ ሲጋለጥ የእግዚአብሔርን እውነተኛና ታላቅ ኃይል ዓይተው ተደነቁ። ማኅበራዊም ሆነ መንፈሣዊ ችግሮቻቸውን ማስወገድ ያልቻለውን ውሸታሙን ሲሞን ተዉት፤ ሲሞንም ሲሞንነቱ እንደማያዋጣው ተገንዝቦ አዲሱን ኃይል ተመኘ።

"ነቢያት"ና "ሐዋርያት" በበዙባት ኢትዮጵያ ዘረኝነት እንደ መዥገር ተጣብቆብን ያበጠው ለምን ይሆን? ብዙ ደዌ እንፈውሳለን የሚሉት እነዚህ "መንፈሣዊያን" ይሄኛውንም ጥገኛ በሽታችንን ጊዜ ሰውተው ቢያክሙት በታሪካችን ላይ ትልቅ የፈውስ አሻራ ጥለው ማለፍ በቻሉ ነበር። በርካታ ሕዝብ ሰብስበው በተዓምሮቻቸው በማስጮህና ማስለቀስ እንችላለን የሚሉት ነቢያት አገራችን ውስጥ ለተስፋፋው ምግባረ-ብልሹነት ተከታዮቻቸውን ለምን በንስሐና ምልጃ አያስለቅሱም?




የዘመኑን ነቢያት አስመልክቶ ጌታ ጥንት ተንብዮ ነበር፤ "በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ በመግባት ከሚያሽምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ ያፈራል። … በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤' የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም። በዚያ ቀን ብዙዎች፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?' ይሉኛል። በዚያ ጊዜ፣ 'ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንት ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ' ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ" (ማቴ. 7:15-17, 21-23)።

የዛሬ ተዓምር ሠሪዎች ምን ዓይነት ፍሬ አፍርተዋል? በአስደንጋጭ ፍጥነት የተገኘ ገንዘብ፣ እጅግ ውድ የሆኑ በርካታ ልብሶች፣ ያማሩ ቤቶችና ውብ መኪናዎችን መዘርዘር ይቻላል። በመንፈስ ፍሬ አለመበልፀጋቸው ግን በእነርሱና በየዋህ ተከታዮቻቸው ብልሹ ሥራዎች ላይ በየቀኑ ይታያል።

ታዲያ መፍትሄው ምንድነው? ጴጥሮስ ለጠንቋዩ ሲሞን የሰጠው ተግሳፅ ለዛሬዎቹም "ነቢያት"ና "ሐዋርያትም" ፍቱን ምክር ነው፤ "አሁንም ስለዚህ ክፋትህ ንስሓ ግባ፤ ወደ ጌታም ጸልይ፤ ምናልባት ይህን የልብህን ሐሳብ ይቅር ይልህ ይሆናል" (ሐዋ. 8:22)።

ሁላችንም ወደ ጌታ ተመልሰን የልባችንን ሃሳብ እንዲለውጥ መፀለይ ይገባናል። ከራስወዳድነት፣ ከዝናና ከገንዘብ ፍቅር ተላቀን እውነተኛ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት እንድንችል ጌታ አምላክን መማፀን አለብን። አውቀንም ይሁን በየዋህነት የምንከተላቸውን "ነቢያት" እና "ሐዋርያት" እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች የሚታዩባቸው እንደሆነ እንመርምር። በቸልተኛነት ከተቀመጥን ግን ሰይጣን በሚቀባቸው ሲሞኖች ተወናብደን፣ ድንቆች የምንከተል ሞኞች እንሆናለን። አወዳደቃችንም እጅግ የከፋ ይሆናል። ዝው

(ድርባ ፈቃዱ)

# ሐዋርያነት፤ ዱሮና ዘንድሮ

በዘመናችን ሐዋርያ ነን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ መበራከት ስለዚህ የአገልግሎት ዘርፍ ምንነት እንድንጠይቅ ይገፋፋናል። ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ሰው ሐዋርያ የሚሆነው በምን መሥፈርት ነው? ሐሰተኛና እውነተኛ ሐዋርያ እንዴት መለየት እንችላለን? በቀድሞ ዘመንና በዚህ ዘመን ሐዋርያ መሆን ልዩነቱ ምንድን ነው? ይህ ጽሑፍ እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል።

## የቃል ፍቺ

ሐዋርያ የሚለው ቃል “አፖስቶሎስ” ከሚል የግሪክ ቃል የተገኘ ነው። ይህንኑ ሃሳብ ሊገልጹ የሚችሉ ሌሎች ሦስት ተዛማጅ የግሪክ ቃላት አሉ። እነዚህም “አፖስቴሎ”፣ “ኤክሳፖስቴል” እና “ፔምፖ” የተባሉ ናቸው። ትርጓሜያቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው “መላክ”፣ “ወደ ውጪ መላክ” እና “መላክ” የሚል ሲሆን “አፖስቶሎስ” የሚለው የግሪክ ቃል ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ “ልዑክ፣ አምባሳደር ወይም ሐዋርያ” ማለት ነው።

ይህ “አፖስቶሎስ” የሚለው ቃል የሚታወቀው ከክርስቶስ ልደት ቀደም ባሉ ጊዜያቶች በባህር ላይ ዕቃ ለማድረስ የተላከ (የሚያጓጉዝ) መርከብን በመወከል ነበር። በኋላ ላይ ግን ዕቃውን እንዲያደርስ የተላከው የመርከቧ ካፒቴን ወይም አዛዥ በዚህ ስም ይታወቅ ጀመረ። እየቆየ ደግሞ የቃሉ ትርጉም “ኃላፊነት ተሰጥቶት የተላከ ግለሰብን”፤ “ከላኪው ተልዕኮና ሥልጣን ተሰጥቶት የተላከና የተላከበትን ተልዕኮ በትክክል ይወጣል ተብሎ የሚጠበቅ” ሰውን የሚወክል ትርጉም እየያዘ መጣ። የእንግሊዝኛው “አምባሳደር” የሚለው ቃል በትክክል የዚህን ግሪክ ቃል ሃሳብ ሊገልጽ የሚችል ሲሆን፤ በመንግሥት ውስጥ በሚገኝ ከፍተኛ ባለሥልጣን አማካኝነት የተሰጠ ሹመት የሚወክልና መንግሥትን ወክሎ የላኪውን አገር ሥራ የሚያስፈጽም ኦፊሲያላዊ ከፍተኛ ልዑክ ማለት ነው።



ልክ እንደዚሁ በተመሳሳይ ትርጉም “ሐዋርያ” ማለት ግልጽ ለሆነ ተልዕኮ የተላከና ለላከው አካል መልስ መስጠት እንዳለበት ተረድቶ በሥልጣንና በተጠያቂነት ስሜት ሥራውን የሚሠራ ማለት ነው። አንዳንዶች ይህንን ቃል የቤ/ክ መሥራች፣ ባለራዕይ፣ ከፍተኛ ባለሥልጣን ወይም የሥራ መሪ እና ሚሽነሪ ከሚሉ ስያሜዎች ጋር ያዛምዱታል። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኘው ትርጉም ግን ከዚህ የዘለለ ነው።

## ስለ ሐዋርያነት ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች

በዘመናችን ባሉ የክርስቲያን ቤተ እምነቶች ሐዋርያነት ውዝግብን ከሚያስነሱ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ ነው። ክርክሩም በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ላይ ባሉ የተለያዩ ስነመለኮታዊ ትምህርት አመለካከቶች ምክንያት የመጣ ነው። እነዚህ አስተምሮዎችም ሦስት ዓይነት ናቸው። 1ኛው አመለካከት ሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከአንደኛው ምዕተ ዓመት በኋላ መሥራት አቁመዋል ሲል፣ 2ኛው ደግሞ ያቆሙት የኃይል፣ የተዓምራትና ድንቅ የማድረግ ስጦታዎች እንጂ የተቀሩት በከፊልም ቢሆን አሉ የሚል ነው። 3ኛው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አሁንም ቢሆን መሉ በሙሉ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ይገኛሉ የሚል ነው።

ስለዚህ በነዚህ አስተምሮዎች ላይ በመንተራስ የሐዋርያነትንና የነብይነትን ስጦታዎች በተመለከተ በተለያዩ ክርስቲያን ቤተ እምነቶች ውስጥ ያለውን አመለካከት ስናጠቃልለው ወደ ሁለት ማሳነስ ይቻላል። አንደኛው አስተምህሮ ሐዋርያነት እና ነብይነት በመጀመሪያው ምዕተ-ዓመት የነበሩ የመሥራችነት ስጦታዎች (ኤፌ 2፡20) ብቻ ሲሆኑ በተጨማሪም የመጨረሻው ሐዋርያ ሲሞት ስጦታነታቸው አቁሟል ይልና ከዚህም ጋር የመጀመሪያዎቹን ቤተክርስቲያናትን ለማቋቋም አብረው የተሰጡ ድንቅ የማድረግ ስጦታዎችም ሐዋርያ ከመሆን ጋር የዚያን ጊዜ አብረው አገልግሎታቸው እንዳከተመላቸው ይናገራሉ። ሁለተኛው አስተምህሮ ደግሞ እነዚህ ሐዋርያና ነብይ የመሆን ጥሪዎች አብሮአቸው ከሚሰጡ የምልክት፣ ተአምራት የማድረግና ድንቅ የመሥራት

ስጦታዎች ጋር አሁንም በቤተክርስቲያን የቀጠሉና ያልተወሰዱ ናቸው የሚል ነው። ሁለቱንም አስተምህሮዎች የሚቀበሉ ክርስቲያን ቤተ እምነቶች ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም።

አንደኛውን አመለካከት ለሚቀበሉ በዚህ ዘመን "ሐዋርያ" ወይም "ነብይ" ነኝ ብሎ የሚመጣ ማንኛውንም ሰው እንደ ሐሰተኛ የሚመለከቱት ሲሆን፤ ሁለተኛውን አመለካከት የያዙ ቤተ-እምነቶች ግን ሐዋርያነትም ሆነ የነብይነት ስጦታ አለ፤ ነገር ግን እውነተኛ መሆናቸው መፈተሸ አለበት ይላሉ (1ተሰ. 5፡21)።

## ለሐዋርያነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሐዋርያነት የሚያስፈልጉ መሥፈርቶች አሉ። እንደሚታወቀው ይህ አገልግሎት እንደማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት በዋነኛነት የመንፈሳዊና የሞራል ብቃት መሥፈርት ያስፈልጉታል። እነዚህ ተፈላጊ የሞራል መሥፈርቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥቂቶቹ በ1ጢሞ. 3፡1-7፣ በሐዋ. 6፡ 3-6ና በቲቶ 1፡ 5-9 ተዘርዝረው ይገኛሉ። ልብ ማለት ያለብን ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ዲያቆን ወይም ኤጲስ ቆጶስ ሊኖራቸው ከሚገባ የባህርይ ዝርዝር ያነሰ የሞራል መሥፈርት ለሐዋርያነት ከተመረጡት ሊጠበቅ እንደማይችል ነው።

በተጨማሪ ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ለመሆን አስቀድሞ በኢየሱስ መመረጥ፣ ኢየሱስ በምድር ላይ በሰጠው አገልግሎት አብረውት መኖርና የትንሳኤው ምስክር መሆንን (ከሞት የተነሳውን ኢየሱስን ማየት) ይጠይቃል። ሐዋርያት ከአስራ ሁለቱ ደቀመዝሙር አንዱ የነበረውን የይሁዳን ቦታ ሊተካ የሚችል ሰው ሲመርጡ በሐዋ. 1፡21-22 "ስለዚህ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፥ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል" በማለት እንደ ተፈላጊ መሥፈርት ተጠቅመው ማትያስን ከአስራ ሁለቱ አንዱ እንዲሆን መርጠውታል።

በተጨማሪም "እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም



እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤ እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን፤ እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት። እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ፤ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን" (የሐዋ. 10፡ 38-41)።

አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ለአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን መቋቋም መሠረት ናቸው (ኤፌ. 2፡20)። በሰማይ ለነርሱ የተለየ አስራሁለት ዙፋን ይኖራል (ማቴ. 19፡28)፤ በተጨማሪም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አስራ ሁለቱ መሠረቶቿ በስማቸው የተሰየሙ ናቸው (ራዕይ 21፡14)። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የአስራ ሁለቱ ሐዋርያነት ከሌሎቹ የተለየ መሆኑን ያሳያሉ።

በተጨማሪ ከአስራ ሁለቱ ውጪ ሐዋርያት ለሚሆኑ ደግሞ "ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል" (1ቆሮ. 12፡11) የሚለውን እንደ ሐዋርያ መመረጫ መሥፈርት ልብ ይሏል።

በርግጥ የጌታ ኢየሱስን ምድራዊ አገልግሎት በቅርበት ይከታተሉ የነበሩ 12ቱ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ደቀመዛሙርትም ነበሩ። ለምሳሌ በአንድ ወቅት ሁለት ሁለት አድርጎ የላካቸውን ወደ 70 የሚደርሱ ተከታዮቹን ልናስታውስ እንችላለን (ሉቃስ 10፡1፣ 17)። በተጨማሪ በዚያን ጊዜ ትንሳኤውንና ዕርገቱን የተመለከቱ ምስክሮች አምስት መቶ ይደርሱ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (1 ቆሮ. 15፡6)።

በሽተኛን የመፈወስ፣ አጋንንትን የማውጣትና ሌሎች ተዓምራትን የመፈጸም ልዩ ጸጋ፤ የሐዋርያነት ጥሪ ሲመጣ ወይም ሲሰጥ አብሮት እንደ ትጥቅ የሚሰጥ መሆኑን የአስራ ሁለቱን ሐዋርያት አገልግሎት መመልከት ብቻ በቂ

ነው። በዚህ አንጻር ማንኛውም የአገልግሎት ስጦታ ሐዋርያነት፣ ነብይነት፣ ፓስተርነት፣ ካህንነትም ሆነ አገር መምራት ከአምላክ በኃላፊነትና በተጠያቂነት የተካፈልናቸው መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሐዋርያነት በተለያዩ ሶስት ገጽታዎች ታይቷል። የመጀመሪያው ኢየሱስ "ሐዋርያ" ተብሎ መጠራቱ ሲሆን (ዕብ. 3፡1) በሁለተኛ ደረጃ አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት "ሐዋርያ" ተብለው መጠራታቸው ነው። በተጨማሪም ሌሎች ከአስራ ሁለቱ ውጪ የሆኑ አገልጋዮች "ሐዋርያ" ተብለው የተጠሩ አሉ።

"ሐዋርያ" የሚለው ቃል ትርጉሙ "የተላከ" ማለት ስለሆነና እግዚአብሔር አብ ደግሞ ኢየሱስን ወደዚህ ምድር ስለላከው፣ ኢየሱስ ራሱ "ሐዋርያ" ተብሏል (ዕብ 3፡1)፣ ኢየሱስ ደግሞ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርቶቹን "ምስክሮቼ ናችሁ" ብሎ ስለላከ እነርሱም "ሐዋርያ" ተባሉ "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ" (ዮሐ. 20፡21)፤ በመጨረሻም ቤተክርስቲያን ለተለያየ አገልግሎት የላከቻቸው አገልጋዮች ደግሞ "ሐዋርያት" ተብለዋል (2ቆሮ. 8፡23፤ ፊል. 2፡25)። ስለዚህ ይህንን የሐዋርያነት አገልግሎት በቀጥታ ከኢየሱስ ጥሪው የተሰጣቸውና በቤተክርስቲያን በኩል ጥሪው የደረሳቸው ብለን በሁለት ለመክፈል እንችላለን።

## አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ከኢየሱስ ጋር ለሦስት አመት ተኩል አብረውት በምድር ላይ ያገለገሉ ናቸው። ከኢየሱስ ጋር ከመጥምቁ ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ጀምሮ አብረውት ሲገቡና ሲወጡ የነበሩና በቀጥታ ከእርሱ ሥልጠናቸውን ተቀብለው የነበሩ ሰዎች ናቸው። በዚህም ብቻ ሳያበቃ በተጨማሪ ኢየሱስ ከሞተና ከተነሳም በኋላ የትንሳኤው የዓይን ምስክሮችም ናቸው። በዚህም ምክንያት በልዩ አኳኋን "እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ" የሚለውን ጥሪ ወይም ተልዕኮ የተቀበሉ ናቸው (ማር. 3፡14-15፤ 6፡30)።

ስለዚህ ከ12ቱ ሐዋርያት እንደ አንዱ ሆኖ ለመቆጠር በትንሹ የሚከተሉት መሥፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

- በምድር ላይ ከጌታ ጋር የነበረ
- ከሞት የተነሳውን ጌታ ያየ
- ለአገልግሎቱ የተጠራ
- የተለየ ተልዕኮ የተቀበለና
- የሐዋርያነት ምልክት በሕይወቱ የታየ የሚሉት ናቸው።

ብዙ ክርስቲያን ቤተ እምነቶች "ሐዋርያ" የሚለውን የመዓረግ ስም የማይጠቀሙት ለአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ካላቸው ክብርና ይህ ስጦታ ከአንደኛው ምዕተ ዓመት በኋላ አቁሟል ብለውም ከማመን የመነጨ ይመስላል።

## ሐዋርያው ጳውሎስ

ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ሐዋርያነቱን የተቀበለው በቀጥታ ከኢየሱስ በመጣ ጥሪ እንደሆነ ይናገራል (ገላ. 1፡1)። የአገልግሎቱ አድማስም አሕዛብን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነበር (ሮሜ. 1፡5፤ ገላ. 1፡16፤ 2፡8)።



ስለመጣለትም ጥሪ ሲናገር "ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ" ይላል። "ጭንጋፍ" ማለት "ያለ ወቅቱ የተወለደ" ማለት ሲሆን የርሱ የሐዋርያነት ጥሪ ከአስራ ሁለቱ ጋር አለመሆኑን ለመግለጽ የተጠቀመበት አገላለጽ ነው(1 ቆሮ. 15.5-8)። እርሱ እንደ ሌሎቹ አስራ ሁለት ሐዋርያት ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ከኢየሱስ ጋር አብሮ የመግባትና የመውጣት ዕድልን ያላገኘ ነበር። እንዲያውም እነዚህን የክርስቶስ ተከታይዎች ሲያሳድድ የነበረና ድንገት ኢየሱስ በደማስቆስ መንገድ ላይ ተገልጦለት "ለምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ድምጹን ከሰማ በኋላ "ለእኔ ልዩ መልእክተኛ ትሆናለህ" የሚል ጥሪ የተቀበለ ነው (1 ቆሮ. 9፡1፤ የሐዋ. 26፡16-18)። ስለዚህ የእርሱ ሐዋርያ መሆን እንደ አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት በቀጥታ ከኢየሱስ የመጣለት ጥሪ ነበር።

የጳውሎስም ሐዋርያነት እንደ እነርሱ የተለየ መልክ አለው። ጳውሎስ ራሱን ያለወቅቱ የተወለደ "ጭንጋፍ" በማለት ይጠራል (1 ቆሮ 15፡5-8)። ምንም እንኳ ያለጊዜው የተወለደ ቢሆንም የሐዋርያነት ፀጋ ተሰጥቶታል (ሮሜ 1፡5)፤ በተጨማሪም ጳውሎስ ሁሉም የሐዋርያነት ምልክቶች በአገልግሎቱ ታይተዋል። ይህም

የተሰጠውን የሐዋርያነት ሥልጣን ያጎላል። አስራ ሁለቱ ሐዋርያት እነዚህ ሊካዱ የማይችሉ የሐዋርያነት ምልክቶች፣ ድንቅና ተዓምራቶች በአገልግሎታቸው ተፈጽመዋል፤ የነዚህ ምልክቶች በአገልግሎታቸው ውስጥ መታየት አገልግሎታቸውን በጌታ ኢየሱስ ሥልጣን እየፈጸሙ መሆናቸው ማሳያ ነበር (2ቆሮ. 5፡ 20)። ይህም የተሰጣቸው ሥልጣን ቤተክርስቲያንን ለማፍረስ ሳይሆን ለመመሥረትና ለመገንባት ነው (2ቆሮ. 13፡10)።

የጳውሎስን የሐዋርያነት ጥሪ በተደጋጋሚ የሚገዳደሩ ቡድኖች እንደነበሩ አዲስ ኪዳን ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን። ለዚህም በሚመስል መልኩ ጳውሎስ ከአንድ ጊዜ በላይ ሐዋርያ መሆኑን ማስረጃ እያቀረበ ሲከላከል ይታያል (ገላ. 1፡1፤ 2ቆሮ. 1፡1፤11)። ክርክሩንም ሲቀጥል "ከእነዚህ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በአንድ ነገር እንኳ እንደ ጎደልሁ ራሴን አልቆጥርም" ይላል (11፡6)።

ድንቅና ተዓምራቶች በተለያዩ ቦታዎች በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ ተፈጽመዋል። በኤስያ (የሐዋ. 19፡ 11-12)፣ በገላትያ (ገላ. 3፡5)፣ በመቄዶንያ (1ተሰ. 1፡5፤ የሐዋ. 16፡ 16-18)፣ በቆሮንቶስ (1ቆሮ. 2፡4፤ 2ቆሮ 12፡12)፤ እነዚህ ሁሉ ድንቅ ሥራዎች የተፈጸሙት ጳውሎስ የሚያስተምረውን ወንጌል ሰሚዎቹ ከአምላክ የተላከ መሆኑን ተገንዝበው ሐዋርያነቱን እንዲቀበሉት ነበር (ገላ. 3፡5)።

አዲስ ኪዳናችንን በደንብ አድርገን ከተመለከትን ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት በተጨማሪ ጳውሎስና የኢየሱስ ወንድም (ያዕቆብ) "ሐዋርያት" ተብለው ለመጠራት ሐዋርያነታቸው ዕውቅና አግኝቶ ቤተክርስቲያንን ይመሩ እንደነበርና ሌሎችም ልክ እንደነርሱ "ሐዋርያት" ተብለው ይጠሩ እንደነበር እንረዳለን።

## ሌሎች ሐዋርያት

ሌሎች ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በቤተክርስቲያኗ በኩል ለሐዋርያነት የተጠሩ አገልጋዮች ነበሩ፤ ከነዚህም ውስጥ በርናባስ (የሐዋ. 14፡4፣14)፣ የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ (ገላ. 1፡19)፣ አንዲራኒቆንና ዩልያን (ሮሜ. 16፡7) (በነገራችን ላይ ዩልያን ወይም "ጁኒያ" የሚለው ስም የሴት ስም መሆኑ ይነገራል)፣ በተጨማሪ ሲላስና ጢሞቴዎስ በጳውሎስ "ሐዋርያ" ተብለው ተጠርተዋል (1 ተሰ. 2፡6)። ሌሎች ደግሞ ከቤተክርስቲያን ሲላኩ ወይም መልዕክት ይዘው ሲሄዱ "ሐዋርያ" ተብለዋል (ፊል. 2፡25፤ 2ቆሮ. 8፡23)።

## የሐዋርያት የሥራ ድርሻ

የሐዋርያት ዋና የሥራ ሸክም መስበክ፣ ማስተማርና ማስተዳደር ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማርና



ከመስበክ ባሻገር በማስተዳደር አገልግሎታቸው የተለያየ ግልጋሎት ይሰጡ ነበር። ከነዚህም ውስጥ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መንፈሳዊ ሕይወት መጎልበትና የበጎ አድራጎት በማከናወን ተግተዋል። እነዚህም የአምልኮን ፕሮግራም በመምራት፣ በጌታ ራት፣ በመካከላቸው የሚገኙትን ችግረኞች ለመርዳት ከምዕመናን የተሰበሰበውን ገንዘብ በማስተዳደር (የሐዋ. 3፡ 7)፣ በተለይ ይህን ገንዘብ የማሰባሰብና የማስተዳደር ሥራ ሰፊ ጊዜ የሚጠይቅ ሸክም ሆኖ ቃሉን ለመስበክና ለማስተማር ያላቸውን ጊዜ ስለተሻማ ኃላፊነቱን ለሌሎች አስተላለፉ (የሐዋ. 6፡1-6)፣ የዲሲፕሊን እርምጃ (የሥነ ሥርዓት ቅጣትም) መውሰድ (የሐዋ. 5፡1-11)፣ እየቆየም ሥራው እጅግ እየሰፋና እያደገ ሲመጣ ሐዋርያት በተለያየ አካባቢ ያለውን ሥራ መቆጣጠርና መጎብኘት ተጨማሪ የሥራ ኃላፊነታቸው እየሆነ መጥቶ ነበር (የሐዋ. 8፡14፤ 9፡32)።

ሌላ በተጨማሪ ይሰጡ የነበረው አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እጃቸውን በመጫን ለምዕመናን ያስተላልፉ ወይም ያካፍሉ ነበር (የሐዋ. 8፡15-17)። ጌታ በምድር በነበረ ጊዜ አጋንንትን እንዲያወጡና በሽተኞችን እንዲፈውሱ የሰጣቸው ጸጋ እርሱ ከሞት ተነስቶ ወደ ሰማይ ካረገም በኋላ እንኳ በሽተኞችን በመፈወስና አጋንንትን በማውጣት አገልግሎታቸው ቀጥለዋል (የሐዋ. 5፡12፤ 2ቆሮ. 12፡12)። በመጨረሻም ቤተክርስቲያኒቱ የገጠማትን የአስተምህሮት (የዶክትሪን) እና ሌሎች የአስተዳደር ግድርድሮሾችን፤ ሐዋርያት ቤተክርስቲያኑ ውስጥ ካሉ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ዴሞክራሲያዊ ሊባል በሚችል ውይይት ችግሮቹን ፈትተዋል (የሐዋ. 15፡6፤ 6፡3)።

## የሐዋርያነት መመዘኛ

የሐዋርያነት ሥጦታ መመዘኛ አለው። እነዚህን መመዘኛዎች በመጠቀም በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ላይ የነበረችው የኤፌሶን ቤተክርስቲያን በወቅቱ ራሳቸውን "ሐዋርያ" ብለው የሚጠሩ አገልጋዮችን መርምራ "ሐዋርያ" አለመሆናቸውን ስላረጋገጠች ከጌታ ኢየሱስ ምስጋናን ተቀብላለች። "ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ" (ራዕይ 2፡2)።

ከዚህ በመቀጠል እውነተኛ ወይም ሐሰተኛ ሐዋርያትን እንዴት በዘመናችን መለየት እንችላለን ለሚል ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መለያ መሥፈርቶችን እንመለከታለን።

## የእውነተኛ ሐዋርያ ምልክት

ሐዋርያነትን የተቀበለ ሰው የዲያቆንና የኤጲስ ቆጶስነትን የሞራል ዝርዝር መሥፈርት የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል። (1 ጢሞ. 3፡1-7)። ለምሳሌ የማይነቀፍ፣ በታመነ ቃል የጸና፣ ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ሊመክርና ሊወቅስ የሚችል፣ ገንዘብን የማይወድ፣ ነውረኛ ያልሆነ፣ ረብ የማይወድ እነዚህ እና ተመሳሳይ የሞራል ብቃት ዝርዝሮች ማሟላት ይጠበቅበታል።

"በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተዓምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ"(2ቆሮ. 12፡12)። "ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው" (2ቆሮ. 11፡28)።



"እነሆ፥ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ ስዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ አልከብድባችሁምም፥ እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና። እኔ ግን ስለ ነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፥ ራሴን እንኳ እከፍላለሁ። ከመጠን ይልቅ ብወዳችሁ በዚህ ልክ ፍቅራችሁ የሚያንስ ነውን?" (2ቆሮ. 12፡13-15)።

"ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን፣ ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሰው ሁሉ መጨረሻ ያሰለፈን ይመስለኛል፤ ለዓለም ሁሉ፣ ለመላእክትም ለሰዎችም ትርኢት ሆነናል። እኛ ስለ ክርስቶስ ብለን ሞኞች ነን፤ እናንተ ግን በክርስቶስ ጥበበኞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን፤ እናንተ ግን ብርቱዎች ናችሁ፤ እናንተ የተከበራችሁ ናችሁ፤ እኛ ግን የተዋረድን ነን። እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጠማለን፤ እንራቈታለን፤ እንደ በደባለን፤ ያለ መጠለያ እንንከራተታለን፤ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን። ሲረግሙን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤ ስማችንን ሲያጠፉ መልካም እንመልሳለን። እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጉድፍ፣ የምድር ጥራጊ ሆነናል" (1ቆሮ. 4፡9-13)።

ከላይ በተዘረዘሩት ጥቅሶች መሠረት እውነተኛ ሐዋርያ ሊኖሩት የሚገቡ የእውነተኝነቱ ማረጋገጫዎች በጥቂቱ ተገልጸዋል። እነርሱም የሞራል ብቃት፣ ያለነቀፋ መኖርን ጨምረው፣ በቃላቸው የሚታመኑ፣ ገበያ ተኮር ሆነው ነውረኛ ያልሆኑና ረብን የማይወዱ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በተለይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን ያስተዋሉና ይህንንም ለማስተማርና የተሳሳቱትን ለማረም የሚችሉ መሆን አለባቸው። በየቀኑ ሕይወታቸውም የምዕመናን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያሳስባቸውና የሚያስጨንቃቸው መሆን አለበት።

በአገልግሎታቸውም ምልክት፣ ድንቅና ተዓምራት እንደ እውነተኛ ሐዋርያ ምልክት ሆነው በማያሻማ መልኩ ሊታዩ ይገባል። ይህንን አገልግሎታቸውን ሲሰጡም "በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ" የሚለውን መመሪያ ተጠቅመው ነጻ ግልጋሎትን እንደነ ጳውሎስ መስጠት ይኖርባቸዋል። በሌላ አባባል አገልግሎታቸው ገንዘብ ተኮር ወይም ገንዘብን በመውደድ ወይም ጥቅምን በማግኘት ወይም አድናቆትን በመሻት መሆን የለበትም። ይህ ማለት ሐዋርያው የዕለት ተዕለት ሕይወቱን የሚመራበት ደሞዝ አይኖረውም ማለት አይደለም። ነገር ግን ምዕመናንን በገንዘብ ማስቸገር ወይም በተለያዩ ስልቶች ጥቅምን መፈለግ በሐዋርያው ሕይወት ሊታይ አይገባም። ለምዕመናን ያላቸውን ገንዘብም ሆነ ሕይወታቸውን ማካፈል እንጂ የምዕመናንን ንብረት የመቀማት

አካሄድ ሊታይባቸው በጭራሽ አይገባም። በመጨረሻም አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆነ ሕይወት ያስፈልጋቸዋል።

## የሐሰተኛ ሐዋርያት ምልክት

“ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ” (2ቆሮ. 11፡3)።

“የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ?” (2ቆሮ. 11፡3-4)። ጳውሎስ ወደ ገላትያ ሰዎች በፃፈው መልዕክት መሠረት ልዩ ወንጌል የሚሰብኩ የተረገሙ ናቸው ብሏል (ገላ. 1፡8-9)።

“የሚመካ ግን በጌታ ይመካ፤ እግዚአብሔር የሚያመሰግነው እንጂ ራሱን የሚያመሰግን እርሱ ተፈትኖ የሚወጣ አይደለምና” (1ቆሮ 10 ፡18)።

“እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና። ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል” (2ቆሮ. 11፡13-14) (በሌላ አነጋገር ጭምብል አጥልቀው ይመጣሉ ነው የሚለው)።

“ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ፥ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኰራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሡላችሁና” (2ቆሮ. 11፡20)። የዘመኑ ሐዋርያት ነን ባዮች እዚህ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው የሚታገሡና አሜን ብለው የሚቀበሉ ሳይሆኑ ትንሽ ከመስመር ያፈነገጠ የሚመስላቸውን በራሳቸው ጥበቃ ኃይሎች አፈር ከድሜ የሚያስገቡ ናቸው። “የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ” (ማር. 12፡40)።

“ምናልባት ክርክር፣ ቅንዓትም፣ ቁጣም፣ አድመኝነትም፣ ሐሜትም፣ ማሾክሾክም፣ ኩራትም፣ ሁከትም፣ ይሆናሉ፤ እንደ ገና ስመጣ በእናንተ ዘንድ አምላኬ እንዲያዋርደኝ፥ አስቀድመውም ኃጢአት ከሠሩትና ስላደረጉት ርኵሰትና ዝሙት መዳራትም ንስሐ ካልገቡት ወገን ስለ ብዙዎች ምናልባት አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ”(2ቆሮ. 12፡20-21)።

ሐሰተኛ ሐዋርያትን ከሚያሳዩት ባህርያት አንጻር ለይቶ ማወቅ ይቻላል። ከላይ በተዘረዘሩት ጥቅሶች ላይ የሚገኙ መገለጫዎችን በመጠቀም ሐሰተኛ የተባሉ ሐዋርያትን መለየት ይቻላል። በተለይ የነዚህ ሐሰተኞች ባህርይ በ 2 ቆሮንቶስ መጽሐፍ ውስጥ በተለያየ መልኩ ተዘርዝሮ ይገኛል። እነዚህም ምዕመንን በማታለል የምዕመንን ሃሳብ ማበላሸት፣ ለክርስቶስ መሰጠት ከሚገባው ቅንነትና ንጽህና ምዕመንን ማደናቀፍ፣ እውነተኞቹ ሐዋርያት ከሰበኩት ውጪ ሌላ ኢየሱስ እና ሌላ መንፈስ ያለበትን ሌላ ወንጌል መስበክ፣ ራስን በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ከፍ (ፕሮሞት) ማድረግ፣ በሰው ዘንድ ማንኛውም የክርስቶስ ሐዋርያ ሊያስብላቸው የሚያስችል፤ የጽድቅ አገልጋይ የሚያስብል ጭንብል ማጥለቅ፣ ሰዎችን ባሪያ አድርጎ መጠቀም (ካዳሚ ማድረግ)፣ ገንዘባቸውን በተለያየ ዘዴ መቀማት፣ ኩራት፣ ርኩሰትና ዝሙት የመሳሰሉት የሚታይባቸው ነው።

## የዱሮና የዘንድሮ ሐዋርያት ንጽጽር



እስከ አሁን ስለ ሐዋርያና ሐዋርያነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ መልኩ ጥናት አድርገናል። ከዚህ በመቀጠል በዚህ ዘመን ራሳቸውን “ሐዋርያ” ብለው በሚጠሩና የጥንት ዘመን ሐዋርያት መካከል ያሉትን ልዩነቶች በንጽጽር መልክ ለመረዳት እንሞክራለን።

የድሮዎቹ ሐዋርያት የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚገነቡና የሚያሰፉ ሲሆን፤ በሚገርም መልኩ የዘንድሮዎቹ የራሳቸውን መንግሥት የሚገነቡና ስለ ባንክ አካውንታቸው ገንዘብ መጠን እጅግ የሚጨነቁ ሆነው ተገኝተዋል። የአገልግሎታቸውም ትኩረት “ገበያ መር እና ጥቅም ተኮር” ነው። ጳውሎስ ራሱን ከሐሰተኞች ሐዋርያ/ወንድሞች ጋር በማነጻጸር እንደሚነግረን እኛ “የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን” (2 ቆሮ. 2፡ 17)።

እውነተኛው ወንጌል “ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው” (1 ጢሞ. 6፡6) ሲል፤ የዘንድሮዎቹ አገልጋዮች ግን ገንዘብን ማትረፊያ አድርገውታል። ድሮ ሐዋርያት “ሞኝ”፣ ምዕመኑ ደግሞ ተጠቃሚ (ብልጥ) ነበር። ዘንድሮ ግን በተገላቢጦሽ ሐዋርያት ብልጥ ምዕመኑ ግን ሞኝ መሆኑ የሚያስገርም ነው። የአንድ አገር መሪ እንደተናገሩት ድሮ ኢየሱስ አምስት ሺህ ሰዉ መገበ፤ ዘንድሮ ግን አምስት ሺህ ምዕመናን አንድ አጭበርባሪ ሐዋርያ ነኝ ባይ የሚመግቡ መሆኑ ያሳዝናል ብለዋል።

በሐሰተኛ ሐዋርያት የተታለለ ምዕመን ስለ ክርስቶስ ቅንነትና ንጽህና ያላቸው ሃሳብ ሊበላሽ ይችላል። በ2 ቆሮንቶስና በገላትያ መልዕክቶች ሐሰተኛ ሐዋርያት የሚሰብኩት ወንጌል “ልዩ ወንጌል” ተብሏል፤ በዘመናችን ደግሞ በሐሰተኛ ሐዋርያት እየተሰበከ ያለው “የብልጽግና ወንጌል” ሲሆን ይህንንም በጳውሎስ ጊዜ እንደተነገረው “ልዩ ወንጌል” በማለት ሊጠራ ይችላል። እውነተኛ ሐዋርያ በሚሠራው ሥራ ምስጋናውን የሚቀበለው ከእግዚአብሔር ነው፤ ሐሰተኛ ሐዋርያ ግን ራሱን ያመሰግናል፣ ያስመሰግናል፣ ራሱንም በመደጋገም ከፍ ከፍ ያደርጋል። በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሐዋርያ የሚባሉ እንዳሉ ሁሉ ውሸተኞች ሐዋርያትም አሉ። የጽድቅ ባሪያዎች የተባሉ እንዳሉ ሁሉ ጭንብል ያጠለቁ፣ ራሳቸውን የብርሃን መልአክና የጽድቅ አገልጋዮች አስመስለው ለማጭበርበር እንዲመቻቸው “የበግ ለምድ” የለበሱ ሐዋርያት ይገኛሉ። ምዕመኑንም ከክርስቶስ ባሪያነት ወደ ሐሰተኛ ሐዋርያ ካዳሚነት ይለውጣሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምዕመናን “አልከብድባችሁም” በማለት ራሱን በፋይናንስ እየደገፈ ሲያገለግል ነበር። በአገራችን ፈልተው የሚገኙት የዘመናችን ሐሰተኛ ሐዋርያት ግን ትኩረታቸው ገበያ መርና ጥቅም ተኮር በመሆኑ



የብዙዎችን “ቤት ይበላሉ፣ ይቀማሉ”፤ “ነውረኛ ረብ የሚወዱ” ናቸው። እውነተኛ ሐዋርያ እንደ ጳውሎስ ራሴን እንኳ እከፍላለሁ ሲል ሐሰተኛ ሐዋርያ ደግሞ በቅጥረኝነት (በሞያተኝነት) መንፈስ የሚመላለስ ነው። የዘመናችን አጭበርባሪ ሐዋርያት ገንዘብ ካጡ ሥራውን አይሠሩም፣ ምዕመኑንም ከአደጋ አይጠብቁም።

በቅርቡ ለአገልግሎት የተጠራ አንድ ሰው “መጀመሪያ አካውንቴ ላይ አራት መቶ ሽህ ብር አስገቡ” ማለቱ ተደምጧል ። “መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል” (ዮሐ. 10፡11-13)።

እንደ ጳውሎስ ያለ እውነተኛ ሐዋርያ ግን አገልግሎቱ በተለያየ ግድርድሮሽ ውስጥ ቢያልፍም እንኳ በጽናት ይፈጽመዋል። እንደ ተቀጣሪና ችግር ሲመጣ ዞር እንደሚሉት ሳይሆን መከራን እየተጋፈጠም ያገለግላል። እንደሚታወቀው ቅጥረኛ አደጋ በመጣ ጊዜ በጎቹን በፍጥነት ትቶ ይሄዳል (ዮሐ 10፡12፤ የሐዋ. 20፡29-30)። በተጨማሪም ሮሜ 16፡18 ሐሰተኞችን እንደዚህ በማለት ይገልጻል፤ “እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፥ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ”።

ዘመኑ የከፋ ሆኗል። ሰዎች በግፍ ላይ ግፍ የሚፈጽሙበትና ለዚህም ደግሞ ሃይማኖትን መደበቂያ ያደረጉበት ዘመን ነው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በማንበብ ለራሳቸው እውነትን ከማወቅ ይልቅ በሃሰተኛ ሐዋርያት ከንቱና ስሜትን ብቻ የሚነካ ንግግር ትኩረት በመስጠት ወደ ጥፋት እየተነዱ ነው። እጅግ በርካታ መረጃዎች እየወጡ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እየተናገረ ቢሆንም ሰዎች አሁንም ራሳቸውን ለስህተት ትምህርት አሳልፈው በመስጠት በጥፋት ጎዳና እየነጎዱ ነው። በማጭበርበርና በመረጃ ለሚደረግ ተዓምራትና ፈውስ ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውንም እያጡ ነው።

ስለዚህ እነዚህንና ከላይ የዘረዘርናቸውን ነጥቦች ልብ በማለት ራሳችንንና ወንድም እህቶቻችንን ሊያሳስቱ ከተነሱ ሐሰተኛ ሐዋርያት ልንጠነቀቅ ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይመክረናል፤ “ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ” (ኤፌ. 5፡16)። ዝዉ

(ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ)

**ዋቢ መጻሕፍት**

ለዚህ ጽሁፍ በዋቢነት የተጠቀሱት በገጽ 20 ላይ “ነቢያት፤ ድሮና ዘንድሮ” ለሚለው ጽሁፍ የተጠቀሱት ናቸው።

# በልሳን መናገር፡ ትርጉምና አጠቃቀሙ

## ልሳን ምን ማለት ነው?

አዲስ ኪዳን የተፃፈው በግሪክ ቋንቋ ነው። በግሪክኛ ግሎሳ (γλῶσσα) የሚለው ቃል ነው በአማርኛ "ልሳን" ተብሎ የተተረጎመው። ግሎሳ ቀጥተኛ ትርጉሙ ምላስ ሲሆን፤ ሁለተኛ ትርጉሙ ደግሞ ቋንቋ ነው።

## ልሳን ለቤተክርስቲያን የተሰጠው ለምንድነው?

ጌታ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱን እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡19)።

ጌታ ይህን በተናገረበት ጊዜ፤ ደቀመዛሙርቱ የዓለምን ሕዝብ ለማስተማር የሚያስችል የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች አልነበሩም። በዚህ ምክንያት ነው ጌታ "የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል … በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ" ያለው (ማር. 16፡17)።

በአዲስ ቋንቋ/ልሳን መናገርን በተመለከተ በጥቅሱ "እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል …" የተባለው ደቀመዛሙርቱ በፊት ባልተናገሯቸው ቋንቋዎች በተዓምራዊ መንገድ (ያለ ጥናት) መናገር ስለጀመሩ ነው።

## ቃሉ በልሳን ስለተናገሩ ሰዎች ምን ይላል?

በልሳን ስለተናገሩ ሰዎች በሐዋርያት ሥራ ላይ ሶስት ቦታዎች ላይ ተፅፏል። (ሐዋ. ሥራ 2፣ 10፣ 19) እነዚህን ታሪኮች መመልከት ስለ ልሳን ጠቃሚ ግንዛቤ ይሰጠናል።

"የበዓለ ኀምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድነት፣ በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ነበር፤ ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው። የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር" (ሐዋ. ሥራ 2፡1-4)።

ወንጌልን ማሰራጨት ቋንቋን በመናገር ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው መንፈስ ቅዱስ በእሳት ምላሶች አምሳያ የተገለጠው። እሳቱ የወንጌልን ኃይል የሚያመላክት ሲሆን ምላሶቹ ደግሞ የንግግር ወይም የቋንቋ ብቃትን ያመላክታሉ።



ይህ በተከሰተበት በበዓለ ኀምሳ ቀን፤ "ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ። ይህን ድምፅ ሲሰሙ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤ እያንዳንዱም ሰው፣ ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ በመገረምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፤ 'እነዚህ የሚነጋገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ፣ **እያንዳንዳችን በተወለድንበት፣ በራሳችን ቋንቋ ሲናገሩ** የምንሰማቸው እንዴት ቢሆን ነው? እኛ **የጳርቴና**፣ **የሜድ**፣ **የኢላሜጤ**ም ሰዎች፣ በ**መስጴጦምያ**፣ **በይሁዳ**፣ **በቀጰዶቅያ**፣ **በጳንጦስ**፣ **በእስያ**፣ **በፍርግያ**፣ **በጵንፍልያ**፣ **በግብፅ**፣ **በቀሬና** አጠገብ ባሉት **በሊቢያ** አውራጃዎች የምንኖር፣ **ከሮም** የመጣን አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን፣ **የቀርጤስ**ና **የዐረብ** ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን!'" (ሐዋ. ሥራ 2፡5-11)።

በዓለ ኃምሳ ከፋሲካ በኋላ ኃምሳ ቀናት ተቆጥረው በኃምሳኛው ቀን ላይ የሚከበር ከአይሁዳውያን ሰባት በዓላት መካከል አራተኛው ነው። ይህንን በዓል ለማክበር አይሁዳውያን ከተለያዩ ቦታ ተሰባስበው በነበረበት ጊዜ ነው ደቀመዛሙርት በተሰበሰቡት ሰዎች ቋንቋ ሲናገሩ የነበረው።

ከላይ የተጻፈው ጥቅስ በግልፅ እንደሚናገረው ለበዓሉ የተሰበሰቡት ብዙ ሰዎች ወንጌልን በተወለዱበት ቋንቋ እንደሰሙ ነው። ሐዋርያት የተጠቀሚቸውን ቋንቋዎችም ዘርዝሮልናል። በልሳን የመናገሩም ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ለማሰማት መሆኑም ይታያል።

የልሳን ስጦታ የታየበት ሁለተኛ ክስተት ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ወንጌልን በሰበከበት ጊዜ ነው።

“ጴጥሮስ ይህን እየተናገረ ሳለ፣ ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። ከጴጥሮስ ጋር የመጡት፣ ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ ይኸውም በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ስለ ሰሚቸው ነው” (ሐዋ. ሥራ 10:44-46)።

ቆርኔሌዎስ የኢጣሊያ ሰው ነበር (ሐዋ. ሥራ 10:1)። ጴጥሮስ ደግሞ አይሁድ ስለነበር በቋንቋ ላይግባቡ ይችል ነበር።



መንፈስ ቅዱስ ሲፈስባቸው ግን አሕዛብ የሆኑት ኢጣሊያውያን እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ አይሁዶቹ ሰሚቸው።

ይህ የሆነበትን ምክንያት ጴጥሮስ ሲገልፅ እንዲህ ብሏል፤ “መንፈስ ቅዱስ፣ በመጀመሪያ በእኛ ላይ እንደ ወረደ ሁሉ በእነርሱም ላይ ወረደ” (ሐዋ. ሥራ 11:15)። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በነጴጥሮስ ላይ በበዓለ ኃምሳ ቀን ሲወርድ በሚስተዋል የሰው ቋንቋዎች ደቀመዛሙርት እንደተናገሩ ተመልክተናል። በነቆርኔሌዎስ የወረደው መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኃምሳ ከወረደው የተለየ ለመሆኑ ምንም የቀረበ መረጃ የለም። አሕዛብ ወደ ክርስትና መምጣታቸውን ለመቀበል ይጠራጠሩ ለነበሩት አይሁዶች ይህንን ክስተት በነቆርኔሌዎስ ላይ ሲወርድ መመስከራቸው ጥርጥራቸው ያቀለለላቸው እንደሆነ እንረዳለን።

በቀጣይ ሐዋርያው ጴጥሮስ የአሕዛብን ጉዳይ አንስቶ ሲናገር “ልብንም የሚያውቅ አምላክ ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን መንፈስ ቅዱስን በመስጠት መሰከረላቸው፤ ልባቸውንም በእምነት ሲያነጻ በእኛና በእነርሱ መካከል አንዳች አልለየም” ብሎ ነበር (ሐዋ. ሥራ 15:8-9)። የነቆርኔሌዎስና የዘመዶቹም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አልነበረም።

ሶስተኛው ልሳንን አስመልክቶ ቃሉ ላይ የምናየው ታሪክ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ከአስራ ሁለት የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ጋር ባደረገው ቆይታ ወቅት የተከሰተ ነው።

“ጳውሎስም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ” (ሐዋ. ሥራ 19:6)።

በኤፌሶን የሆነውም ነገር አዲስ ክስተት አለመሆኑ በቃሉ በግልፅ ተጽፎ እናነባለን።

## ሐዋርያው ጳውሉስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ልሳን ምን መክሯቸው ነበር?

የቆሮንቶስ ከተማ በልቅነትና በፍትወት የታወቀች ነበር። ይህ ልቅነት ደግሞ ከተራ ሕይወት አልፎ በባዕድ አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ስለነበረው ብዙ የከተማይቱ ዜጎች በርኩሰት ተተብትበው ነበር። በከተማይቱ በስፋት የነበረው ምግባረብልሹነት በአንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አባላትም ሕይወት ላይ ይታይ እንደነበር የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ያሳያል (1 ቆሮ. 5:1-2)።

የቆሮንቶስ ከተማ ከልዩ ልዩ አገራት የመጡ ሰዎች የሚኖሩባት በርካታ የንግድ ልውውጥ የሚካሄድባት ታዋቂ የወደብ ከተማ ነበረች። ስለሆነም የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የቋንቋዎች ወይም የልሳን ስጦታ ያስፈልጋት ነበር። ሆኖም የቆሮንቶስ ሰዎች የተቀበሉትን የልሳን ስጦታ ስርዓት በሌለው መንገድ ይጠቀሙ እንደነበር ጳውሎስ ይናገራል።

“እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ፣ በመግለጥ ወይም በዕውቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ በልሳን ብናገር ምን እጠቅማችኋለሁ? እንደ ዋሽንትና እንደ በገና ያሉ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች እንኳ የድምፃቸው ቃና ልዩነት ከሌለው ዜማቸውን እንዴት ማወቅ ይቻላል? ደግሞም መለከት ትክክል ያልሆነ የጥሪ ድምፅ ካሰማ፣ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል? እናንተም እንደዚሁ ናችሁ፤ ከአንደበታችሁ ትርጒም ያለው ቃል ካልወጣ፣ የምትናገሩትን ማን ሊያስተውለው ይችላል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁ”(1 ቆሮ. 14:6-9)።

የቆሮንቶስ አማኞች የልሳን ስጦታ ዋና ዓላማ የወንጌልን ደስታ ለሌሎች ማሳወቅ መሆኑን ረስተው ራሳቸውን ብቻ ወደማስደሰት አዘንብለው ነበር። ይህ ግን ትክክል እንዳልሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ይናገራል። ትርጉሙ የማይስተዋል

ነገር ማውራት ለነፋስ ከመናገር አይለይም፤ በዚህ መንገድ ተናግሮ ጉባዔውን ከማወክ ዝም ማለት እንደሚሻልም ይመክራል።

“ነገር ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተማር፣ ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ፣ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር ይሻላል” (1 ቆሮ. 14:19)።

የቆሮንቶስ ሰዎች ከስነሥርዓት ውጪ፣ ሳይጠባበቁ፣ በመንጋጋት ይናገሩ ነበር። ሁሉም ተናጋሪ በሆነበት ጉባዔ ውስጥ ብዙ ትምህርት መቅሰም አይቻልም። ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን፣ ለዘመናችንም ፍቱን የሆነ ምክር ሰጠ።

“በልሳን የሚናገር ቢኖር፣ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት በየተራ ይናገሩ፤ ሌላው ደግሞ ይተርጉም፤ የሚተረጕም ሰው ከሌለ ግን በጉባኤ መካከል ዝም ይበልና፤ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር” (1 ቆሮ. 14:27-28)።

## በአንዳንድ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ዛሬ የሚታየው ልሳን 1 ቆሮንቶስ 14 ላይ የተጠቀሰው ነው?

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ እንዲህ ይላል፤ “በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለ ሚናገር የሚረዳው የለም” (1 ቆሮ. 14፡2)።

በዚህና በሌሎቹም ምክሮቹ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ልሳን ሲናገር የተጠቀመው ቃል “ግሎሳ” (γλῶσσα) የሚለውን ነው። ይህ ቃል “ቋንቋ” ማለት ስለሆነ፤ አንድ ሰው በመንፈስ ሆኖ ምስጢር ሲናገር የሚረዳው ባይኖርም በቋንቋ እየተናገረ ነው ማለት ነው። ምሥጢር ቢሆንም ግን ልሳኑ በባሕርዩ የሥነቋንቋ፣ የቃላት ትርጉም፣ አጠቃቀምና የሰዋሰው ሕጎችን የሚከተል መግባቢያ ነው እንጂ ከዚያ የተለየ አይደለም።


በኮንጎ አንዲት ሴት “በልሳን” ስትናገር፤ the New York Times Nov. 7, 2006

ቋንቋዎች ሁሉ የሚከተሏቸው መሠረታዊ ሕግጋት አንድ አይነት እንደሆኑ የሥነቋንቋ ተመራማሪዎች ይመሰክራሉ። ሌሎች ቋንቋዎችን ለመማር የሚያስችለው ጥበብ ያለንም፤ የምንናገራቸው ቋንቋዎችና የማንናገራቸው ቋንቋዎች የሚጋሩት የሰዋሰው መሠረት ስላለ ነው። ስለሆነም በስመ “ልሳን” ሌሎች የማይረዷቸውን ጥቂት ቃላት በመደጋገም የጠለቀ ምሥጢራዊ መልዕክት ማስተላለፍ እንደማይቻል አምላክ እንድናገናዝብ የቸረን አእምሮ ሊያስተውል ይገባል። ይህ ከሆነ በየቤተክርስቲያናቱ “ልሳን” እየተባለ የሚሰማው የተጠና የሚመስለው ድግግሞሽ በየትኛው የቋንቋ ህግ ነው መንፈሳዊ ምሥጢር የሚያስተላልፈው? ትርጉም አልባ የማይገባና የማይስተዋል ተደጋጋሚ የቃላት ናዳ በአምልኮ ውስጥ አላስፈላጊ መደናቆር የሚፈጥር አሳዛኝ ክስተት ነው።

“እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም። በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲሁ ነው” (1 ቆሮ. 14:33)።

ብዙ ጊዜ ሰዎች በልሳን እንናገራለን የሚሉባቸው ቦታዎች ላይ ሥነ ሥርዓት የለቀቀ መደናገርና ሁከት ይታያል። በሐዋርያት ሥራ ላይ የልሳን ስጦታ በጌታ ክርስቶስ የማያምኑትን ወደ ወንጌል እውነት እንደሳበ ከላይ ተመልክተናል። የዘመኑ ልሳን ግን በማያምኑት ዘንድ ቤተክርስቲያንን ትዝብት ላይ የጣላት ለምንድነው? የሰላም አምላክ ሦስትና አራት እንግዳ ቃላት እየደጋገሙ በሁከት ከሚፈነጩ ግለሰቦች ጋር ኅብረት አለው? የእግዚአብሔር ቤትና አምልኮስ በእንዲህ ዓይነት ሁከት በተቀላቀለበት ሁኔታ መመራት አለበት?

“በልሳን የሚናገር ቢኖር፣ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት በየተራ ይናገሩ፤ ሌላው ደግሞ ይተርጉም፤ የሚተረጕም ሰው ከሌለ ግን በጉባኤ መካከል ዝም ይበልና፤ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር (1 ቆሮ. 14፡27-28)።

ሕጻናት ተራ ጠብቆ መናገር ይከብዳቸዋል፤ ስለዚህ ተራ ጠብቀው እንዲናገሩ ትምህርት እንሰጣቸዋለን። አዋቂዎች ግን በእግዚአብሔር ቤት ተንጋግተው ሲጮሁ መስማትና ማየት ፍጹም ሊስተዋል የሚችል ጉዳይ አይደለም። ጥንት ቤተክርስቲያን የምትታወቀው ለጸሎትና ጽሞና በምትሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ነበር። ጳውሎስ “ቢበዛ ሦስት” ሰዎች ብቻ በልሳን እንዲናገሩ የመከረው ለዚህ ነው። የሚተረጉም ከሌለ ደግሞ ዝም ማለት ይሻላል ብሏል። ይህን የተናገረው ቅዱስ ጳውሎስ በድምጽ ማጉያ የሚሰማውን የማያቋርጥ ጉራማይሌ ቢሰማና፤ የጦርነት ብጥብጥ የሚመስለውን ጉባዔያዊ ነውጥ ቢያይ ምን ይል ይሆን?

“በምትሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳንዱ መዝሙር አለው፤ ትምህርት አለው፤ መግለጥ አለው፤ በልሳን መናገር አለው፤ መተርጐም አለው። ይህ ሁሉ ግን ለማነጽ ይሁን” (1 ቆሮ. 14፡26)።

ዛሬ ቤተክርስቲያን የሚያንጽ መዝሙር፣ ትምህርት፣ መግለጥና ልሳን ትፈልጋለች። በኢትዮጵያ ልሳን የሚባለው ሥጦታና ሌሎች መንፈሣዊ ርኩሰቶች በተመሳሳይ ፍጥነት እየተስፋፉ ነው። የሚያንጽ ልሳን ካለ መረን የለቀቀ ግፍ፣ ብልግና፣ ሌብነትና ሥርዓት አልበኝነት ለምን ምድራችንን ወረሱብን? መንፈስ ቅዱስ የቋንቋን ስጦታ አበርክቶ የልብ ንጽህና ስለነፈገን ነው? መቅደም ያለበት ስጦታ የቋንቋ ጥበብ ነው ወይስ ለጌታ የሚታዘዝ ትሁት ልብ?

እግዚአብሔርን እናምናለን ካልን፤ ሁከት በማያውቀው መንፈስ ቅዱስ ምሪት ወደሚያንጽ እውነትና ሕይወት መድረስ አለብን።

ስለዚህ በ፣ኛ ቆሮንቶስ 14 ላይ የተጠቀሰው በተመለከተ የሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ እንችላለን፤

**1ኛ** ይህ “ልሳን” ተብሎ የተጠቀሰው በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደተጻፈው “ግሎሳ” ወይም የሥነቋንቋ እና የሰዋሰውን ሕግ የተከተለ ቋንቋ ነው፤

**2ኛ** በጉባዔ መካከል “ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት በየተራ” ሊናገሩ ይገባቻዋል፤

**3ኛ** የሚነገረው ልሳን መተርጎም አለበት፤

**4ኛ** “የሚተረጉም ሰው ከሌለ” ልሳን ተናጋሪው “በጉባዔ መካከል ዝም ይበል”፤

**5ኛ** ልሳን ይነገራል በሚል ሁከት ሊፈጠር አይገባም፤ እግዚአብሔር የሁከት ሳይሆን የሰላም አምላክ ስለሆነ አምልኮውም እንዲሁ በሰላምና በሥርዓት መካሄድ ይገባዋል።

## ስለ ዘመናችን ልሳን ታሪካዊ አመጣጥ ምን ማለት ይቻላል?

ባለንበት ዘመን በልሳን እንናገራለን የሚሉ ሰዎች በሚስተዋል ቋንቋ ሲያወሩ አይደመጡም፤ በቆሮንቶስ እንደታየው ሁሉም ሰው ሊባል በሚችል ሁኔታ በአገልግሎት ጊዜ ሳይጠባበቁ፣ ያለ ተራ ሲናገር ይሰማል ። እንዲህ ያለውን ትርጉም ዓልባ ቃላት ድግግሞሽና ጩኸት ከአምላክ የመጣ ስጦታ ነው ብሎ መቀበል ያዳግታል።

ልክ እንደ ዛሬዎቹ የልሳን ተናጋሪዎች በአምልኮ ፈንጠዝያ ሰክረው በሚያደናግር ቋንቋ የሚያወሩ ሰዎች ጥንትም ነበሩ። ክርስቶስ ከመወለዱ ስድስት መቶ ዓመታት በፊት ሜዲቴራኒያን ዙሪያ ባሉት አገራት በፓርናሱስ ተራራ ሥር ዴልፊ በተባለው አምላክ ስም ለተራ ሰው በማይገባ ቋንቋ ምስጢር ይናገራሉ የሚባልላቸው ካህናት ነበሩ። ይህ አምላክ ከስካር፣ ከሚያነቃቃ ሙዚቃና ከብልግና ጋር ትሥሥር ነበረው።



በዴልፊ አምልኮ ሥርዓት ላይ አስደሳች ሙዚቃ ከቀረበ በኋላ ሊቀካህኗ በመጠጥና በአምልኮ ስካር ተንቀጥቅጣ፣ ራሷን መቆጣጠር ይከብዳትና “በመንፈስ” መናገር ትጀምራለች። ንግግሯን የሰሙ ካህናት ትርጉሙን በግጥም መልክ ለተሰበሰቡት ሰዎች ያሳውቃሉ። መልዕክቱ ደግሞ አፖሎ ከተባለው አምላክ እንደመጣ ተደርጎ ይቆጠራል።

እንዲህ ዓይነቱ ከአምልኮ ጋር የተያያዘ ጩኸትና ትርጉም የለሽ ንግግር በብዙ የባዕድ አምልኮ ውስጥ ዛሬም ይታያል። በአፍሪቃዊው የቩዱ አምልኮ ሥርዓትና በአንዳንድ የኢትዮጵያ ልማዳዊ የጥንቆላ ዕምነቶችም ውስጥ በ“መንፈስ” ተይዞ የመጮህ ልማድ እንዳለ ይታወቃል። በተለምዶ ዛር ወረደ፣ ውቃቢው ተነሳ፣ ወዘተ በመባል የሚጠቀሱት ከዚህ ጋር ተያያዥነት አላቸው።

ይህ ዓይነቱ ልምምድ ወደ ፕሮቴስታንት ዕምነት የገባው በሃያኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ አካባቢ ነው። ከጀማሪዎቹ ዋና የሚባለው የሎሳንጀለስ ከተማ ነዋሪ የነበረው ዊልያም ሲሞር የተባለ ሰባኪ ነው (ምንጭ፡Azusa Street Revival)። ክርስቲያን ሁሉ በልሳን መናገር አለበት በሚል እሳቤ የተነሳው ዊሊያም፤ ወንጌል ከሚያዘው የቅድስና ሕይወት ወጣ ያሉ፣ በጥራዝ ነጠቅ ጩኸትና የእንግዳ ቃላት ጋጋታ ሰላም የሚነሱ ጉባዔዎች መብዛት ምክንያት ሆኗል። ይኸው ልምምድ እየተሻሻለና እየረቀቀ በመሄድ አሁን ድረስ የመንፈስ ቅዱስ መገለጫ ተደርጎ በተግባር ሲውል ይስተዋላል።

የወንጌል እውነት አንድ ናት። በሚያደናግር ቋንቋ መጮህና መዘለል፤ ሁከት የማያውቀውንና ሥርዓትን የሚወደውን እግዚአብሔርን አያስከብርም። አምላካችን የስነሥርዓት ጌታ ነው። ባለንበት ዘመን የሚያስፈልገው ራስን ወደመቆጣጠርና ፈተናን ማሸነፍ ወደሚያስችል ፅሞና ውስጥ መግባት ነው። ከሚያስጮኸው መንፈስ ይልቅ ኃጢአትን የማሸነፍ ኃይልና ትህትና የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ይሻለናል። ጊዜው (ድርባ ፈቃዱ)

# ብልጽግና ወይስ ዕረፍት?

አስጨናቂው የዚህ ምድር ኑሮ ሰዎችን ከሰብዓዊ ባህርይ በማስወጣት ሊታሰብ በማይችል የሕይወት መስመር ውስጥ ሲከታቸው ይስተዋላል። “የቸገረው እርጉዝ ያገባል፤ ጫን ያለበትም እመጫት” እንደሚባለው፤ ሰው ሲቸግረው፣ ሲጨንቀው፣ መግቢያ መውጫው ሲጠፋበት፤ የኑሮ ማዕበል ሲያላጋው፤ ወጀቡ ሊደፍነው ሲደርስ አድርግ የተባለውን ብቻ ሳይሆን ያልተጠየቀውንም ለመፈጸም ብዙ ርቀት ይሄዳል። ጠንቋይ፣ አዋቂ፣ ወዘተ ቤት በመሄድ፤ ገብር የተባለውን በመገበር ከችግሩ ለመላቀቅ፤ ሸክሙን ለማራገፍ ሄዶ ሌላ ችግር፣ ሌላ ሸክም ተሸክሞ ይመጣል። የፈለገው ቢሳካለት እንኳን እንዴት እንዳገኘው ስለሚያውቅ በአንድ በኩል ያዝኩት ያለውን መልሶ እንዳያጣው በሌላ ደግሞ እንዴት እንዳገኘው ሰዎች እንዳያውቁበት ለመሸፈን በሚያደርገው የሚከሰተው የኅሊና ጭንቀት ሌላ ዕረፍት የሚያሳጣ ጉዳይ ይሆናል። ይህም “መፍትሔ” የሚባለውንም አግኝቶ እንኳን በማያቋርጥ የችግር አዙሪት ውስጥ እንደሚገባ የሚሳይ ነው።



ወጣቱ ልጅ አንድ አዋቂ ነው የሚባል ሰው ዘንድ ሄዶ “የወደፊት ሕይወቴ ምን እንደሆነ ለማወቅ ፈልጌ ነው” ይላል። ጠንቋዩም “ሠላሳ ዓመት እስኪሞላህ በድህነት፣ በስቃይና በመከራ ትኖራለህ” ይለዋል። ልጁ 29ኛው ዓመት ላይ ነበረና አንድ ዓመት ነች የቀረችን በሚል ተደስቶ “ከዚያስ፤ ከ30ኛው ዓመት በኋላ፤ ሕይወቴ ምን ይመስላል?” በማለት በተስፋ ሲጠይቅ “አዋቂው” መልሶ “ከዚያማ ችግርህን ትለምደዋለህ” በማለት መለሰለት።

በዚህ ምድር ሳለን ችግር ቢያጥቡት እንደማይጠራ ሽንፍላ ነው። አበቃ፣ ከችግር ነጻ ሆንሁ የምንልበት ዘመን ሳይኖር ነው የዚህች ምድር ሕይወታችንን የምናጠናቅቀው። በተለያዩ መንገዶች ለችግሮቻችን ማቃለያ ያገኘን ቢመስለን እንኳን የችግር አዙሪት ግን አይፋታንም። መፍትሔ ችግርን የሚወልድ እየሆነ በመቀጠል ዕረፍት ዓልባ ሕይወት በሁሉም የኑሮ ዕርከን ላይ የሚገኝ ሰው ነባራዊ እውነታ ነው። ድሃው መፍትሔ ዓልባ ሕይወት የሚኖር ይመስለዋል። ብዙ ሃብት ያካበተውን ደግሞ ችግር ዓልባ ኑሮ የሚኖር ቢመስለንም ሌሎች በርካታ ሃብት ወለድ ችግሮች ሰንገው እንደያዙት እንዘነጋለን። በጣም ጥቂቶች ግን በማግኘትም ቢሆን በማጣት ሲቅበዘበዙ አይታዩም። ምሥጢሩ ምንድነው ብለን ብንጠይቅ፤ ምላሹ መስከን፣ መረጋጋትና ማረፍ ሆኖ እናገኘዋለን።




በአሁኑ ጊዜ በባዕድ አምልኮነት የምናውቀው ማጭበርበርና ጥንቆላ በክርስትና ስም መልኩን ቀይሮ የወቅቱ እውነታ እየሆነ መምጣቱ እጅግ የሚረብሽ ነው። በአሠራሩ ከጥንቆላ በምንም ያልተለየው የዘመኑ የብልጽግና ወንጌልና የሃሰተኛ ነቢያት፣ ሐዋርያትና መሰል ግለሰቦች ተግባር ብዙዎችን እያታለለ ያለው በእግዚአብሔር ስም የሚካሄድ በመሆኑ ነው። አንዳንዴም በረቀቀና በተጠና ሥልት ለሰዎች ችግር ቅጽበታዊ ምላሾች መሰጠታቸው ሌላው ማሳሳቻ ነው። ወደ እነዚህ ቦታዎች የሚሄደው ሕዝብ አገኘሁ በሚለው ነገር እንኳን ተማምኖ ለመቀመጥና በሕይወቱ ለመርካት እያቃተው ደጋግሞ ወደተለያዩ ቦታዎች ለተመሳሳይ ተግባር ሲኀርፍ ይስተዋላል። ዕረፍት እና ሰላም “በአዋቂ” አይመጣም። የብልጽግና ወንጌል አስተምህሮ፣ የዘመናችን “ነቢያት” እና “ሐዋርያት” ሳይሆኑ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ነው ዕረፍትን የሚሰጠን።

ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም” (ዮሐንስ 14፡27)። በእግዚአብሔር ላይ የማይነቃነቅ፣ የተተከለ፣ የጸና ሕይወት የምትመራ ነፍስ እንደ ኢዮብ “ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ፤ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ” ትላለች (ኢዮብ 13፡15)።

ሸክም የሚቀለው እንደኛው ሰው ወደ ሆኑ ደካማ ፍጡራን በመሄድ ሳይሆን እግዚአብሔርን በማወቅና በእርሱ ላይ ፍጹም በመተማመን ነው። እርሱም እንዲህ ይላል፤ “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ **እኔም አሳርፋችኋለሁ።** ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ **ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ**” (ማቴዎስ 11፡28-30)። ዝዐ

“በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች

ሆነው ሳሉ የበግ ለምድ

ለብሰው መካከላችሁ በመግባት

ከሚያሽምቁ ሐሰተኛ ነቢያት

**ተጠንቀቁ።**

**ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤**

ከእሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣

ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?

እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ

ጥሩ ፍሬ፣

መጥፎ ዛፍ ግን

መጥፎ ፍሬ ያፈራል።

ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣

መጥፎም ዛፍ ጥሩ ፍሬ

ማፍራት አይችልም።

ጥሩ ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ

ይቈረጣል፤

ወደ እሳትም ይጣላል።

ስለዚህ

**በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ”**

ማቴዎስ 7፡15-20።

